የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት
ETHIOPIAN DIASPORA SERVICE

In Association with

I.S Promotions &
Special Events

presents

# ETHI OPIA



## ETHIOPIA FOR ME, I FOR ETHIOPIA

**FIRST EVER BOOK ON ETHIOPIAN COMMUNITY** TO SHOWCASE THE VALUE AND CULTURE



*Lucy, a 3.2 million-year old fossil skeleton of a human ancestor, was discovered in 1974 in Hadar, Ethiopia.*

This First Edition of the "Ethiopia for Me, I For Ethiopia"
Showcasing the History and Impostant aspects of Ethiopia from all walk of life.
Conceptualized and Produced by :IS Promotions & Special Events
Contents by - Individuals / Edited by - Joohi Qadri /Photography - Unspalsh.com / Vikas B
Design,Created & Published by

DCOM Designs

Printed at: Galadari Press, Al Quoz, Dubai
All right reserved. No part of this book may be reproduced or transmitted in any form or by any means, electronically or mechanically, without prior permission in writing from the producers.
"Ethiopia for Me, I For Ethiopia"- First Edition- 2022©DCom Designs FZE
All pictures copyright©IS Promotions & Special Events
All Design, Content & Images are provided and later approved by all the persons featured in this Edition.


Roaring Ethiopia







የክብርት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ መልዕክት፤

ውድ በመላው ዓለም የምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፤

‘ኢትዮጵያዊን ከሀገሩ እንጂ ሀገሩን ከውስጡ ማውጣት አይቻልም’ እንደሚባለው ከሀገራችሁ ርቃችሁ ብትኖሩም ሁልጊዜ ሀገራችሁ በውስጣችሁ እንዳለችና እንደማትረሷት በምታደርጓቸው እንቅስቃሴዎች እንረዳለን። በተለይም በሀገራችን የለውጥ ጸሐይ ከበራበት ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ እያጋጠሙን ያሉ ፈተናዎችን ለመጋፈጥ የምናደርገውን ትግል በባለቤትነት ስሜት ከጎናችን ሆናችሁ በመደገፍ እያበረከታችሁ ያለው አስተዋጽኦ ዘወትር ሲታወስ የሚኖር እንደሆነ በዚህ አጋጣሚ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

ለውጡን ተከትሎ መንግስት ትኩረት ከሰጣቸው ጉዳዮች መካከል የዳያስፖራ ጉዳይ ይገኝበታል። ከዚህም ጋር በተያያዘ በለውጡ ማግስት በልዩ ልዩ የዓለም ክፍል የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ለማነጋገር እንቅስቃሴ ተደርጎ እንደነበር ይታወሳል። በዚህም ጉዞ በጀርመን ፍራንክፈርት፣ በአሜሪካ በሚገኙ የተለያዩ ከተሞች፣ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ እንዲሁም በመካከለኛው ምስራቅ ዱባይ በመዘዋወርና ሰፋፊ መድረኮችን በማመቻቸት ‘ግንቡን እናፍርስ፤ ድልድዩን እንገንባ’ በሚል መርህ ከዳያስፖራው ጋር ውይይት ተደርጓል። በወቅቱም ለዘመናት የተገነባው የልዩነት ግንብ ፈርሶ ኢትዮጵያውያን በመደመር መርህ ለመሰባሰብ፣ የሀገራቸውን ጥቅም ለማስከበርና የሁልጊዜም አጋርነታቸውን ለማረጋገጥ ዝግጁ መሆናቸውን አሳይተዋል። መንግስትም ለዚህ ከፍተኛ የዳያስፖራ መነሳሳት የሚመጥን አደረጃጀት በመፍጠር የዳያስፖራውን ተሳትፎ ለማትጋት እንደሚሰራ ቃል በገባው መሰረት ከሶስት ዓመት በፊት በዳያስፖራ ጉዳይ ላይ ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎትን አቋቁሟል፤ ጥረቱም አበረታች ውጤትን በማስመዝገብ ላይ ይገኛል።

ኢትዮጵያ ብዙ ተስፋዎች ያሏት ሀገር ብቻ ሳትሆን ለዕድገት የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ግብዓቶች ተሟልተው የተሰጧት ሀገር ናት። ይህንን የተገነዘቡ አንድ አንድ አፍራሽ ሀይሎች ሀገራችን ይህን ዕምቅ አቅሟን ተጠቅማ እንዳታድግና በቀጠናው ያላት ሚና እንዳይጎላ ተደራራቢ ጫና በመፍጠር ላይ ይገኛሉ።

ጫናዎቹ ሀገራዊ ለውጡ እውን በሆነባቸው ባለፉት አራት አመታት መደጋገማቸውንና ሀገራችን ከዚህ በፊት ካጋጠሟት ችግሮች የተለዩ መሆናቸውን በማየት ሀገር ወዳድ የሆንን አካላት ሁሉ ‘ለምን?’ ብለን እንድንጠይቅ የሚያስገድዱ መሆናቸው ግልጽ ነው። የጥያቄውን መልስ ለማግኘትም ሩቅ መሄድ አይጠበቅብንም። ለውጡና ዓላማዎቹን ብቻ ማስታወስ በቂ ነው። ለውጡ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ውስጥ ህብረ ብሔራዊ አንድነት እንዲዳብር፣ ኢትዮጵያ በሁሉም ዜጎቿ አቅም ለምታ ለሁሉም ዜጎቿ እንድትተርፍ፣ ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብት፣ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቶቿን ተጠቅማ እንድትለማ፣ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያለን ግንኙነት በጋራ ተጠቃሚነትና መከባበር ላይ ተመስርቶ ወደ ቀጠናዊ ትስስር እንዲያድግ በመስራት ላይ ይገኛል።

ይህ ሀገራዊና ቀጠናዊ ትስስርና ዕድገትን ታላሚ አድርጎ የተነሳ ለውጥ ግቡን እንዲመታ የተራመድናቸው እርምጃዎች ብዙ እንደሆኑት ሁሉ የኢትዮጵያ ግስጋሴ ወደ ኋላ እንዲራመድ ደግሞ ከየአቅጣጫው ጫና እየተፈጠረበት ይገኛል። በሀገር ውስጥ ያጋጠመን የሰሜን ዕዝ ጥቃትና እሱን ተከትሎ የተፈጠሩ ግጭቶችና መፈናቀሎች፣ ይህን ሰበብ አድርጎ በሀገራችን ላይ ለመፍጠር የተሞከሩ ያልተገቡ ጫናዎችና ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሙሌትን ለማስተጓጎል እየተሸረቡ ያሉ ሴራዎች ለውጡን መቀልበስ ባይችሉም የለውጡን ሂደቱና ሀገራችንን በርካታ ፈተናዎችን እንዲጋፈጡ እያደረጉ ይገኛሉ።

በመላው ዓለም የምትገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንም ይህን ተገንዝባችሁ ለሀገራችሁ በተናጠልም ሆነ በህብረት እያደረጋችሁ ስላለው ዘርፈ ብዙ ድጋፍ በድጋሚ ምስጋናዬን መግለጽ እወዳለሁ። በሀገራችሁ ላይ የተቃጡ ያልተገቡ ጫናዎችን ለማለዘብ የምታካሂዷቸው የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስራዎች፣ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችንና ወቅታዊ ሀገራዊ ጥሪዎችን ለመደገፍ የምታሰባስቡት ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት፣ ወደ ሀገር ቤት የምትልኩት በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ሬሚታንስ፣ በንግድ፣ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም ዘርፎች እያደረጋችሁት ያለው ተሳትፎ የሚበረታታና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ተግባር መሆኑን ማሳሰብ እወዳለሁ። በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረውን ግጭት በሰላም ለመፍታት የተፈረመውን ስምምነት ተከትሎም በድህረ የሰላም ስምምነት ለምናከናውናቸውና ዘላቂ ሀገራዊ ፋይዳ ላላቸው ተሳትፎዎች ከወዲሁ ራሳችሁን እንድታዘጋጁ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ሀገራችሁን ለመደገፍ የምታደርጓቸው እንቅስቃሴዎችን መንግስት በከፍተኛ አድናቆት የሚመለከተው ብቻ ሳይሆን፣ ስራዎቻችሁም ዕውቅና እንዲሰጣቸውና በማስታወሻነት እንዲዘከሩ በመስራት ላይ ይገኛል። ከዚህም ጋር በተያያዘ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች የዕውቅና እና የመጽሐፍ ምረቃ መርሀ ግብር አዘጋጅቷል። መርሀ ግብሩ በየአደረጃጀቶቻችሁ እያደረጋችሁላት ላለው ድጋፍ መንግስታዊ ዕውቅና የመስጠትና በዚህም ተበረታትታችሁ ለበለጠ ስራ እንድትነቃቁ ማድረግ ዓላማን ሰንቆ የሚካሄድ ሲሆን፣ ወደፊትም በልዩ ልዩ ዘርፎች የላቀ አስተዋጽኦ ያበረከቱ የዳያስፖራ ማህበረሰብ አባላትን ማበረታታትና ዕውቅና የመስጠት ስራ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።



የክቡር አቶ ደመቀ መኮንን ም/ጠ/ሚ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መልዕክት፤

ውድ በመላው ዓለም የምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፤

ሀገራችሁ በአስጋሪ ሁኔታ ውስጥ ባለችበት ወቅት ሁሉ ከጎኗ በመቆም እያደረጋችሁ ስላለው ያልተቋረጠ ድጋፍና ሀገራዊ አለኝታነታችሁ ምስጋናዬ በቅድሚያ ይድረሳችሁ።

በበርካታ ሀገራት ተሞክሮ እንደታየው ዳያስፖራው የዕድገት አማራጭ በመሆን ዕውቀት፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሀገር ቤት ለማሸጋገር ይሰራል። ከፍተኛ የኢንቨስትመንትና የውጭ ምንዛሪ ፍሰት ምንጭ በመሆንም ለሀገራት ዕድገት ጉልህ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል። በሚኖርናቸው ሀገራት የሀገሩ አምባሳደር በመሆን ባህልና ታሪኳን በማስተዋወቅና የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስራዎችን በማካሄድ ድጋፍ ያደርጋል። በሀገር ቤት ለሚከናወኑ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች የሚያስፈልጉ ሀብቶችን በማሰባሰብም ሁነኛ የልማት አጋር በመሆን ይሰራል።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራም በፈጠራቸው አደረጃጀቶች አማካኝነት ከሀገሩ ጋር ያለውን ትስስር የሚያጠናክሩ ዲፕሎማሲያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ሰፋፊ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል። ባለፉት አራት ዓመታት እየተጋፈጥናቸው ካሉ ውስጣዊና ውጫዊ ጫናዎች አንጻር የዳያስፖራው ድጋፍ ባይኖር እንደ ሀገር ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ልንገባባቸው የሚችሉ ዕድሎች ሰፊ ነበሩ። ዳያስፖራው አገሩን ታድጓል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ዳያስፖራው አሁንም ጫናዎቹ ቅርጻቸውን እየቀያየሩ የሚመጡ መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ ሁልጊዜም ለዘላቂ ሀገራዊ ጥቅሞቻችን ያለውን አለኝታነት አስጠብቆ እንዲቀይ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን ማቅረብ እወዳለሁ።

በሀገር ቤት ያሉ ኢትዮጵያውያን ዕድርና ዕቁብን የመሳሰሉ የመሰባሰቢያና የመደጋገፊያ መድረኮች አሏቸው። መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ትልልቅ ማህበረሰባዊ አደረጃጀቶችንም ፈጥረው እርስ በእርስና ከሀገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር አጠናክረው ለሀገራዊ አንድነት በመስራት ላይ ይገኛሉ። ዳያስፖራውም ከተለያዩ የዓለም ክፍል ከመጡ ዜጎች ጋር በጋራ እንደመኖሩ መጠን  አደረጃጀቱ ጠንካራ፣ ሀገራዊ አንድነት ያለውና አለማቀፋዊነትን የተላበሰ ለመሆን ሰፊ ዕድል አለው። እነዚህን ተሞክሮዎች በመውሰድ ዳያስፖራዎች በያሉባቸው አካባቢዎች ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን ፈጥረው እንደሚንቀሳቀሱ ይታወቃል። አደረጃጀቶቹም ዳያስፖራው እርስ በእርሱ እንዲረዳዳ ከማድረግ ባለፈ እንደ ሀገር የሚገጥሙንን ፈተናዎች ለማሸነፍ የሚያገለግሉ ተቋማት ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። የተደራጀ ዳያስፖራ በሚኖርበት ሀገር መብትና ጥቅሙን ከማስከበር ባለፈ ሀገሩን የሚጠቅሙ ተግባራትን ለማከናወን ምቹ ሁኔታዎች እንደሚፈጠሩለት የቅርብ ጊዜ ተሞክሮዎቻችን ምስክር ናቸው።

ከዚህም ጋር በተያያዘ በየሀገሩ ያሉ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች ባከናወኗቸው ተግባራት የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብሩ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎች ተከናውነዋል። ከፍተኛ የሆነ ሀብት በማሰባሰብም በሀገር ቤት ላሉ ፕሮጀክቶች ድጋፍ ተደርጓል። የዳያስፖራው ጥረት ታክሎበት በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረውን ግጭት በሰላማዊ መንገድ መፍታት የሚያስችል ስምምነት ተፈርሞም ወደ ስራ ተገብቷል። ይህም በድህረ የሰላም ስምምነት የሚኖረን የዳያስፖራ ተሳትፎ በግጭት ምክንያት የተጎዱ ወገኖችን  ከማቋቋም ባለፈ  የዳያስፖራውን ተሳትፎ ከዘላቂ ሀገር ግንባታ ስራዎች ጋር ለማስተሳሰር ዕድል ፈጥሮልናል።

የተወደዳችሁ በየሀገራቱ የምትገኙ የዳያስፖራ አደረጃጀቶችና አባላት ኢትዮጵያ ያላትን ተስፋናዕድል እንዲሁም ያለችበትን ችግር ተረድታችሁ ተስፋውን ወደ ጥቅም መቀየሪያ ከችግሩ ደግሞ መውጫው መንገድ በአንድነት መቆምና በተባበር መሆኑን አምናችሁ ሀገራችሁን ለማገዝ ስለምታከናውኑት ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ጥረታችሁ የተለየ ምስጋና በመፈለግ ሳይሆን ሀገርን መልሶ በመክፈል መንፈስ የሚደረግ እንቅስቃሴ አካል መሆኑ ቢታወቅም ስራችሁ ዕውቅና እንደተሰጠው ለማሳየት እንዲያገለግል ለተዘጋጀው የዳያስፖራ አደረጃጀቶች የዕውቅና እና የመጽሐፍ ምረቃ መርሀ ግብር እንኳን አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ። ዳያስፖራው እያደረጋቸው ያሉ ጥረቶችን ለማበረታታት እንዲቻል መሰል የዕውቅና እና የማበረታቻ መድረኮች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው እያሳሰብሁ፣ ዳያስፖራው በተናጠልም ሆነ በልዩ ልዩ አደረጃጀቶቹ አማካኝነት የጀመራቸውን አበረታች ተግባራት አጠናክሮ በመቀጠል የዘላቂ ሀገገራዊ ልማት አለኝታነቱን እንዲያሳይ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ክቡር አቶ ደመቀ መኮንን ም/ጠ/ሚ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት
ETHIOPIAN DIASPORA SERVICE



የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ክቡር ዶ/ር መሐመድ እንድሪስ መልዕክት፤

ውድ በመላው ዓለም የምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፤

ባለፉት አራት አመታት መንግስት ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ልዩ ትኩረት በመስጠቱ የዳያስፖራውን ዘርፈ ብዙ ተሳትፎ የሚያሳልጡ ህጋዊና መዋቅራዊ ማዕቀፎችን ማዘጋጀቱና ወደ ስራ ማስገባቱ ይታወሳል። ከነዚህም መካከል የዳያስፖራ ጉዳዮችን እንዲያስተባበር የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት መቋቋሙ፣ ዳያስፖራው በሚኖርባቸው ሀገራት ያሉ የኢፌዴሪ ሚሲዮኖች የዳያስፖራ ጉዳዮችን በተሻለ ብቃት መምራት የሚያስችላቸው አሰራሮች መዘርጋታቸው፣ ዜጋ ተኮር የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መተግበር መጀመሩ እንዲሁም ለዳያስፖራ ተሳትፎ ዝግ የነበሩ የፋይናንስ ዘርፎች ክፍት መሆናቸው የሚጠቀሱ ናቸው።

ለዳያስፖራ ተሳትፎ በተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች አማካኝነትም ባለፉት አራት የለውጥ አመታት በሁሉም የዳያስፖራ ወረቶች የዳያስፖራው ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ በማደግ ላይ ይገኛል። ኢትዮጵያ አስጨናቂ ጊዜ ላይ በነበረችበት ወቅት ዳያስፖራው ከዳር እስከ ዳር በመንቀሳቀስ የሀገሩን ጥቅም ለማስከበርና እውነቷን ለማስረዳት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በ'#በቃ' ንቅናቄ የተካሄዱ ዓለም አቀፍ ሰላማዊ ሰልፎችና የዲጂታል ዲፕሎማሲ ዘመቻዎች ሁሌም የሚታወሱ ናቸው። ኢትዮጵያ በችግሯ ወቅት 'ልጆቼ ኑ' ብላ ጥሪ ስታቀርብም በመቶ ሺዎች የሚቀጠሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከያሉበት ወደ ሀገራቸው በመትመም የሀገራቸው የቁርጥ ቀን ልጆች መሆናቸውን አረጋግጠዋል። በታላቁ ጉዞ ወደ ሀገር ቤትና በከኢድ እስከ ኢድ ጥሪዎች የታቀዱ ዲፕሎማሲያዊ፣ ማህበረ-ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግቦች የተሳኩት በዚህ ምክንያት ነው።

ዳያስፖራው ካከናወናቸው ሰፋፊ የፐብሊክ ዲፕሎማሲና የገጽታ ግንባታ ስራዎች በተጨማሪ የልማት ተሳትፎውም የጎላ ነበር። በተጠቀሱት የለውጥ አመታት ዳያስፖራው ለወቅታዊ ሀገራዊ ጥሪዎችና ፕሮጀክቶች ከሶስት ቢሊዮን ብር በላይ በአይነትና በገንዘብ ድጋፍ አድርጓል። ከ12 ቢሊዮን ዶላር በላይ በሬሚታንስ መልክ ወደ ሀገር ቤት በመላክም ለውጭ ምንዛሪ ግኝታችን ከፍተኛ አበርክቶ አድርጓል። የኢንቨስትመንት፣ የዕውቀትና ክህሎት ሽግግር ተሳትፎም በየጊዜው በማደግ ላይ ይገኛል።

በዳያስፖራቸው ተሳትፎ እመርታዊ ለውጥ ያመጡ ሀገራት ተሞክሮዎች ዳያስፖራው ያሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ወረቶቹን በሚገባ ተጠቅሞ በሀገሩ ልማት ላይ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት በተደራጀ ሁኔታ መንቀሳቀሱ ወሳኝ መሆኑን ያሳያሉ። ያለፉት አራት አመታት የዳያስፖራ ተሳትፎ ስራዎቻችንና ውጤቶቻቸው ያረጋገጡትም ይህንኑ ሀቅ ነው። ኢትዮጵያውያን በያሉበት ሀገር ያቋቋሟቸውን በርካታ የዳያስፖራ አደረጃጀቶችን በመጠቀማቸው ድምጻቸው መሰማትና ተጽዕኗቸው ማደግ ከመቻሉም በላይ በሀገራዊ ልማት ላይ ያላቸው አስተዋጽኦም እየጨመረ መጥቷል።

ይህን የተደራጀ የዳያስፖራ ተሳትፎ ማትጋትና ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር ተገቢ በመሆኑ በየሚኖሩበት ሀገር የላቀ አስተዋጽኦ ማበርከታቸው በየሚኖሩበት ሚሲዮን ተለይተው ለቀረቡ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች እውቅና በመስጠት ይበልጥ ተሳትፏቸውን ለማሳደግ እንዲሁም ሌሎችም የእነሱን አርአያነት ተከትለው ለተሻለ ስራ እንዲነሳሱ ለማድረግ ይህን የዳያስፖራ አዋርድና የመጽሐፍ ዝግጅት ማሰናዳት አስፈልጓል።

ያከናወናችኋቸው ስራዎች ለዕውቅና ላበቋችሁ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች በሙሉ እንኳን ደስ አላችሁ እያልሁ፣ ሽልማቱ እናንተን ከማበረታታት ባለፈ ሌሎች አደረጃጀቶችም ፈለጋችሁን እንዲከተሉ እንደሚያደርግ ያለኝን እምነት መግለጽ እወዳለሁ። አደረጃጀቶቻችሁን ተጠቅማችሁም በቀጣይ እንደ ሀገር ለማከናወን ላቀድነው የመልሶ ግንባታና ዘላቂ የዳያስፖራ ተሳትፎ ስራዎች አጋርነታችሁን አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ክቡር ዶ/ር መሐመድ እንድሪስ



# Amazing Africa



Africa is the world's second-largest and second-most populous continent, after Asia in both cases. At about 30.3 million km2 (11.7 million square miles) including adjacent islands, it covers 6% of Earth's total surface area and 20% of its land area With 1.3 billion people as of 2018, it accounts for about 16% of the world's human population. Africa's population is the youngest amongst all the continents; the median age in 2012 was 19.7, when the worldwide median age was 30.4. Despite a wide range of natural resources, Africa is the least wealthy continent per capita, in part due to geographic impediments, legacies of European colonization in Africa and the Cold War, predatory/neo-colonialistic activities by Western nations and China, and undemocratic rule and deleterious policies. Despite this low concentration of wealth, recent economic expansion and the large and young population make Africa an important economic market in the broader global context.

The continent is surrounded by the Mediterranean Sea to the north, the Isthmus of Suez and the Red Sea to the northeast, the Indian Ocean to the southeast and the Atlantic Ocean to the west.

The continent includes Madagascar and various archipelagos. It contains 54 fully recognised sovereign states (countries), eight territories and two de facto independent states with limited or no recognition. Algeria is Africa's largest country by area, and Nigeria is its largest by population. African nations cooperate through the establishment of the African Union, which is headquartered in Addis Ababa.

Africa straddles the equator and the prime meridian making it the only continent in the world to be situated in all four cardinal hemispheres. It is the only continent to stretch from the northern temperate to southern temperate zones.

The majority of the continent and its countries are in the Northern Hemisphere, with a substantial portion and number of countries in the Southern Hemisphere. Most of the continent lies in the tropics, except for a large part of Western Sahara, Algeria, Libya and Egypt, the northern tip of Mauritania, the entire territories of Morocco, Ceuta, Melilla and Tunisia which in turn are located above the tropic of Cancer, in the northern temperate zone. In the other extreme of the continent, southern Namibia, southern Botswana, great parts of South Africa, the entire territories of Lesotho and Eswatini and the southern tips of Mozambique and Madagascar are located below the tropic of Capricorn, in the southern temperate zone.

Africa is home to much biodiversity; it is the continent with the largest number of megafauna species, as it was least affected by the extinction of the Pleistocene megafauna. However, Africa also is heavily affected by a wide range of environmental issues, including desertification, deforestation, water scarcity, and other issues. These entrenched environmental concerns are expected to worsen as climate change impacts Africa. The UN Intergovernmental Panel on Climate Change has identified Africa as the continent most vulnerable to climate change.

African Union






The history of Africa is long, complex, and has often been under-appreciated by the global historical community. Africa, particularly Eastern Africa, is widely accepted as the place of origin of humans and the Hominidae clade (great apes). The earliest hominids and their ancestors have been dated to around 7 million years ago, including Sahelanthropus tchadensis, Australopithecus africanus, A. afarensis, Homo erectus, H. habilis and H. ergaster— the earliest Homo sapiens (modern human) remains, found in Ethiopia, South Africa, and Morocco, date to circa 200,000, 259,000, and 300,000 years ago respectively, and Homo sapiens is believed to have originated in Africa around 350,000–260,000 years ago.

Early human civilizations, such as Ancient Egypt and Carthage emerged in North Africa. Following a subsequent long and complex history of civilizations, migration and trade, Africa hosts a large diversity of ethnicities, cultures and languages. The last 400 years have witnessed an increasing European influence on the continent. Starting in the 16th century, this was driven by trade, including the Trans-Atlantic slave trade, which created large African diaspora populations in the Americas. In the late 19th century, European countries colonized almost all of Africa, extracting resources from the continent and exploiting local communities; most present states in Africa emerged from a process of decolonisation in the 20th century.





# Ethiopia
LAND OF ORIGINS



Make time to explore Ethiopia and you will be put in touch with your own origins As you travel across her great heights and explore her deep places you will experience breath-taking beauty and astounding achievements.

For this is a land of origins, it is the cradle of humanity, where we first walked on two legs. It is also the source of the Blue Nile, the great river whose power and fertility nurtured the origin of civilization itself. And it is the origin of one of life's great pleasures - Coffee, our gift to the world. So come to Ethiopia and take the time to be enchanted by her extraordinary past and to share in her dynamic present. Come, and you will discover why Ethiopia is origins in many ways.





**ADDIS ABABA**

ETHIOPIA










Addis Ababa Bole international airport which is the hub for plenty of connection flights to the different corners of Africa is an ideal spot for stopover tourists. The city is full of rich and captivating history and culture. It won’t take you long to get a feel for it within a day trip.

Addis Ababa is also an interesting city for nightlife, The Jazz music in Bole area and the cultural restaurant that dotted across the bole and Kazanchis area give a lifetime experience.

As Ethiopia is the origin place of coffee visiting coffee shops around the piazza area is one of the intriguing experiences to be done in the city. Check the lavish museums around 5 and 6 kilo areas to elevate your knowledge of how Ethiopia is an old nation more than you could imagine.

If you are into history and historical landmarks there are a lot of important squares that keep significant monuments and icons. Go to the main city centers and you will find many astonishing landmarks. Immerse into the unique food culture of Ethiopia by testing the local dishes or being a part of the food preparation itself. There some companies who provide a gastronomy tour in the city to take you around and let you experience the food preparation.

The newly developed boutique parks; Unity, Entoto, and Sheger Parks are the right spot for people who love city parks. The outdoor market at Mercato and the souvenir shops around the Ethiopian post office headquarter is an ideal place for shopping



## HISTORICAL WONDERS

Ethiopia is an ancient country whose unique cultural heritage, rich history and remarkable biodiversity are reflected in a tally of nine UNESCO World Heritage Sites - more than any other countries in Africa. Within i’s borders, you’ll find the world fourth-holiest Islamic city, along with as the oldest continuously- occupied town south of the Sahara. Compelling antiquities include the mediaeval rock-hewn churches of Lalibela and Gheralta, ruined palaces and temples dating back 3,000 years, the magnificient 17th century castles of Gondar and the oldest human fossils unearthed anywhere on the planet..




A UNESCO World Heritage site since 1980, Axum is 'Sacred' as Jerusalem, old as Rome and historical as Constantinople, is an exceptional place in Ethiopia. Considered the beacon of Ethiopian Christianity, Axum is the mirror of the glorious period of Ethiopia. Ruined palaces, obelisks, mausoleums, ruined churches, megalithic erected stones, coins, and manuscripts witness the golden period of the Aksumite Empire. The importance of the city is much elevated as it houses the most valuable and sacred relics of the tablet of Mosses or the arks of the covenant and as the place where one of the 'Three Wise Men' buried here.




Lalibela is found in the northern part of Ethiopia known for its rock hewn churches and amazing mountainous scenery. The old town of Lalibela with its rock hewn churches in and around it is a world heritage site registered by UNESCO. The rock hewn churches found in the villages of Bilbala, Yimrahane Christos, Naakuteklab, Genete Mariam and Asheten Mariam are among those found outside the Town and have got their own unique features. All churches are daily serving living culture and tradition including the annual religious festival Ethiopian Christmas.




Dubbed the Camelot of Africa, the city of Gondar — the capital of Ethiopia from 1636 until the mid 19th century — combines a modern veneer with an architectural sensibility harking back to the Middle Ages. The city's physical and architectural centerpiece is Fasil Ghebbi, a stone-walled Royal Compound containing half a dozen fairytale castles including the three-story original built by Emperor Fasil in the 1630s. The Fasil Ghebbi UNESCO World Heritage Site also incorporates several more remote constructions, most notably the Church of Debre Berhan Selassie, with its beautifully painted interior.




Hidden away in the mountains ancient treasures, the churches in Gheralata are described as ’’ the greatest of the historical-cultural heritage of the Ethiopian people’’. The Gheralta Mountains chain is found deep within the northern high plateau of the Tigray region. The geography of the Gheralta range is one of the most striking landscapes in all of Ethiopia. It’s picturesque setting, dazzling heights, age-old rock painting churches from the middle ages make it one of the premium destinations to be explored. It is tentatively listed as UNESCO world heritage site in 2018.




With its 368 alleyways squeezed into just 1 sq.km., Harar is believed to be the fourth holiest city after Mecca, Madina and Jerusalem. The 82 mosque and 102 Shrines within the fortified city formed the largest concentration of mosques in the world. Noted for being a center of Muslim scholarship and commerce, it once issued its own currency. The city’s lively markets and unique gey gar (city houses) are relicts of the many centuries when Harar served as the most important trade emporium in the Horn of Africa, linking the ports of the Somali coast to the fertile Ethiopian interior. Harar Jugol was inscribed as a UNESCO Heritage site




The capital of Coffee producing area, lively city blessed with excellent tourist facilities and a warm location in the fertile western highlands. The town is named after the 19th-century Islamic kingdom of Jimma, which lay at the meeting point of several trade routes. The last autonomous ruler of Jimma was king Abba Jiffar, whose impressive palace in Jiren, the outskirts of city has been restored with partial funding from UNESCO. Other attractions include the daily central market, the ethnographic displays at the Jimma Museum, a nearby patch of forest inhabited by the spectacular colobus monkey, and out-of-town Lake Boye with its resident hippos.



Dire Dawa - The queen city of Deserts

Ethiopia’s one of the largest city, Dire Dawa was established in 1902 as a major stop along the railway between Addis Ababa and Djibouti as it traversed the hot dry plains north of Harar. The city is split into two distinct quarters by the normally dry Dachata River. To the northwest is Kezira, a stately colonial-style quarter whose wide leafy avenues converge on the impressive French-built railway station. Southwest of the river, the old Islamic quarter of Megaala has an altogether more organic feel, epitomized by a trio of lively daily markets offering kafia (foodstuff & other local items) Taiwan (electronic and other imported goods), and Ashewa (livestock market).



Tiya Stelae Field

The UNSECO – listed Tiya Stelae Field is an important stelae cluster at the south end of Tiya village, about 35 km after the turn off to Adadi. Tiya contains 41 stelae up to 5 km in height (including the buried portions), engraved with enigmatic symbols including swords. They mark graves of individuals aged between 18 and 30 who died around 700 years ago and were buried in the fetal position, though little is known about the culture that carved them.

Ethiopia is one of Africa's most beautiful countries and its landscapes are epic in both scale and beauty. Here is a place where you can trek more than 9800ft above sea level (the Simien and Bale mountains) or visit the lowest place on the African continent, the Danakil Depression. In between, there are lush highlands and stirring deserts, vertiginous canyons and sweeping savanna, vast lakes and high plateaus. If you look hard enough, you’ll also find landmarks of great significanc, from the source of the Blue Nile to, again, the mesmerizingly desolate Danakil Depression, peppered with an astonishing 25% of Africa’s active volcanoes.

Ethiopia is one of the oldest civilizations, the source of the mighty Nile River, and is endowed with a long-aged heritage and uninterrupted political independence. Located in the horn of Africa's Rift Valley region and known globally as the origin of mankind, Ethiopia offers a variety of tourism attractions such as Natural, Cultural, Historical, Mystical, Athletics, and MICE.

Ethiopia commands a large and untapped potential for the tourism and hospitality business. The increasing number of tourists and the evolving profile of today's traveler demand a host of new tourism offerings and infrastructure projects

## INVESTMENT AREAS RESERVED ONLY FOR DOMESTIC INVESTORS

- Hotel, lodge, resort, motel, guest house, pension services (excluding those that are star designated)
- Restaurant, tearoom, coffee shops, bars, night clubs and catering services (excluding star designed national cuisine restaurant services)
- Travel agency, travel ticket sales and trade auxiliary services
- Tour operation
- Transport services (excluding Railway, Cable car, Cold-chain, freight transport having a capacity of more than 25 tones and transport services reserved for joint investment with the government or domestic investors)
- Producing bakery products and pastries for domestic market

## INVESTMENT AREAS RESERVED FOR JOINT INVESTMENT (DOMESTIC AND FOREIGN INVESTORS)

- Domestic air transport service
- Cross country transport service using buses with a seating capacity of more than 45 passengers
- Urban mass transport service with large carrying capacity

Note that a foreign investor jointly investing with a domestic investor in areas listed above shall not hold more than 49% of the share capital of the enterprise

## INVESTMENT AREAS OPEN TO FOREIGN INVESTORS

Investment areas that are not listed herein the above; are open to foreign investors.

# WHY INVEST IN TOURISM IN ETHIOPIA

1. GROWING DOUBLE DIGIT ECONOMY

The International Monetary Fund (IMF) ranks Ethiopia as among the five fastest growing economies in the world. New buildings are rising in the cities daily and sectors like tourism, trade, agriculture, infrastructure, education, health, sport and many others are developing at a fast pace. Ethiopia is a country in motion and presents a positive energy for investors.

2. STABILITY AND SECURITY

Ethiopia is stable and safe for travelling, and the locals are welcoming and hospitable. Ethiopia is ranked positively in the Global Competitiveness Report in terms of 'Business costs of crime and violence' (44 out of 144 countries).

3. GROWING TREND OF INTERNATIONAL TOURISM ARRIVALS

Inbound Tourist Arrivals in Ethiopia have grown from 115,000 in 1999 to almost 849,000 in 2019.

4. INTERNATIONAL AIR CONNECTIONS

Thanks to its strategic location in the crossroads between Africa, the Middle East, and Asia and to the national carrier Ethiopian Airlines (a member of Star Alliance), Addis Ababa is an air transportation hub of Africa. Ethiopian Airlines is a dynamic company constantly expanding its network of flights, currently serving more than 120 destinations worldwide.

# INVESTMENT INCENTIVES
# INCENTIVE PACKAGES

The following attractive investment incentives are given by the investment board for seven potential destinations; Abijatta-Shalla National Park, Bale Mountain National Park, Semien Mountains National Park, Gheralta Mountains, Erta Ale, Abaya and Chamo lakes, Arba Minch and Wenchi Crater Lake.

• 5 years of income tax exemption for those who invest on the five specified regions.

• Duty free privileges on Capital good and spare-parts.

• Duty free privileges on finishing construction materials (if they're going to build the hotel themselves).

• Duty free import of the following vehicles. [ Station wagons (NEW), A bus (minimum capacity of 30 passengers excluding the foldable seats) ]



በተለያዩ አገራት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመደራጀት የሚያጋጥሟቸውን ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከመፍታት ባሻገር ለአገራቸው ሠላም፣ ለገጽታ ግንባታ እና ዕድገት መረጋገጥ ጉልህ አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ። እነዚህ አደረጃጀቶች ኢትዮጵያ በፈተና ውስጥ በሆነችባቸው ወቅቶች የአድቮኬሲ ሥራ በመሥራት የኢትዮጵያን ጥቅም እና ክብር በማስጠበቅ፣ በአገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ የማይተካ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ።

አደረጃጀቶቹ እያከናወኗቸው ያሉ ተግባራት አገራዊ ፋይዳቸው ጉልህ ለመሆኑ ያለፉት ሁለት አመታት ተሞክሮዎቻችን ህያው ምስክሮች መሆናቸውን መጥቀስ ይቻላል። በመሆኑም በልዩ ልዩ የዓለም ክፍል የሚገኙና በየደረጃቸው የላቀ አስተዋጽኦ ያበረከቱ የዳያስፖራ አደረጃጀቶችን በመለየት ለስራቸው እውቅና መስጠት እየሰሩ ላሉት ተጨማሪ አቅምን የሚፈጥርና የሚያበረታታ ለሌሎችም መነሳሳትን እንደሚፈጥር በማመን ከኢፌዲሪ ሚሲዮኖች ጋር በመተባበር በአምስት አህጉራትና ከሀያ በላይ አገራት የሚገኙና የላቀ አስተዋጽኦ ያበረከቱ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አደረጃጀቶችን ማስተዋወቅ አስፈልጓል።



## 1. በኬንያ የኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ማህበር

ኢትዮጵያና ኬንያ ከሀምሳ አምስት ዓመታት በላይ በመልካም ጉርብትና እና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ዘመን ተሻጋሪ ግንኙነት ያላቸው አገሮች ናቸው። ኢትዮጵያና ኬንያ ጠንካራ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ዲፕሎማሲያዊ ትብብር ያላቸው አገሮች ሲሆኑ፣ ተመሳሳይ ባህልና ቋንቋ ያላቸው ህዝቦችንም ይጋራሉ። በቋሚነት ኑሯቸውን በኬንያ መስርተው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም በርካቶች ናቸው። ኬንያ እ.ኤ.አ. ከ1970ዎቹ ጀምሮ ከሀገራቸው በተለያየ ምክንያት ለሚወጡ ኢትዮጵያውያን ጊዜያዊም ይሁን ዘላቂ መቆያ አገር በመሆን ቆይታለች። በአሁኑ ወቅት በኬንያ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ከ30ሺ በላይ እንደሚሆኑ ይገመታል። ዛሬ በልዩ ልዩ የአለም አገራት በተለይም በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣ በካናዳና በአውስትራሊያ በብዘት ተበትነው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከ75% በላይ የሚሆኑት አሁን ወደ ሚኖሩበት የዓለም ክፍል ከመድረሳቸው በፊት መሸጋገሪያ አድረገው ከተጠቀሙባቸው አገሮች ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ የምትይዘው ኬንያ ነች።

በኬንያ እና ሚሲዮኑ በተወከለበት አገር የኮሙዩኒቲ አደረጃጀቶችና የሃይማኖት ተቋማት ህብረትን ጨምሮ በአጠቃላይ አስር የሚሆኑ የዳያስፖራ ስብስቦች አሉ። እንሱም የኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ማህበር በኬንያ፣ በኬንያ የኢትዮጵያውያን ሴቶች ድርጅት፣ በኬንያ የኢትዮጵያ ባለሙያዎች አንድነት ለዘላቂ ልማት መድረክ፣ የኢትዮ-ኬንያ የወዳጅነት ማህበር፣ በኬንያ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ህብረት፣ የሶማሌ ኮሚኒቲ፣ የቡርጂ ኮሚኒቲ፣ የጉራ ኮሚኒቲ እና ጉልቱም ቪዢን /የሃረርጌ/ ኮሚኒቲ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ከሰላሳ አመታት በፊት የተመሠረተው በኬንያ የኢትዮጵያውያን ማህበር አንዱ ነው።

# በኬንያ የኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ማህበር ሊቀመንበሩ መልዕክት፤


የኮሚኒቲ ማህበሩ ሊቀመንበር

በኬንያ የኢትዮጵያዊያን ማህበር ከ30 አመታት በፊት የተመሠረተ፣ በኬንያ መንግስት ህጋዊ ምዝገባና ፍቃድ ያለው እና በኬንያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውናያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በአንድ ጥላ ማህበር ስር በማስተባበር ለራሳቸውና አገራቸውንም እንዲጠቅሙ ለማድረግ በየጊዜው ልዩ ልዩ ጥረቶችን የሚያደርግ ማህበር ነው፡፡ ማህበሩ በተለያዩ ጊዜያት አገራችን በሰው ሰራሽም ይሁን በተፈጥሮ ችግር ሲገጥማት ለሚቀርቡ አገራዊ ጥሪዎች በኬንያ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በማስተባበር ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥ በማድረግ ሀገራዊ ሀላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል፡፡ በኬንያ የሚኖሩና ቆይታ አድርጎ የሚያልፉ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው የሚያስቡ፣ የተቻለቸውን ሁሉ ያለመቆጠብ የሚያደርጉ፣ አገራቸውንና ህዝባቸውን የሚወዱ እንደሆኑ በልዩ ልዩ መንገድ በተግባር ሲያሳዩ ቆይቷል፡፡ በኬንያ የሚኖርና በኬንያ የሚያልፈው ህዝባችን ለአገሩ ትልቅ አስተዋፅኦ ሊያደርግ የሚችል አቅምና ችሎታ እንዳለው በመገንዘብ በቅርብ ጎረቤት አገር እንዳለ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሰፊ አስተዋፅኦ የሚያደርግበትን የንግድና ልምድ ልውውጥ፣ የአቅም ግንባታ፣ የኢንቨስትመንት፣ የግንኙነት እና የጉዞ መሠረተ-ልማት ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ ከኬንያ መንግስት ጋር በመተባበር ቢሰራ እስከዛሬ ከሚታየውም የበለጠ አስተዋፅኦ ማድረግ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ህዝቧን ይባርክ!

በኬንያ የኢትዮጵያውያን ማህበር በኬንያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውናያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር በተለያዩ ጊዜያት አገራችን በሰው ሰራሽም ይሁን በተፈጥሮ ችግር ሲገጥማት ለሚቀርቡ አገራዊ ጥሪዎች ፈጣን ምላሽ በመስጠት አገራዊ ሀላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል።


የማህበሩ ተሳትፎዎች፤



• በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተፈጠረው ችግር ምክንያት ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን ከ60 ሺህ የአሜሪካን ዶላር በላይ በመሰብሰብ ድጋፍ አድርጓል።

• ማህበሩ ለችግር የተጋለጡ ወገኖቻችን ድጋፍ እንዲያገኙ በኬንያ የዳያስፖራ ማህበረሰቡን በማስተባበር 2,000 ኪ.ግ የሚሆን የተለያዩ አልባሳትን በማሰባሰብ ወደ ሀገር ቤት ልኳል።



• በአገራችን በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት በርካታ ሕፃናት ያለወላጅ በመቅረታቸው "አንድ ዳያስፖራ ለአንድ ቤተሰብ" በሚል መርህ ወላጅ አልባ ሕፃናት እንዲረዱ በተደረገው ጥሪ መሠረት የማህበሩ አመራር አባላት እያንዳንዳቸው አንድ አንድ ልጅ ለመርዳት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የቃል-ኪዳን ሰነድ በመፈራረም እ.ኤ.አ ከኤኘሪል/2022 ጀምሮ "ለወገን ደራሽ ወገን ነው" በሚለው መርህ ታሪካዊ ሃላፊነቱን እየተወጣ ነው።



• አንዳንድ የዓለም አቀፍ ሚዲያ ተቋማት በአገራችን ጉዳይ ላይ የተዛባ መረጃን በማውጣት እና በአገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባታቸው ምክንያት በመላው ዓለም የሚገኙ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት ይህንን የተሳሳተ አካሄድ በመቃወም እንዳደረጉት እንቅስቃሴ ሁሉ ኬንያ የበርካታ ዓለም አቀፍ ሚዲያ ተቋማት መቀመጫ አገር በመሆኗ የአገራችንን እውነታ ለማሳወቅ እና ሉዓላዊነቷን ለማስከበር በናይሮቢ ማህበሩ የ"#በቃ" (#Nomore) ዘመቻ ሰላማዊ ሰልፎች የማስተባበር ስራ አከናውኗል።

## 2. በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር

ኢትዮጵያና ጅቡቲ ዘመናትን ያስቆጠረ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የባህል ግንኙነት ያዳበሩ አገሮች ናቸው። የጅቡቲ ወደቦች ለኢትዮጵያ ገቢና ወጪ እቃዎች ዋነኛ መተላለፊያ በመሆናቸው ምክንያት የሁለቱ አገራት ግንኙነት በጠንካራ መሰረት ላይ የተገነባ እንዲሆን እድልን ፈጥሮለታል። ጅቡቲ ለኢትዮጵያ ያላትን ፋይዳ በመረዳትም ኢትዮጵያ የቆንስላ ጽ/ቤቷን በጅቡቲ የከፈተችው አገሪቱ የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ከነበረችበት እ.አ.አ ከ1923 ጀምሮ ነው። ጅቡቲም ከነጻነት በኋላ እ.አ.አ ከ1978 ጀምሮ ኤምባሲዋን በኢትዮጵያ ከፍታለች።

በጅቡቲ  ከመቶ እስከ መቶ ሃምሳ ሺህ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን እንደሚኖሩ  የሚገመት ሲሆን፣ ኢትዮጵያውያኑ ባቋቋሟቸው አደረጃጀቶች በመጠቀም እርስ በእርስ የመረዳዳት፣ የአገራቸውን ባህልና ታሪክ የማስተዋወቅ እንዲሁም ለአገራቸው ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን በማበርከት ላይ ይገኛሉ። በጅቡቲ የጎላ እንቅስቃሴ ከሚያደርጉ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች መካከል የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር፣ የኦሮሚያ  ልማት ማህበር፣ የአማራ ልማት ማህበር፣ የአፋር ልማት ማህበር፣ የድሬዳዋ ከተማ ተወላጆች ማህበር፣ የሶማሌ ኮሚኒት ማህበርና የሴቶችር ማህበር ይገኙባቸዋል፡፡ ከመካከላቸውም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር የላቀ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል።



# በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ስራ አስኪያጅ መልዕክት፤



በመላው አለም የምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በቅድሚያ እንኳን ለዚህ ቀን አደረሳችሁ አደረሰን። በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በጅቡቲ በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን አማካኝነት በመጀመሪያ እንደ መረዳጃ ማህበር የተቋቋመ ሲሆን፤ በሂደት እራሱን እያሻሻለ ጠንካራ የኮሚዩኒቲ ማህበር ለመሆን ችሏል።

ማህበሩ በጅቡቲ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውለደ ኢትዮጵያዊያን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ማለትም በኢኮኖሚ እና ማህበራዊ አገልግሎት ለሌሎች በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን አርዓያ በሚሆን መልኩ በተለይ በሀገራዊ ጉዳዮች ማህበሩ በጅቡቲ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በማስተባበር የቦንድ ግዥ በመፈፀም፣ በሀገርቤት በተለያየ ምክንያት የተፈናቀሉ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋም የሚውል ሀብት በማሰባሰብ፣ በጅቡቲ የሚኖሩ ዜጎቻችን ችግር ላይ ሲወድቁ በተናጠል ወይንም በጋራ አሰባስቦ /Mobilized/ በማድረግ ወደ አገር ቤት የመመለስ በርካታ ስራዎችን እያከናወነ የሚገኝ መረዳጃ ማህበር ነው።

ማህበሩ ከኤምባሲው ጋር በመተባበር በተለያዩ ማረሚያ ቤቶችና ፖሊስ ጣቢያዎች የሚገኙ ዜጎቻችን አስፈላጊ ቁሳቁስ በመያዝ ጉብኝት ያደርጋል። እንዲሁም በጅቡቲ በተለያዩ ሆስፒታሎች በመገኘት ከራሱ ወጭ የህክምና ገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል። በተጨማሪም በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር ለተጋለጡ ዜጎች የምግብ፣ የመጠለያና ወደ ሀገር ቤት የሚገቡበት ትራንስፖርት ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል። አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛል።

በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ት/ቤት በማህበረሰቡ ተሳትፎ እንዲገነባ በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ለጅቡቲ መንግስት ጥያቄ ቀርቦ መሬት መሠጠቱ ይታወሳል። በቦታው ላይ ግንባታ እሰኪጀመር ይዞታውን ለማስከበር የአጥር ሥራ የተካሄደ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅትም ለትምህርት ቤቱ ግንባታ የሚውል ሀብት ለማሰባሰብ በተቋቋመው ኮሚቴ አባል በመሆን ሀብት የማሰባሰብ ስራ እየሰራ ይገኛል።

በቀጣይም ማህበሩ በጅቡቲ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እርስ በእርስ እንዲደጋገፉ እና አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል። በተጨማሪም ዜጎቻችን ለበርካታ ጊዜ ሲጠይቁት የነበረው በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ት/ቤት ለመገንባት አጠቃላይ ማህበረሰቡን እና ባለድርሻ አካላትን አስተባብሮ የት/ቤት ግንባታ ሃብት በማሰባሰብ ግንባታው በአጭር ጊዜ እንዲጀመር በትኩረት እየተሰራ ይገኛል። ማህበሩ በቀጣይ ለማከናወን ካቀዳቸው ተግባት መካከል ለዜጎች ምቹ ሁኔታ መፍጠር እና ችግራቸውን በጋራ መፍታት፣ ደስታቸውን በጋራ ማክበር የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ በአገራቸው ልማት ግንባር ቀደም ተሳታፊ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይገኙበታል።

ኢትዮጵያ  በልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኖራለች

አሸናፊ ማረጌ

የማህበሩ ስራ አስኪያጅ



## የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር

ዜጎች በተለያዩ ምክንያቶች ከትውልድ አገራቸው በመውጣት ጅቡቲን መኖሪያቸው ሲያደርጉ የጋራ ባህላቸውን ለማዳበር፣ የሚደርስባቸውን መገፋትና የመብት ጥሰት በጋራ ለመከላከል እንዲሁም የእናት አገራቸውን ልማት ለመደገፍ ከመሰረቷቸው አደረጃጀቶች መካከል አንዱ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ነው። ማህበሩ ከማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊና ከዘር ነፃ በሆነ መንገድ ከሀገሬው ህዝብና መንግስት ጋር በትብብርና በወዳጅነት ስሜት በመስራት የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ ለመገንባት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ማህበሩ ከምስረታው ጀምሮ አገራዊ የልማት ፕሮጀክቶችን በግንባር ቀደምትነት ከመደገፍ ባሻገር በህገወጥ የሰዎች ዝውውር የተነሳ ህይወታቸው አደጋ ላይ የሚወድቅ ዜጎችን በማስጠለል ሀላፊነቱን በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡

## የማህበሩ ተግባራት፤

⁘ በጅቡቲ በኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ማህበር በጅቡቲ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አማካኝነት በመጀመሪያ እንደ መረዳጃ ማህበር የተቋቋመ ሲሆን፣ በሂደት እራሱን እያሻሻለ ጠንካራ የኮሚኒቲ ማህበር ለመሆን ችሏል፡፡

⁘ ማህበሩ የራሱን ህንፃ ጥር 9 ቀን 1982 ዓ.ም ገንብቶ የገቢ አቅሙን ለማሳደግ የመዝናኛ ክበብ ከፍቷል፡፡ በመዝናኛ ክበቡም ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ የተለያዩ አገር ዜጎች የምግብና የመጠጥ አገልግሎት የሚያገኙ ሲሆን ይህም የአገራችንን ባህል ለማስተዋወቅ አብርክቶ እያደረገ ይገኛል፡፡ ማህበሩ በክበቡ ከምግብና ከመጠጥ አቅርቦት በተጨማሪ የአዳራሽና ተያያዥ አገልግሎቶች ለኢትዮጵያውያንና ለሌሎች አገር ዜጎች ጭምር እየሰጠ የሚኝ ሲሆን በስሩ ለ28 ቋሚ እና ለ5 ጊዜያዊ ሰራተኞች የስራ ዕድል ፈጥሯል፡፡

⁘ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በቦንድ ግዥ በስጦታ 148,610 የአሜሪካ ዶላር አበርክቷል፡፡

⁘ በጅቡቲ የሚገኙ መንግስታዊ መ/ቤቶች ለተለያዩ ስብሰባዎች አዳራሽ ሲጠይቁ በድጋፍ መልክ ክበቡን በነፃ እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡

⁘ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ማኅበር በጅቡቲ በአሁኑ ወቅት በዶላር 118,406.78 በብር 329,460.07 እና በቦንድ 148, 610 ዶላር ሃብት አለው፡፡

⁘ ከኤምባሲው ጋር በመተባበር በተለያዩ ማረሚያ ቤቶችና ፖሊስ ጣቢያዎች የሚገኙ ዜጎቻችን አስፈላጊ ቁሳቁስ በመያዝ ጉብኝት ያደርጋል፡፡

⁘ በተለያዩ ሆስፒታሎች በመገኘት ለዜጎች የህክምና ገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

⁘ በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር የተጋለጡ ዜጎች የምግብ፣ የመጠለያና ወደ ሀገር ቤት የሚገቡበት የትራንስፖርት ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

⁘ በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ት/ቤት በማህበረሰቡ ተሳትፎ እንዲገነባ ለጅቡቲ መንግሥት ጥያቄ ቀርቦ መሬት እንዲሰጥ አድርጓል፡፡ በቦታው ላይ ግንባታ እስኪጀመር ይዞታውን ለማስከበር የአጥር ማሳጠሪያ 6,797,105 የጅቡቲ ፍራንክ ወይም አንድ ሚሊዮን ብር ገደማ ወጭ አድርጓል፡፡

⁘ በቅርብ ዓመታት ለቀረቡ የድጋፍ ጥሪዎችም ከ42, 824 ዶላር በላይ ሀብት በማሰባሰብ ድጋፍ አድርጓል።







## 3. የፖርት ሱዳን የኢትዮ ጵያውያን ኮሚዩኒቲ ማኅበር

ኢትዮጵያ እና ሱዳን ከአባይ ሸለቆ (Nile Basin) ጥንታዊ ስልጣኔ መንግስታት ዘመን ጀምሮ በንግድ፣ በባህል፣ በሕዝብ ለሕዝብ የጉርብትና ግንኙነት ጠንካራ ትስስር ያላቸው አገሮች ሲሆኑ፣ በሁለቱ አገሮች መካከል ኦፊሴላዊ የዲፕሎማሲ ግንኙነት የተመሰረተው እ.ኤ.አ. በ1956 ዓ/ም ሱዳን ከአንግሎ እጂብሺያን ቅኝ ግዛት ነፃ ከወጣች በኋላ ነው።

በአገረ ሱዳን ከአንድ መቶ የሚበልጡ ልዩ ልዩ የኢትዮጵያውያን አደረጃጀቶችና ማህበራት ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል የአጥባራ ኮሙዩኒቲ፣ በካርቱም የሰላም መረዳጃ ማህበር፣ ባህሪ መዲና ኮሙዩኒቲ፣ ኡንዱርማን ኮሙዩኒቲ፣ በሱዳን የአማራ ልማት ማህበር፣ በሱዳን የኦሮሞ ልማት ማህበር፣ የወልቃይት ጠገዴ ሰሜን አርማጠሆ እድር በሱዳን፣ የጀምአተ ዳዋ ሙስሊሞች ማህበር በሱዳን፣ የመድህኔ አለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ በሱዳን እንዲሁም በሱዳን የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች ህብረት ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ አደረጃጀቶችና ማህበራት በተለያዩ የአድቮኬሲና የልማት ስራዎች የነቃ እንቅስቃሴ እያደረጉ ከሚገኙት መካከል አንዱ የፖርት ሱዳን የኢትዮጵያውያን ኮሚዩኒቲ ማኅበር ነው።

የፖርት ሱዳን የኢትዮጵያውያን ኮሚዩኒቲ ማኅበር የተመሰረተው በሱዳን የቀይ ባህር ግዛት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን መብትና ጥቅም ለማስከበር እና የኢትዮጵያን ባህልና ቋንቋዎች ለኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ልጆች እንዲሁም በግዛቱ ለሚኖሩ ሱዳናውያንና ሌሎች ማኅበረሰቦች ለማስተዋወቅ ዓላማ አንግቦ ነዉ። ኮሚዩኒቲው በግዛቱ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንንና ትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ሱዳናውያንን በማካተት ከ21 ዓመታት በፊት የተመሰረተና በአሁኑ ጊዜ 450 የተመዘገቡ ቋሚ አባላት ያሉት እና በርካታ ስራዎችን በማከናወን ላይ ያለ ኮሙዩኒቲ ነው።

## የፖርት ሱዳን ኢትዮጵያውያን ኮሚዩኒቲ ሊቀመንበር መልዕክት፤



የፖርት ሱዳን የኢትዮጵያውያን ኮሚዩኒቲ ከተመሰረተ ከ21 ዓመታት በላይ የሆነው ሲሆን፣ በሚያከናውናቸው በግባራት ከአገር አልፎ በአካባቢው ለሚኖሩ ሌሎች የአፍሪካ አገራት ኮሚዩኒቲዎችም የአፍሪካዊ አንድነት ስሜት መፍጠር ችሏል።

ኮሚዩኒቲያችን በአካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን መብት እንዲከበር እና ጥቅማቸውም እንዳይቀማ ከቀይባህር ግዛት መሪዎች ጋር ተቀራርቦ እየሠራ በመሆኑ ችግሮችን በፍጥነት የመፍታት ልምድ እያዳበረ ይገኛል። በሌላ በኩል ከሱዳናውያን ጋር በወንድማማች ስሜት የሚያኖሩ ሁኔታዎችም እንዲመቻቹ እያደረገ ነው።

አገራዊ ጉዳዮች ለሆኑት ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ፣ ለገበታ ለአገር ፕሮጀክቶች፣ በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ወገኖችን ለማቋቋም ባለፉት 2 ዓመታት ከ 4 ሚሊዮን የሱዳን ፓውንድ እና ከ2,200 የአሜሪካ ዶላር በላይ ገንዘብ በማዋጣት ድጋፍ አድርጓል።

ለአገራችን ሰላምን፣ አንድነትን እና ዕድገትን እየተመኘሁ የፖርት ሱዳን ኢትዮጵያዉያን ሁሌም ከኢትዮጵያ ጎን ተሰልፈን አስፈላጊውን ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን አረጋግጣለሁ።

አምላክ ኢትዮጵያን ይባርክ፣ አመሰግናለሁ!!

ሰሚር አልሀጅ አልአወት

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

ኮሚዩኒቲው በአገረ ሱዳን ከሚገኙ የኤርትራ፣ የናይጄሪያ፣ የደቡብ ሱዳን እና የቻድ ኮሚዩኒቲዎች ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር በአገራችን ባህላዊ እና ሐይማኖታዊ ኩኔቶች አከባበር የኢትዮጵያን በጎ ገጽታን ከማስተዋወቅም በላይ አፍሪካዊ ወንድማማችነትን በማንገብ በሚፈጥረው የአንድነት ስሜት ለሌሎቹ ኮሚዩኒቲዎች እንደ አርአያ የሚታይ ነዉ።

በ2014 ዓ/ም በጀት ዓመት የጥምቀት በዓል መልካም አጋጣምን በመጠቀም የፈጠረው አፍሪካዊ ወንድማማችነት ስሜት እና በአከባቢው ለሚኖሩ 150 በጣም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው እና የዕድሜ ባለፀጋ ኢትዮጵያውያን ከሱዳን የቀይ ጨረቃ ማኀበር በነፃ መታከሚያ መታወቂያ (ካርድ) እንዲያገኙ ያስቻለና በተመሳሳይ መልኩ ለወንድም የኤርትራና ደቡብ ሱዳን ኮሚዩኒቲዎች አባላትም ጠይቆ ማስገኘት የቻለ አፍሪካዊ ወንድማማችነት በተግባር ያሳየ ማህበር ነው።

በኢትዮጵያ ላይ የተከፈተውን ጦርነት ተከትሎ ማህበሩ በአገራዊ ጉዳዮች አባላቱን አስተባብሮ በማሳተፍ ለወቅታዊ ሀገራዊ ጥሪዎች እና ለተፈናቃዮች ማቋቋሚያ በሁለት ዙር በድምሩ 3 ሚሊዮን የሱዳን ፓዉንድ ድጋፍ ያደረገ ሲሆን፣ ለታላቁ የሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ፋይናንስም ባለፈዉ ዓመት የ2 ሺህ ዶላር ቦንድ ግዥ እንዲፈጸም አድርጓል።

የዜጎችንና አባሎቹን መብትና ጥቅም ከማስከበር አኳያም በተለያየ ምክንያት የሚታሠሩ ዜጎችን በዋስትና በማስፈታት፣ የሞት ፍርድ የተወሰነባቸው ኢትዮጵያውያንን ጉዳይ በመከታተል ውሳኔው ወደ ደም ካሳ እንዲቀየር በማድረግ ካሳ አስተባብሮ በማስከፈል ነፃ እንዲወጡ በማድረግ፣ ገንዘባቸውን ዘራፊዎች ለቀሟቸዉ ሦስት ኢትዮጵያውያን ከፖሊስ ጋር በመተባበር 100 ሺህ የሱዳን ፓዉንድ እንዲመለስላቸዉ በማድረግ፣ እንዲሁም በካርቱም ስቴት እና አጎራባች አካባቢዎች ሕጋዊ መኖሪያ ፈቃድ የሌላቸው ዜጎቻችን በአፈሳ እየተያዙ እስከ 250 ሺህ የሱዳን ፓዉንድ እየተቀጡ ያለበትን ሁኔታ ኮሚዩኒቲዉ ከአካባቢዉ አስተዳደር ጋር በመነጋገር በ25ሺህ ፓዉንድ ብቻ በየ6 ወሩ የሚታደስ የመኖሪያ ፈቃድ የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት ዜጎቻችንና አባላቶቻቸው ከአፈሳ፣ አላስፈላጊ ወጪ እና እንግልት መታደግ ችሏል።

በአድቮኬሲ ረገድ የኢትዮጵያን እና የሱዳንን ሕዝቦች ወዳጅነት ለማጠናከር ክቡር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የሱዳንን ፖለቲካ ከገባበት አጣብቂኝ ለማውጣት ያደረጉትን ጥረትና ያበረከቱትን አስተዋፅኦ በማስታወስ እንዲሁም የሁለቱን አገራት ሕዝቦች ጉርብትና፣ የታሪክ እና የጋብቻ ትስስር አጉልቶ በማሳየት የግዛቱ አመራር አባላትና የከተማዉ ሕዝብ ስለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት እንዲኖራቸዉ በመስራት ላይ ይገኛል።

## 4. በደቡብ አፍሪካ የተባበሩት የኢትዮጵያ ማህበረሰብ (United Ethiopian Community Association in South Africa-UECASA)

በኢትዮጵያና በደቡብ አፍሪካ መካከል ያለው የሁለትዮሽ ግንኙነት 27 ዓመታት ገደማ ያስቆጠረ ሲሆን የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥ በፖለቲካው መስክ ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትከተለው የቆየችውና በአ.አ.ድ፣ በተ.መ.ድና በመሳሰሉት መድረኮች ያራመደችው ጠንካራና የማያወላውል የጸረ-አፓርታይድና የጸረ-ቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ፣ እንዲሁም ለትግሉ ያበረከተችው ተጨባጭ ድጋፍ ሀገሪቱ ዛሬ ላይ ከመላ የአፍሪካ አገራት ጋር ላላት ግንኙነት የማዕዘን ድንጋይ ነበር ማለት ይቻላል። ኢትዮጵያ ለተለያዩ የደቡብ አፍሪካ የነጻነት ታጋይ ድርጅቶች በተለይም ለኤ.ኤን.ሲ ፓርቲ የገንዘብ፣ የማቴሪያል፣ የወታደራዊ ስልጠና፣ የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲና የስነ-ልቦና /የሞራል/ ድጋፍ መስጠቷ ደቡብ አፍሪካ ከአስከፊው የአፓርታይድ ሥርዓት ተላቃ ከዓለም-አቀፉ ማህበረሰብ ጋር ስትቀላቀል ከአገራችን ጋር ለመሠረተችው መልካም ወዳጅነት የድርሻውን ተወጥቷል ማለት ይቻላል፡፡ በአገሪቱ የመጀመሪያው ዙር ዴሞክራሲያዊ አገር አቀፍ ምርጫ እ.ኤ.አ በኤፕሪል ወር 1994 ተካሂዶ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ከተፈጠረ ወዲህ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተው የሁለቱ አገራት ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ መጥቶ ከጁን ወር 1994 ጀምሮ በፕሪቶሪያ ተወካይ ጽ/ቤት በመክፈት ከደቡብ አፍሪካ ጋር ሙሉ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት መመስረት ተችሏል።

ዛሬ ላይ ዜጎቻችን በብዛት ከሚሰደዱባቸው አገራት መካከል በዋናነት የምትጠቀስ ደቡብ አፍሪካ ስትሆን፣ በዚች አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሁለት አይነት ባህሪያት ያላቸው ማህበረሰብ ናቸው፡፡ በአንደኛ ደረጃ አውሮፓና አሜሪካ ለመድረስ ደቡብ አፍሪካን እንደመተላለፊያ አድርገው የሚጠቀሙ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደቡብ አፍሪካን መዳረሻ ያደረጉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ደቡብ አፍሪካ ለበርካታ ኢትዮጵያውያን ዋናኛ መዳረሻ አገር ናት ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ ዜጎች ቁጥር በውል በይታወቅም በአገሪቱ በአጠቃላይ ከ200-300 ሺህ ኢትዮጵያዊን እንደሚኖሩ ይገመታል፡፡

በውጭ የሚኖሩ ዜጎች በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከታቸው ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግባቸው በትውልድ አገራቸው አጠቃላይ ጉዳይ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ለራሳቸው ተጠቅመው ትውልድ አገራቸውንም እንዲጠቅሙ በማድረግ ረገድ በጎ እርምጃዎች እየታዩ ሲሆን፣ በውጭ የሚኖረው ማህበረሰብ በባለቤትነትና በአገር ፍቅር ስሜት በአደረጀጀቱና በግለሰብ ደረጃ ምላሹን እየሰጠ ይገኛል።

በደቡብ አፍሪካና ሚሲዮኑ በተወከለባቸው አገሮች 18 የሚሆኑ በኮሙኒቲ፣ በምሁራን፣ በአከባቢ ልማትና በመረዳጃ ማህበራት አንዲሁም በሃይማኖት ተቋማት ተሰባስበውና ተደራጅተው መብታቸውን ሲያስከብሩ፣ ጥቅማቸውን ሲያስጠብቁና ለአገራቸው ልማትና እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህም መካከል በደቡብ አፍሪካ የዳያስፖራ ማህበራዊ ሚዲያ ተቋማት ቡድን፣ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ በደቡብ አፍሪካ፣ የደቡባዊ አፍሪካ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን፣ የደቡባዊ አፍሪካ የኢትዮጵያ ዲጂታል ዲፕሎማሲ ቡድን፣ የደቡባዊ አፍሪካ የኢትዮጵያውያን ምሁራን ማህበር፣ በሌሴቶ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ማህበር፣ በእስዋቲኒ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ማህበር፣ በናሚቢያ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ማህበር እንዲሁም በቦትስዋና የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ማህበር ተጠቃሾች ናቸው።

ከነዚህ አደረጃጀቶች መካከል የተባበሩት የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ማህበር በደቡብ አፍሪካ (United Ethiopian Community Association in South Africa-UECASA) ባበረከተው የላቀ አስተዋጽኦ ተጠቃሽ ነው፡፡

## በደቡብ አፍሪካ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር ሊቀመንበር መልዕክት፤



በደቡብ አፍሪካ ሰፊ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ እንደሚገኝ ይታወቃል። ይህ ማህበረሰብ በተለያዩ አካባቢዎች በጋራ ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በመደራጀት በትብብር እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በመላው ደቡብ አፍሪካ የሚገኙ የተለያዩ የማህረሰባችን አደረጃጀቶችን ከፖለቲካ፣ ከኃይማኖት፣ ከብሔር፣ ከወገንተኝነት ነጻና ገለልተኛ በመሆን ሁሉንም ዜጎች በአንድነት የሚያቅፍ ጠንካራ አደረጃጀትት በመመስረት መንቀሳቀስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ “የተባበሩት  የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር በደቡብ አፍሪካ” የተሰኘ ማህበር እ.ኤ.አ. ጁን 3 ቀን 2019 ከደቡብ አፍሪካ መንግስት ህጋዊ እውቅና አግኝቶና ተቋቁሞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

ማህበሩ በደቡብ አፍሪካ በዘጠኙም ፕሮቪንሶች (ክልሎች) የሚገኙ ሁሉንም የማህበረሰባችን አደረጃጀቶች በአባልነት በማቀፍ የተጠናከረ የኢትዮጵያውያን የአንድነት ተቋም ነው።

የማህበሩ ዋነኛ ተልዕኮ በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ ዜጎቻችን ክብራቸው፣ መብታቸውና ጥቅማቸው እንዲከብርና እንዲጠበቅ እንዲሁም የደቡብ አፍሪካ እና የአገራችን ህዝቦች ታሪካዊና ወንድማማችነት መስተጋብር እንዲሳለጥ በማድረግ የህዝብ ለህዝብ ትስስሩን ይበልጥ ለማጠናከር ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በቅርበትና በትብብር መንቀሳቀስ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ዜጎቻችን በጋራ አገራዊ ጉዳዮች በዋናነት በሰላም ጉዳዮች፣ በአገር ግንባታ እና በገጽታ ግንባታ ዙሪያ ወቅታዊ መረጃዎችን በማጋራት ከአገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር በማጠናከር የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ማህበሩ በአገራዊ ዋና ዋና ጉዳዮች ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓ እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች ከሚገኙ አቻ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር እየተንቀሳቀሰ የራሱን አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

ማህበሩ ከምስረታው አንስቶ በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ መላው ኢትዮጵያውያንን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች በማስተባበርና ከሚመለከታቸው የአገሪቱ ተቋማት፣ አቻ ማህበራት፣ ሲቪል ማህበራት እንዲሁም በፕሪቶሪያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጋር በመተባባር በአገሪቱ የሚኖሩ ዜጎቻችን እያጋጠማቸው ያለውን ፈርጀ-ብዙ የኑሮና የሥራ ከባቢያዊ ችግሮች እንዲቀንሱ በመስራት ላይ ይገኛል። በአገሪቱ የሚኖሩ የውጭ አገራት ዜጎች እና ንብረቶቻቸው ላይ በማነጣጠር በሚፈጸሙ የመጤ ጠል ጥቃቶችና ዝርፊያዎች ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ድርጊቱን የማውገዝና እንዲቆሙ ማድረግ፣ ችግር ውስጥ ለሉ ዜጎች የተለያዩ ድጋፎችን መሰብሰብ፣ በገጽታ ግንባታ መሳተፍና በሌሎችም በርካታ አገራዊ ጉዳዮችና የልማት ተሳትፎ ማሳደግ ላይ ይንቀሳቀሳል።

በመጨረሻ የተባበሩት የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር በደቡብ አፍሪካ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ ተልዕኮውን ለማሳካት በርካታ እንቅስቃሴ ያደረገና እያደረገ የሚገኝ ሲሆን፣ በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ሁሉም ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያ እና የኢትዮጵያ ወዳጆች እንዲሁም በተልዕኮው ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ሌሎች አቻ ማህበራትና ህብረቶች ለማህበሩ ተልዕኮ ስኬት ላበረከቱት ያልተቆጠበ አስተዋጽኦ በማህበሩ እና በራሴ ስም የላቀ ምስጋና እያቀረብኩ ትብብራችሁ፣ ተሳትፏችሁ እና ድጋፋችሁን አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ ጥሪዬን ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!
አቶ ዮሐንስ ሀቢብ ከቾሌ

በደቡብ አፍሪካ የተባበሩት የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት፣ ከብሔር፣ ከወገንተኝነት ነጻና ገለልተኛ የሆነና ሁሉንም ዜጎች በአንድነት ያቀፈ፣ ጠንካራ የወገን ህብረትና አንድነት ለመፍጠርና የኢትዮጵያውያንን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የተመሠረተ ማህበር ነው፡፡

የማህበሩ ዋነኛ ተልዕኮም በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ ዜጎቻችን ላይ የሚደርሱ የመብት ጥሰቶችንና የደህንነት ስጋቶችን (የስብዕና አለመከበር፣ የንብረት መዘረፍ፣ የአካል መጉደል፣ የህይወት መጥፋት፣ የስነ-ልቦና መረበሽ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ማጣት/መጓደል፣ ከመኖሪያና ስራ ቦታ መፈናቀል፣ ወዘተ... ችግሮች) በህጋዊና ተቋማዊ በሆነ መንገድ መከላከል፣ በመብቶቻቸውና ጥቅሞቻቸው ዙሪያ ከሚመለከታቸው የደቡብ አፍሪካ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ተቀናጅቶና ተባብሮ መስራት ነው፡፡




## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

• በደቡብ አፍሪካ ጆሃንስበርግ ከተማ በተለያዩ የንግድ ስራዎች ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን "አስመስሎ የተመረቱ ዕቃዎችን ትሸጣላችሁ" በሚል በተወሰደው እርምጃ ምክንያት ተከስተው በነበሩ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ በርካታ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን የተገኙበት ህዝባዊ የንቅናቄ መድረክ በመጥራት በደቡብ አፍሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ፣ የቢዝነስ ኮሚኒቲ መፍትሄ አፈላላጊ ጊዜያዊ ኮሚቴ፣ የአገሪቱ ገዥ ፓርቲ- የአፍሪካ ብሄራዊ ኮንግረስ (ANC) እና የደቡብ አፍሪካ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ተወካዮች በተገኙበት ውይይት እንዲካሄድ አደርጓል፡፡

• " Counterfeit Goods " ለመዋጋት በሚል የተወሰዱት የሃይል ዕርምጃዎች ጥንቃቄና ግልጽነት የጎደላቸው፣ የሰዎችን ስብዕና የሚጋፉና እንዲሁም ብዙዎችን ለጉዳት የዳረጉ እንደሆነ በአገሪቱ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት የስራ ሃላፊዎች እንዲታወቅ በማስረዳት አስፈላጊው ድጋፍ እንዲደረግልን ጥያቄ የቀረበ ሲሆን፣ በቢዝነስ ኮሚኒቲው እና በጸጥታ ሃይሉ መካከል የተፈጠረው ፍጥጫ ተጨማሪ ጉዳት እንዳያደርስ እንዲሁም የዜጎች መብትና ደህንነት እንዲከበር ጠንካራ የክትትል ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

• የደቡብ አፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደቡብ አፍሪካ ውስጥ በሚኖሩ የውጭ አገራት ዜጎች እና ንብረቶቻቸው ላይ በማነጣጠር ተፈጽሞ በነበረው ጥቃትና ዝርፊያ ዙሪያ በአገሪቱ ከሚኖሩ የውጭ አገራት ዜጎች አደረጃጀቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ባካሄደው ውይይት ላይ በመሳተፍ የዝርፊያውና የጥቃቱ አንዱና ዋነኛው መንስኤ በተለያዩ ጊዜያት በአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት እና የፖለቲካ ሰዎች የሚሰነዘሩ አመጽን የሚያነሳሱ ቃላቶች መሆናቸውና ከስተቱም ኢትዮጵያውያን ለደቡብ አፍሪካ ኢኮኖሚ እያበረከቱ ካለው ጥቅም ጋር የሚጋጭ መሆኑን አስገንዝቧል፡፡

• ጁላይ 18, 2019 የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የማንዴላ ቀንን ምክንያት በማድረግ በጆሃንስበርግ የጽዳት ዘመቻዎችን አካሂዷል፣ ለተቸገሩ የደቡብ አፍሪካ ማህበረሰብ አባላትም ድጋፍ አድርጓል፡፡

• የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝን ተከትሎም በደቡብ አፍሪካ ከሚኖሩ ከኢትዮ-ሳውዝ አፍሪካ መልቲሚዲያ፣ ከዩናይትድ ሚዲያ ሐውስ፣ ከየኛ ሰው በደቡብ አፍሪካ ሚዲያዎች ጋር በመቀናጀት ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ተሰርቷል። ለተቸገሩና ለተጎዱ በደቡብ አፍሪካ ለሚኖሩ ወገኖችና ለሀገሩ ዜጎች ድጋፍ አድርጓል። በዚሁ መሠረት 701,000 ራንድ ድጋፍ በመሰብሰብ ከ600 በላይ ለሚሆኑ በደቡብ አፍሪካ ለሚኖሩ ተጎጂ ወገኖች እና ከ360 በላይ ለሆኑ ለሀገሩ ተወላጆች 651,000 ራንድ ወጪ በማድረግ ለያንዳንዳቸዉ በነፍስ ወከፍ የ660 ራንድ የምግብ ድጋፍ አበርክቷል፡፡



• በሀገር ውስጥ ለሚደረገው የኮቪድ-19 መከላከል ስራ እንዲውልም 50,000 ራንድ በማሰባሰብ በደቡብ አፍሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ገቢ አድርጓል።

• ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎችን እንዲሁም የአፍሪካ አገራትን ዜጎች በማሳተፍ የምዕራባውያን መንግስታትን ያልተገባ ጫና እና ጣልቃ-ገብነት፣የሀሰት ዘመቻ እና ገጽታን ማጠልሸት የሚቃወም በግጭት ምክንያት ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ እና አጋርነትን የሚያሳይ ታላቅ ህዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ ኖቬምበር 29/2021 በፕሪቶሪያ ከተማ አካሂዷል፡፡



• ዜጎች በሚያጋጥሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ ማህበሩ ከአፍሪካ ዳያስፖራ ፎረም፣ ከሌሎች ሲቪክ ማህበራት፣ ከህግ ባለሙያዎች፣ ከተጽዕኖ ፈጣሪ ደቡብ አፍሪካውያን፣ ከጸጥታ ተቋማት ከፍተኛ ሃላፊዎች ጋር ተከታታይ ውይይቶችን አካሂዷል፡፡



## በበሳዑዲ አረቢያ የላቀ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ያሉ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አደረጃጀቶች

ኢትዮጵያና ሳዑዲ አረቢያ ለረጅም ጊዜ የዘለቀ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትና ትስስር ያላቸው ሲሆን፣ ግንኙነቱ ኢትዮጵያ የመጀመሪዎቹን የእሥልምና እምነት ተከታዮች በስደት በመጡበት ወቅት ተቀብላ ማስተናገዷን ተከትሎ እየተጠናከረ መጥቷል። የሁለቱ አገራት የግንኙነት ታሪክ እስከ አክሱም ዘመነ መንግሥት የሚዘልቅ ቢሆንም ኦፊሳላዊ ዲፕሎማሲ ግንኙነት የተጀመረው እ.ኤ.አ በ1949 ነው። ሁለቱ አገራት ካላቸው የቆየ የህዝቦች ትስስርና ከጂኦግራፍያዊ ቅርበት የተነሳ ከ800,000 በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን በሳዑዲ ዓረቢያ በተለያዩ ስራዎች ተሰማርተው እንደሚኖሩ ይገመታል፡፡

እ.ኤ.አ. 1985 መቀመጫው ጂዳ የነበረው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወደ ሪያድ ኢንዲዛወር በሳዑዲ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መገለጹን ተከትሎ ኤምባሲውን በሪያድ ለማቋቋም የህብረተሰቡ አስተዋጾ በማስፈለጉ ዳስፖራውን ለማስተባበርና ለማሳተፍ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር እንዲመሰረት በወቅቱ የነበሩ የዳያስፖራ ተወካዮች ጥንስሱ ተጀመረ። በዚህ ሁኔታ ጀምሮ ለምስረታ የበቃው በሪያድ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በርካታ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል።

## 5. በሪያድ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር



በሪያድ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ የማህበር ሊቀመንበር መልዕክት፤

በሳዑዲ አረቢያ ሪያድ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ ያለው ታሪክ በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው በመካከለኛው ምስራቅ ተጠቃሽና ጠንካራ ከሚባሉት የኮሚኒቲ ማህበራት አንዱ ነው፡፡

በሪያድ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ግንባታና ማቋቋም ስራዎች፣ በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ዓለም አቀፍ ት/ቤት ምስረታ፣ በልማት ማህበራት ድጋፍና ዕገዛ ፣ የኤምብሲውን የአገልግሎት ስራዎች ለመደገፍ በሚያስፈልግ የሰው ኃይል (ሠራተኛ) አቅርቦት፣ መጠጊያ የሌላቸውን ሴቶችን ተቀብሎ በማስጠለልና በመደገፍ፣ ወደ አገር የሚመለሱ ዜጎችን በተመለከቱ ስራዎች በመሳተፍና ኤምባሲውን በመደገፍ፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጅክትን ጨምሮ በተለያየ ጊዜ ለሚቀርቡ አገራዊ፣ የሰብአዊና ልማት ድጋፍ ጥሪዎች አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ በመስጠት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ሲወጣ ቆይቷል፤ ለወደፊቱም ይኸንኑ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

ላለፉት ሁለት ዓመታት ከማህበሩ ቁጥጥር ውጭ በሆኑ ውጫዊ ምክንያቶች በተለይ ደግሞ ሕጋዊ የጉዞና የመኖሪያ ፈቃድ በሌላቸው ሰዎች ላይ እየተደረገ ባለው ጠንከር ያለ ቁጥጥር ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ ክስተቶችና ነባራዊ ሁኔታዎች ለኮሚኒቲ ስራ እንቅስቀሴ የማይመቹ እና በኮሚኒቲው እንቅስቀሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳረፉ ቢሆንም እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን በመቋቋም ተጠናክሮ ለመቀጠል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ኮሚኒቲው እንዲጠናከርና የተቋቋመለትን ዓላማ እንዲያሳካ ኤምባሲያችን የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል ገንቢና ይበል የሚያሰኝ በመሆኑ ይኸንን ድጋፍና ክትትል አጠናክሮ በመቀጠል እና እየታዩ ያሉ ተግዳሮቶች እንዲቀረፉ በጋራ በመስራት ዜጎቻችንና አገራችንን በተሻለና በተጠናከረ መንገድ ማገልገል እንደምንችል አንጠራጠርም፡፡

በመጨረሻም መንግስት የአገራችንን ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልጽግና ለማረጋገጥ እያደረገ ያለውን ፈርጀ ብዙ እንቅስቀሴ በትኩረት የምንከታተለውና ለተግባራዊነቱ የተቻለንን ሁሉ ድጋፍ በማድረግ ምንጊዜም ከአገራችን ጎን የምንቆም መሆናችንን እያረጋገጥኩ፤ ያለ ሕጋዊ የጉዞ ሰነድ ለሕይወት እጅግ አስጊ በሆነ መንገድ ወደ ሳዑዲ አረቢያ የሚደረገው የስደት ጉዞ በዜጎቻችንና በአገራችን ላይ ፈርጀ ብዙ አሉታዊ ውጤቶችን እያስከተለ የሚገኝ በመሆኑ መንግስት እያደረገ ያለውን ጥረት የተለየ ትኩረት በመስጠትና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበርና በማሳተፍ ዘለቄታ ያለው መፍትሄ እንዲበጅለት ማሳሰብ እንወዳለን፡፡

አብዱል አዚዝ መሀመድ

በሳዑዲ ዓረቢ ሪያድ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ሊቀመንበር

ኢትዮጵያንና ሕዝቧቿን ፈጣሪ ይባርክ !

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

❖ በሪድ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ታሪክ ሲነሳ በሪያድ የሚገኘው የሚሲዮኑ ጽ/ቤት እና የአምባሳደር መኖሪያ ቤት ህንጻ ግንባታ አስተዋጽኦው ከፍተኛና ጉልህ ቦታ የሚይዝ የታሪኩ ክፍል ሆኖ በግንባር ቀደምትነት ይወሳል፡፡

❖ የሳዑዲ አረቢያ መንግስት የተለያዩ ሃገራት ኤምባሲዎቻቸውን በአንድ አካባቢ እንዲገነቡ ውሳኔ ባስተላለፈበት ወቅት ኮሚኒቲው በመላው የገልፍ አገራት የሚገኙ ኢትጵያውያንን በማስተባበር 18,000,000 (አስራ ስምንት ሚሊዮን) የሳዑዲ ሪያል በማሰባሰብ በአሁኑ ሰዓት ኤምባሲው እየተጠቀመበት የሚገኘውን ማራኪና ደረጃውን የጠበቀ ሕንጻ ግንባታ በማካሄድ የዜግነት ሚናና የአንበሳውን ድርሻ በመወጣት ደማቅ አገራዊ አሻራውን አኑሯል፡፡

❖ የሳዑዲ ትምህርት ሚኒስቴር የውጭ አገር ዜጎች በራሳቸው ስርዓተ ትምህርት ትምህርት ቤት ከፍተው ዜጎቻቸዉን እንዲያስተምሩ ፈቃድ በሰጠ ወቅት የኢትዮጵያ ዳስፖራ አባላትም ዕድሉን ተጠቅመው አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት እ.ኤ.አ. በ 1994 ዓ/ም በሪያድ የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤትን መስርተው በሳዑዲ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተመጣጣኝ ክፍያ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

❖ ኮሚኒቲው ከሚያከናውናቸው ተግባራት ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዘውና ተጠቃሽ የሆነው ከኢፌዴሪ ኤምባሲያ ጋር በመተባበር ለዜጎቻችን እየሰጠ ያለው የሴቶች ጊዜያዊ መጠለያ ማዕከል አገልግሎት ነው። ሴት እህቶቻችን ከሴትነታቸው ጋር ተያያዥነትን ባላቸውና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ጨምሮ የሳዑዲን ምድር ሳይረግጡ ገና በጉዞ ላይ ሳሉ ጀምሮ ለጤናቸውና ለህይወታቸው ጠንቅ የሆኑ የስነ ልቦናና አካላዊ ጉዳቶች ያጋጥሟቸዋል። ለእንግልትና ህመም በመዳረግ መግቢያ መጠለያ አጥተው በጎዳና ላይ ይወድቃሉ፡፡ የኮሚኒቲው ጊዚያዊ የሴቶች የመጠለያ ማዕከል እንደነዚህ ዓይነት ከአቅም በላይና የከፋ ችግር አጋጥሟቸው የሚያስጠጋቸው የሚያስጠልላቸው ቤተሰብ ዘመድ አጥተው የሚቸገሩ ሴቶችን ተቀብሎ በማስጠለል እንዲሁም ከኤምባሲው ጋር በመተባበር ጉዳዮቻቸውን ለሚመለከተው አካል በማቅረብ የብዙዎችን እምባ ሲያብስ ቆይቷል፤ አሁንም አቅሙ የፈቀደውን ድጋፍና አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

❖ ማህበሩ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ ከኤምባሲው ጋር በመተባበር በኤምባሲው አካባቢ የሚታየውን የስራ ጫና ለማቃለልና ኤምባሲው የሚሰጠውን አገልግሎት ለመደገፍ አቅሙ በፈቀደ መጠን አገልግሎት ሰጪ ሠራተኞችን በማቅረብ ጭምር ለዜጎች የሚሰጡ አገልግሎቶች ፈጣን፣ ተደራሽና ቀልጣፋ እንዲሆኑ ድጋፎችን ሲያደርግ ቆይቷል፤ በማድረግም ላይ ይገኛል፡፡ ያለ ሕጋዊ የጉዞ ሰነድ ድንበር አቋርጠው ወደ ሳዑዲ አረቢያ ገብተው በየጊዜው በአገሪቱ የሕግ አስከባሪ አካላት ተይዘው በተለያዩ የመጠለያ ጣቢያዎች (እስር ቤቶች) የሚገኙ ዜጎችን ወደ አገራቸው ለመመለስ በሚከናወኑ ስራዎች ከኤምባሲው ጎን በመቆምና አባላቱን በማሳተፍ በጉዞ ሰነድ ዝግጅትና መሰል ስራዎች በመሳተፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቷል፤ አሁንም እያደረገ ይገኛል፡፡

❖ በሪያድ የሚገኘው የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማህበረሰብ ከልማት ማህበራት ጋር በመተባበር በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች መጠነ ሰፊ የልማት ስራዎችን ሲደግፍ ቆይቷል። ከነዚህም መካከል በጤና እና ትምህርት ተቋማት ግንባታ፣ በመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክቶች ግንባታና በመሳሰሉት የተደረጉ ተሳትፎዎች ይገኙበታል።

❖ ሌላውና በሪያድ የሚገኘው የኢትጵያ ኮሚኒቲ አባላት አስተዋጾ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ እየተደረገ ያለው ተሳትፎ ነው። የህዳሴው ግድብ ስራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በሪያድ የሚገኘው የኢትጵያ ማህበረሰብ በጉልህ ሊታይ የሚችል ተሳትፎ በማድረግ የግድቡ ፕሮጀክት አሁን ለደረሰበት ደረጃ የበኩሉን አገራዊ አስተዋጽኦ በማደረግ በዚህ ታላቅ አገራዊ ፕሮጀክት ደማቅ አሻራውን አሳርፏል።

## 6. በጂዳና አከባቢዋ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ

በጂዳና አከባቢዋ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ በወቅቱ በነበሩ አንጋፋና አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በ1989 ዓ.ም የተመሰረተበት ሲሆን፣ ዋናው ዓላማውም በሳዑዲ አረቢያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን በአንድ ጥላ ስር በማሰባሰብ በዜጎች መካከል የመረዳደትና የመተሳሰብ መንፈስ እንዲዳብር በማድረግ የተሻለ ህይወት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡

### የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

- በጂዳና አከባቢው በሚኖሩ ዜጎችን ላይ የምደርሱ የሙብት ጥሰት እና የሚያጋጥሟቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቅረፍ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

- በሪያድ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ህንጻ ግንባታ ወቅት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

- ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ገቢ ማሰባሰብ ስራዎችን በማከናወን የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የ69,950 የአሜሪካን ዶላር ወይም 262,312 የሳዑዲ ሪያል በቦንድ ግዥና በስጦታ መልክ አበርክቷል፡፡

- ሌሎች ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበርም ግድቡን ለመደገፍ በሎተሪ እጣ የሚሸጥ አንድ የቤት መኪና ወደ አገር ቤት በመላክ የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

- በተለያዩ ምክንያቶች ለማህበራዊ ችግሮችና ለሙብት ጥሰት የተዳረጉ እና ጉዳያቸው በተለያዩ የሀገሪቱ የፍትህ ተቋማት የተያዘ እና በቀጠሮ ላይ ያሉ ዜጎች ጉዳያቸው መፍትሔ እስኪያገኝ በጊዜያዊነት የሚያርፉበት መጠላያ በሰባ ሺህ የሳዑዲ ሪያል በመገንባት እና በየዕለቱ ምግብ፣ መድሃኒት እና የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ ማቅረብ ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

- የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተከስቶ በነበረበት ወቅት ህብረተሰቡን በማስተባበር የተገኙ የምግብ፣ የመድሃኒት፣ አልባሳት እና የተለያዩ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ቤት ለቤት በመሄድ ለተቸገሩ ዜጎች ተደራሽ አድርጓል፡፡

- ሹሜሲ በተባለ የእስረኞች ማቆያ ማዕከል የሚገኙ ዜጎችን ወደ አገር ቤት የመመለሱ ሂደት እስኪጀመር ድረስ በየዕለቱ ምግብ፣ መድሃኒት፣ ለህጻናት ወተት እንዲሁም ለሴት እህቶቻችን የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስን ያጠቃላለ ድጋፍ በማሰባሰብ እስከ አራት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር የሚገመት ድጋፍ አድርጓል፡፡

- ቆንስላ ፅ/ቤቱ በማቆያ ማዕከሉ የሚያካሂደውን ዜጎች የመመዝገብና የጉዞ ሰነድ አዘጋጅቶ ወደ አገራቸው የመመለስ ስራ ለማቀላጠፍ እና ለማገዝ ኮሚዩኒቲው ሁለት ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች ገዝቶ በስጦታ መልክ ድጋፍ ያደረገ ሲሆን፣ በቅርቡ ዜጎቻችንን ወደ አገራቸው የማስመለስ ሂደት ለማገዝ ሃምሳ ሺህ የሳዑዲ ሪያል ድጋፍ አድርጓል፡፡

- ከሶማሌ ክልል የተፈናቀሉ ዜጎችን ለመደገፍ አንድ ሚሊየን የኢዮጵያ ብር፣ ለአገራዊ ጥሪዎች በተለይም ለመከላከያ ሰራዊት እና በጎርፍ ለተጎዱ ክልሎች በአጠቃላይ አንድ መቶ ሺህ የሳውዲ ሪያል እንዲሁም በቅርቡ መንግስት ላቀረበው ሀገራዊ የፋይናንስ ድጋፍ ጥሪ ሃምሳ ሺህ የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ አድርጓል።



## በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች የላቀ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ያሉ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አደረጃጀቶች

የኢትዮጵያና የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬቶች የሁለትዮሽ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከመሰረቱ አጭር ጊዜ ነው። የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱ የተጀመረው እ.ኤ.አ ከ1973 ዓ/ም ጀምሮ ሲሆን፣ ሁለቱም በዚህ ወቅት ውክልናቸውን በየመን ሰነዓ በሚገኙት ኤምባሲዎቻቸው አማካኝነት ሲሸፍኑ ቆይተዋል፡፡

በአገራቱ መካከል በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ የመንግስት ለመንግስትና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ለመመስረት የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል።

በሁለቱ አገራት መካከል ያለዉ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ግንኙነት እያደገ በመምጣቱ የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬቶች ኤምባሲዋን አዲስ አበባ ላይ በ2002 ዓ/ም እንድትከፍት፣ በሁለቱ ሃገራት ከፍተኛ ባለስልጣናት የተለያዩ ጉብኝቶች እንዲደረጉ እንዲሁም ኢትዮጵያ በ2006 ዓ.ም በአቡዳቢ ኤምባሲ እንድትከፍት አስችሏቸዋል፡፡

በኢኮኖሚ በተለይም በንግድ በሁለቱ ሃገሮች መካከል ያለው ግንኙነት እየተጠናከረ መጥቷል። በሁለቱ ሃገራት መካከል ያለው ትስስር ባለፉት አስር አመታት ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ አድጓል፡፡

በአሁኑ ወቅት በርካታ ኢትዮጵያውያን ለስራ ፍለጋ ወደ የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬቶች የሚሄዱ ሲሆን፣ ይህም በአገሪቱ ያለውን የዜጎቻችን ቁጥር እያሳደገ እንደሚሄድ ይገመታል። በአሁኑ ጊዜ ወደ 100,000 የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን ለስራ የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬቶች ውስጥ እንደሚገኙ ይገመታል፡፡

በመጋቢት 2014 አዲስ አባባ የሚገኘው የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬቶች ኤምባሲ ያሳተመው መፅሄት እንደሚያሳየው ከሆነ በተባበሩት ዓረብ ኤሚሬቶች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው የሚልኩት የገንዘብ መጠን (remittance) በየወሩ በአማካኝ 5,000,000 ዶላር ይደርሳል፡፡ ይህም ለኢትዮጵያ ወሳኝ የገቢ ምንጭ እንደሆነ ይገልፃል፡፡

አገራቱ በተለያዩ መስኮች ማለትም በከፍተኛ ትምህርት እና የሳይንሳዊ ምርምር ዘርፍ፣ በስፖርት ዘርፍ፣ በጉምሩክና በመሳሰሉት በትብብር እየሰሩ የሚገኙ ሲሆን በፍትሕ ትብብር፣ በአየር በረራ አገልግሎት፣ በሰራተኛ ልውውጥ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በደህንነትና በቆንስላ ጉዳዮች በጋራ ለመስራት ረቂቅ ስምምነቶች ላይ ድርድሮችና የሰነድ መለዋወጥ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

## 7. የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ማህበር በአቡዳቢ

የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ማህበር ከተቋቋመበት ከ2006 ዓ/ም ጀምሮ በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ በተለይም በአቡዳቢና አላይን ለሚገኙ በተለያዩ ደረጃ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በጽ/ቤቱ በኩል በርካታ አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል። ማህበሩ 50ሺ አባላት ያሉት ሲሆን፣ ከተቋቋመባቸው ዋና ዋና አላማዎች መካከል በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ በተለይም በአቡዳቢና አላይን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዜጎችን ማቀራረብ፣ የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ፣ ባህልና እሴቶችን ማስተዋወቅ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን መርዳት፣ ዜጎች በስደት አገር ላይ መብታቸውን እንዴት ማስከበር እንደሚችሉ ግንዛቤ መፍጠር እንዲሁም ለመብታቸው መታገል እንዳለባቸው ማስገንዘብና አስፈላጊውን የህግ ድጋፍ መስጠት የሚጠቀሱ ናቸው።

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

❖ ለዜጎች የሚደረጉ ማንኛውም የዜጋ ተኮር አገልግሎትን የማህበሩ ዋና አላማ በማድረግ ለዜጎች ፈጣን፣ ግልጽና አስተማማኝ አገልግሎቶችን ለመስጠት እና የተገልጋይን እርካታ ለማሳደግ እንዲያስችል ማህበሩ የኮሚኒቲ ጽ/ቤትን በሰው ሀይል በማደራጀት አስፈላጊውን አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።






❖ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉብኝትን ምክንያት በማድረግ በከፍተኛ ችግር ላይ የነበሩ ዜጎችን እና ህፃናትን ጨምሮ 135 ኢትዮጵያዊያን ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ ማህበሩ የሎጂስቲክ አቅርቦት እና አስፈላጊውን ድጋፍ አድርጓል። በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ 105 የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን እስረኞች እንዲፈቱ ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ መንግስት በኩል ጥያቄያቸው ተቀባይነት አግኝቶ ምህረት ተደርጎላቸው ከእስር ቤት በቀጥታ ወደ ሀገር ቤት እንዲሸኙ ማህበሩ ከኢትዮጵያ ኤምባሲ በአቡ ዳቢ ጋር በመሆን ከፍተኛ የማስተባበር ስራ በመስራት ስኬታማ እንዲሆን አድርጓል።




❖ በቅርቡ በዓለም ላይ በተከሰተው የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ወረርሽኝ ምክንያት በአቡዳቢ እና በአል አይን ለሚኖሩ በችግር ላይ ለወደቁ እና እራሳቸውን መመገብ ላልቻሉ 6000 ለሚጠጉ ዜጎቻችን ለ 3 ወር በተከታታይ የገንዘብ፣ የምግብ እና የንጽህና መጠበቂያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን ከኤምባሲው ጋር በመተባበር ባሉበት ቦታ በአካል በመሄድ አስፈላጊውን ድጋፍ አድርጓል።




❖ በተለያዩ ምክንያት መጠለያ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች መጠለያ በኤምባሲው ግቢ ውስጥ በማዘጋጀትና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ለተቸገሩ ዜጎች ከኤምባሲው ቅጥር ውጪ በመከራየት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። መጠለያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች የተመጣጠነ ምግብ እና አስፈላጊው ግብአት እንዲሟላላቸው በማድረግ አገልግሎቱን ተጠቃሚ ከሆኑት ዜጎቻችን ውስጥ ወደ 700 የሚጠጉ ችግር ያጋጠማቸው ዜጎቻችን በመጠለያ ውስጥ ሆነው ጉዳያቸውን ጨርሰው ወደ አገር ቤት እንዲሄዱ ወይም ወደ መደበኛ ስራ እንዲመለሱ ድጋፍ አድርጓል።




❖ በህመም እና በተለያየ ምክንያት አቅም ለሌላቸው ወደ 5000 ለሚጠጉ ዜጎችን ወደ አገር ቤት መሄጃ ትኬት በመቁረጥ እና አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም በተለያየ ምክንያት ከዚህ አለም በሞት የተለዩ 900 የዜጎች አስክሬንን ወደ አገር ቤት እንዲሸኙ አድርጓል።

❖ በተከታታይ በእስር ቤቶችና ሆስፒታሎች ጉብኝት እና ክትትል በማድረግ 1500 ለሚጠጉ ዜጎች አስፈላጊውን ድጋፍ አድርጔል።

❖ የህግ ድጋፍ የሚሹ የዜጎችን በመደገፍ ከ30,000 በላይ ዜጎች የምህረት አዋጅ ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ በአደጋ ምክንያት ህይወታቸውን ያጡ 600,000 ሺህ ድርሃም ኢንሹራንስ እንዲወሰንላቸው እና የአእምሮ ታማሚ ዜጎችም 214,000 ሺህ ድርሃም የፍርድ ቤት እዳ እንዲሰረዝላቸው አድርጓል።

❖ ኢትዮጵያውያን ከአሰሪዎቻቸው ጋር የሚገጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት በተደረገው ጥረት 16,000 ዜጎች ተጠቃሚ ሲሆኑ፣ በድምሩ ወደ 350,00 ድርሃም የሚጠጋ ገንዘብ እንዲያገኙ አድርጔል። እንዲሁም የመኖሪያ ፈቃድ ሳይኖራቸው በመዘዋወር የሚሰሩ ወደ 8,000 የሚሆኑ ዜጎችን ጉዳይ ከፖሊስ ጋር በመከታተል ወደ አገር ቤት በሰላም እንዲመለሱ አድርጓል።

❖ የኢትዮጲያውያን ወጣቶች ከአጉል ባህል፣ ከወንጀልና ከአልባሌ ሱስ ነጻ እንዲሆኑ፣ የምክር፣ የስልጠና ድጋፍና እርዳታ እንደየአስፈላጊነቱ በመስጠት ህብረተሰቡን ያገለግላል። አመታዊ የሆኑ የተለያዩ የስፖርት ውድድሮችን በማዘጋጀት ወጣቱ ተደራጅቶ እንዲሳተፍ ያደርጋል። የስፖርት ቡድኖችን ከማደራጀትና ከማሳተፍ አንጻር በተለይ በአቡ ዳቢ እና በአል አይን አካባቢ ያሉ ወደ 6 የሚጠጉ የእግር ኳስ ክለቦችን ሙሉ ትጥቅ እና ለስፖርቱ የሚያስፈልጉ ቁሳቆሶችን በመደገፍ ወጣቱ በሙሉ ንቃት በተለያዩ መድርኮች ላይ እንዲሳተፍ በቋሚነት ሁኔታ እየሰራ ይገኛል።









❖ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በጋራ ለማገናኘት በየአመቱ የሚከበሩ የተለያዩ የኢትዮጵያ በዓላት በአቡዳቢ እና በአል አይን በማክበር ዜጎች እንዲዝናኑ እና የአገራችንን ባህል፣ የቱሪስት መስህቦች እና የመሳሰሉትን መልካም ገጽታዎች እንዲተዋወቁ ያደርጋል። በተለይ የኢትዮጵያውያንን ቀን ለየት ባለ ሁኔታ በታላቅ ድምቀት በማክበር በመላው ኤምሬቶች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እንዲሳተፉበት ከማድረግ በተጨማሪ ታዋቂ ድምፃዊያን የሚገኙበት የሙዚቃ ኮንሰርት፣ የተለያዩ የባህል እሴቶችን የሚያሳይ አዝናኝ ዝግጅቶችና የፋሽን ሾው፣ የፍጻሜ የእግር ኳስ ውድድር እና መሰል አዝናኝ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል።









❖ ዜጎችን ከማገልገል በተጨማሪ የኢትዮጲያ መንግስት እና የኢትዮጲያ ህዝብ በሚያደርጉት የሀገር ጥሪ እና የሀገር ግንባታ ላይ በመሳተፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል። ከዚህም ጋር በተያያዘ የኮቪድ-19 ቫይረስ ወረርሽኝን ለመከላከል፣ ለህዳሴው ግድብ ግንባታ የቦንድ ግዢ፣ ለጀግናው የሀገር መከላከያ ሰራዊትና በጦርነቱ ምክንያት ለተፈናቀሉ ዜግቻችን መልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን በአጠቃላይ በድምሩ ወደ 40, 000, 000 ብር (አርባ ሚሊዮን ብር) በላይ ማህበሩ የገንዘብ እርዳታ ያደረገ ሲሆን፣ ወደ 150, 000, 000 ብር (መቶ ሀምሳ ሚሊዮን ብር) የሚገመት የተለያዩ የቁሳቁስ እና ለከፍተኛ ትምህርት መማሪያ የሚሆኑ መጽሃፍትን በማሰባሰብ፣ በማስተባበርና የሎጂስቲክ ወጪ በመሸፈን ወደ አገር ቤት ልኳል። ከዚህ በተጨማሪ በቅርቡ በ3ተኛው ዙር የህግ ማስከር ዘመቻ ላይ የተደረገውን ወቅታዊ አገራዊ ጥሪ በመቀበል 15,000,00 ብር (አስራ አምስት ሚሊዮን ብር) የሚጠጋ የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል። በኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ ለመሰማራትም አስፈላጊውን እቅድ አውጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።









## 8. በዱባይና ሰሜን ኤምሬቶች የኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ማህበር (Dubai)

በዱባይና ሰሜን ኤምሬቶች የኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ማህበር በመካከለኛው ምስራቅ አገራት ከሚገኙ የኢትዮጵያውያን ማህበራት ቀደም ብሎ የተመሰረተ ማህበር ነው።

የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማሕበር ሥራ አስፈፃሚዎች



አቶ ኢድሪስ ቡንሱር
ሊተማበር



አቶ አየሁ ዳምጤ
ም/ሊቀመንበር



አቶ ቃደሰ ፍሰሐ
የህዝብ ግንኙነት



አቶ መሐመድ ሀሰን
የፋይናንስ ኃላፊ



ኢንጅነር አብዱላሂ ጅሩ
ፀሐፊ



አቶ መኮንን ጌታቸው
ዜጎች ድጋፍና ክትትል

በዱባይ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ከተመሰረተ ሀያ ስድስት ዓመታት ያስቆጠረ ሲሆን ህግ እና መተዳደሪያ ደንብ ወጥቶለት በቆንስላ ጽ/ቤት ሥር በጽ/ቤት ደረጃ የተደራጀው በታህሳስ ወር 2005 ዓ/ም ነው፡፡ ከ2005 ዓ/ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የተመዘገቡ እና የአባልነት ክፍያ የከፈሉ ኢትዮጵያዉያን እና ትዉልደ ኢትዮጵያዉያን ቁጥር ወደ 86,000 ይሆናል። ማህበሩ በተባበሩት ዐረብ ኤምሬቶች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተለይም ደግሞ ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች የተጋለጡ ዜጎቻችን፣ የመብት ጥሰት የሚደርስባቸው፣ የሚታመሙ፣ የሞት አደጋ የሚያጋጥማቸውን ጉዳያቸውን የመከታተል፣ የመደገፍ እና ችግሮቻቸውን የመፍታት ተግባራትን የሚያከናውን ሲሆን፣ በተጨማሪም ከቆንስላ ጀነራል ጽ/ቤት ጋር በመሆን ዳያስፖራው በአገር ገፅታ ግንባታ፣ በኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖረው የማስተባበር ሥራዎችን ይሰራል። በተጨማሪም ሌሎች በሙያና በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍል የሚደራጁ የዳያስፖራ ማህበራትን የማደራጀትና የመደገፍ ሥራዎችን ያከናውናል።

ማህበሩ በዱባይ እና ሰሜን ኤምሬቶች ለሚኖሩ አባላትና ኢትዮጵያውያን ዜጎች መብትና ጥቅም የቆመ ማኅበር በመፍጠር በ2030 በአባላትና ዜጎች ላይ የሚደርሰው የሰብአዊ መብትና የፍትህ መጓደል፣ እንዲሁም ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተቀርፎ የማየት ራዕይ አንግቦ ይንቀሳቀሳል። ይንንም ለማሳካት አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በዱባይ እና ሰሜን ኤምሬቶች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዜጎች የሰብአዊ መብትና የፍትህ መጓደል፣ የህመም፣ የአደጋ/አካል ጉዳት ሲያግጥማቸው ወይም በሞት ሲለዩ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል። የተለያዩ የገቢ ማግኛ አማራጮች በመጠቀም የማኅበሩን አቅም በገንዘብና በቁሳቁስ በመገንባት እና የማህበሩ አባላት በቂ የሙያ ክህሎት እንዲያገኙ በማድረግ ላይ ይገኛል። ዜጐች የአገራቸው ኢትዮጵያን ባህልና ታሪክ እንዲያውቁ ሁኔታዎችን በማመቻቸት እንዲሁም በአባላትና በዜጎች መካከል ማህበራዊ ግንኙነቶች እንዲዳብሩ በመስራት በአገራቸው እየተካሄደ ባለው የሰላም፣ የአንድነት፣ የፍቅር፣ የመተሳሰብ፣ የመረዳዳትና የልማት እንቅስቃሴ በጋራም ሆነ በተናጠል ተሳታፊ እንዲሆኑ በመስራት ተልዕኮውን እየፈጸመ ይገኛል፡፡

ማህበሩ እንደ ዓላማ አድርጎ የተነሳው ከፖለቲካ፣ ከዘር፣ ከሃይማኖት፣ ከጎሳ እና ከፆታ አድልዎ ነጻ በሆነ ሁኔታ የማኅበሩ አባላትን በእኩልነት የሚያስተናግድና የሚያገለግል የሁሉም በዱባይ እና ሰሜን ኤምሬቶች ነዋሪ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ማገልገልና ማደራጀት ነው፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያውያንን በማኅበሩ ስር በማሰባሰብ መብታቸውንና ጥቅማቸው ስለሚከበርበት ሁኔታ እንዲወያዩ፣ እርስ በርስ እንዲደጋገፉ፣ ስለአገራቸው ሁኔታ ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙ፣ ማንነታቸውንና ባህላዊ እሴቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ እንዲሁም በአገራቸው በሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎች በየአቅማቸው ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሰራል።

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

•ኢትዮጵያውያን የቦንድ ግዢ እንዲፈፅሙና የአገራቸው ልማት ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ባለፉት ዓመታት ከዘጠኝ ሚሊዮን ዶላር በላይ እንዲሰበሰብ አጋርነቱን አሳይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ማኅበሩ በአጠቃላይ የ450 ሺ የአሜሪካ ዶላር የቦንድ ግዢ የፈፀመ ሲሆን፣ ለሎተሪ የሚውል ዘመናዊ ቶዮታ ራቭ4 አዲስ መኪና በስጦታ አቅርቧል፡፡

• በኤክስፖ 2020 ዱባይ ከኢትዮጵያ ፓቪሊዮን እና ከቆንስላ ጀኔራል ጽ/ቤቱ ጋር በመቀናጀት የአገራችንን ታሪክ፣ ባህል፣ የተለያዩ የቢዝነስና የኢንቨስትመንት ፎርሞች፣ የዓድዋ ድል በዓል፣ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን March 8 ቀን፣ የአልነጃሺ ቀን፣ ገልፉድ (Gulfood) ኤግዚብሺን እና ሌሎች የተለያዩ ኹነት ዝግጅቶች የተሳኩ እንዲሆኑ ኮሚኒቲ ማህበሩ እና ዳያስፖራው በገንዘብ፣ በዕውቀት እንዲሁም ውድ ጊዜን በመስጠት ርብርብ አድርጓል፡፡

• በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ለመከላከያ ሠራዊትና ለተፈናቀሉ ዜጎች የሚሆን 500,000.00 ድርሃም የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል፡፡

• የተጀመረውን ለውጥ ለመደገፍ እና ከኤርትራ ሕዝብ ጋር ለማቀራረብ የሚውል የ 99,000 (ዘጠና ዘጠኝ ሺ) ድርሃም ድጋፍ አድርጓል፡፡

• ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ ችግር ላይ ለወደቁ ዜጎች 368,000 ድርሀም በመመደብ በተጨማሪም ከበጐ ፈቃደኞች 25,880 ድርሃም በማሰባሰብ ከ7,000 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ዕርዳታ አድርጓል፡፡

• በተለያዩ ምክንያቶች ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን መልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን የ15, 000.00 ዶላር ድጋፍ አድርጓል፡፡

• በሰሜን ኢትዮጵያ በጦርነቱ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች በተባበሩት ዐረብ ኤምሬቶች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲና በዱባይና ሰሜን ኤምሬቶች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ቆንስላ ጀነራል ጽ/ቤትና በኮሚኒቲ ማህበር ትብብር ከኩፖን ሽያጭ 117,600.00 ድርሃም ድጋፍ በማሰባሰብ ገቢ አድርጓል፡፡





## 9. የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ማህበር በኳታር

ኢትዮጵያና ኳታር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የጀመሩት እ.ኤ.አ በ1995 ነው። ለረጅም ጊዜያት የዘለቀው የኢትዮ-ኳታር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እ.ኤ.አ ከ2006 ተቋርጦ የነበር ቢሆንም በ2012 ግንኙነቱ እንደገና ተሻሽሎ ሁለቱም አገራት ሚሲዮኖቻቸውን በአዲስ አበባ እና በዶሃ ከፍተው ግንኙነታቸውን ለማደስ ችለዋል። በአሁኑ ወቅት ሁለቱ አገራት በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ በትብብር እየሰሩ የሚገኙ በመሆኑ የሁለትዮሽ ግንኙነቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በፖለቲካው ዘርፍ የኳታርና የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቶች የሁለትዮሽ የፖለቲካ ምክክር ለማድረግ የሚያስችላቸው የመግባቢያ ሰነድ እ.ኤ.አ ኖቨምበር 2012 ተፈራርመዋል። በኢኮኖሚው ዘርፍም በኢኮኖሚና በቴክኒክ መስክ ለመተባበር የሚያስችል ስምምነት በ2012 ተፈርሟል። በተጨማሪም የሁለቱ አገራት ከፍተኛ ባለስልጣናት አንዱ የሌላውን በተለያየ ጊዜ ጎብኝዋል፡፡

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

❈ በኳታር የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በዶሃና አካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአንድነት በማሰባሰብ መብታቸውና ጥቅማቸው ለማስከበር፣ እርስ በርስ በመደጋገፍ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማግኘትና ስለአገራቸው ወቅታዊ ሁኔታ መረጃ ለመለዋወጥ እንዲያግዝ እ.ኤ.አ. በ1999 ተቋቋመ። ኮሚኒቲው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በሌለበት የሕዝቡ ወኪል ሆኖ ከ14 አመት በላይ ከማገልገሉም በላይ ዜጎች ማንነታቸውን፣ ባህላቸውንና እሴቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ እንዲሁም በአገራችን የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ በማድረግ ላይ ይገኛል።

❈ በተለይ ፓስፖርት እድሳትና የተለያዩ ዜጎቻችን የሚፈልጉትን አገልግሎት ኩዌት ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጋር በመተባበር ወገኖቻችንን ሲያገለግል ቆይቷል። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ በዶሃ በ2013 ከተከፈተ ባኋላም ከኤምባሲው ጋር በመቀናጀትና የበለጠ ራሱን በማደራጀት በኳታር ያሉ ወገኖቻችን በተለያዩ መስኮች ለሚገጥማቸው ችግሮች እገዛና እርዳታ በማድረግ ጥቅማቸውንና መብታቸውን ለማስጠበቅ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በማህበራዊው ዘርፍ ባህላዊና ስፖርታዊ ዝግጅቶችን የሚያዘጋጀ ሲሆን፣ ጠቃሚ አገራዊና አካባቢያዊ መረጃዎችም ያሰራጫል፡፡

• በኳታር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በመካከለኛው ምስራቅ የሚኖሩ እንደመሆናችን መጠን በአሜሪካ ወይም አውሮፓ ካሉ ይበልጥ ለተለያዩ ችግሮች፣ አደጋዎችና የሙብት ጥሰት ጉዳዮች የተጋለጡ ናቸው፡፡ በኳታር የኢትዮጵያ ኮሚኒቲም ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የዜጎች ክትትልና ድጋፍ ክፍልን እንደዋነኛ የኮሚኒቲው ክፍል አድርጎ በማቋቋም በሰውም ሆነ በቁሳቁስ አቅም በፈቀደ የተሟላ በማድረግ ለዜጎቻችን ክትትልና ድጋፍ እያደረገ ነው፡፡

• የዜጎች ክትትል ስራ በየዕለቱ የሚካሄድና ቅርብ ክትትል የሚያስፈልገው በመሆኑ በአመራሩ ብቻ





• ህዝቡ በባህል መስክ የማንነቱ መገለጫ የሆነውን ባህሉን እንዳይረሳ፣ እንዲዝናና እርስ በርስ መግባባትና አንዱ የሌላውን የባህል እሴት እንዲያውቅ የሚያደርግ የባህል ቡድን የተቋቋመ ሲሆን፣ ቡድኑ በዓመት በዓል፣ በህዝብና በመንግስት በዓላት ወቅት የተለያዩ ዝግጅቶችን ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም ከኢትዮጵያ የተለያዩ ዘመናዊና የባህል ሙዚቀኞችን በማስመጣት ህዝቡ ከአገሩ ጋር ያለው ትስስር እንዲጠናከር ይሰራል።



• በስፖርቱ መስክ በየአመቱ ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው የራሳቸውን ቡድን ወይም ክለብ እንዲያቋቁሙ በማድረግ ለሁለት ወራት የእግር ኳስ ውድድር ያካሂዳል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲን የሚወክሉ ስፖርተኞችን በመመልመል በኳታር የኔሽን ካፕ የእግር ኳስ ውድድር ላይ አገራችን ተወክላ እንድትጫወት በማድረግና በኳታር የስፖርት ቀን ላይ ዜጎቻችን በነቂስ ወጥተው እንዲሳተፉ እያደረገ ይገኛል፡፡




• የኮሚኒቲው የህዝብ ግንኙነት ክፍልም ሶሻል ሚዲያዎችን በመጠቀም ከኤምባሲው ሆነ ከሚመለከታቸው አካላት የሚገኙ መረጃዎችን ለህዝብ ያደርሳል፡፡

• ኮሚኒቲው በተለይ ከኤምባሲው ጋር በመተባበርና ዜጎች ድጋፍ በሚፈልጉበት ጊዜ እገዛ ለማድረግ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ከዚህም ጋር በተያያዘ እስካሁን ከዜጎች ለቀረቡ የመጠለያ አገልግሎት፣ የትኬትና የገንዘብ ድጋፍ እንዲሁም ከጤና፣ ከአሰሪና ሰራተኛ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ አድርጓል፡፡



## 10. የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ በኩዌት

የኢትዮጵያ እና የኩዌት ፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የተመሰረተው ኩዌት ሙሉ ነፃነቷን እ.ኤ.አ 1961 ባገኘች ማግስት የኢትዮጵያ መንግስት ለኩዌት መንግስት ዕውቅና ከሰጠበት እ.ኤ.አ በ1967 ጊዜ የጀመረና እ.ኤ.አ በ1990/91 ቀጥተኛ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት በመፍጠር በሳዑዲ አረቢያ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሸፍኖ ሲሰራ የቆየ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ ግንቦት 1997 ጀምሮ ግን የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩዌት በይፋ ተከፍቶ መደበኛ ስራውን ጀምሯል። በዚህም በሁለቱ አገራት መካከል የቆየ የንግድ፣ የኢንቨስትመንትና ቴክኒክ ትብብር ከመመስረቱም በላይ በረካታ ቁጥር ያሏቸው ኢትዮጵያውያን በኩዌት እደሚኖሩ ይገመታል።

እነዚህ በኩዌት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተለያየ መንገድ በመደራጀት የአድኬሲና የልማት ሥራዎች ላይ የነቃ ተሳትፎ እያደረጉ ከሚገኙት መካከል አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ በኩዌት ማህበር በአንፃራዊነት የተጠናከረና የተሻለ አቅም የፈጠረ የዳያስፖራ አደረጃጀት ነው።

## የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ በኩዌት ሊቀመንበር መልዕክት፤



አገር ማለት የምንኖርበት  ቦታ ሳይሆን ሁልጊዜም በውስጣችን የምትኖር ዕሴት ናት። የሰው ልጅ በህይወት አጋጣሚ የትም ቦታ ሊኖሩ ቢችልም ፍቅርና ትውስታው ግን ሁሌም  በልቦናዉ ውስጥ ካለች አገር የተባለች ዕሴት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነዉ። ይህንን ዕውነታ በመግለጽ ረገድ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሕያው ምስክሮች ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ለዚህም ነው እናት አገርን እየናፈቅን፣ ስለርሷ እያሰብንና እየተጨነቅን የምንኖረው። ለዚህም ነው ለወቅታዊ አገራዊ ጥሪና የልማት ስራዎች ሳናመነታ አቤት እንድንል አቅምና ጉልበት ያገኘነው።

አቶ ሲሳይ ተሾመ

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ በኩዌት ማህበር እ.ኤ.አ በ2018 እንደ አዲስ የተዋቀረ ማህበር ሲሆን፣ ዓላማው በኩዌት የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንና ትውልደ ኢትዮጵያዉያን የጋራ ጉዳዮቻቸውን በተደራጀ ሁኔታ ለማከናወን፣ ለችግሮቻቸው የጋራ መፍትሔ ለማፈላለግ እንዲሁም በአገር ልማት ላይም የዜግነት ግዴታቸውንና የበኩላቸውን አሻራ ለማኖር የተቋቋመ ማህበር ነው። ማህበሩ አንግቦ የተነሳውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከተመሰረተበት ዕለት አንስቶ በርካታ ሥራዎችን ሲያከናዉን ቆይቷል።

ለወቅታዊ ሀገራዊ ጥሪ ምላሽ ለመስጠት በተደረገ እንቅስቃሴ ከማህበሩ አካውንትና ዳያስፓራን በማስተባበር ከአንድ ሚሊዬን ብር በላይ ድጋፍ አድርጓል። የኩዌት ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ለህዳሴዉ ግድብ ለተከታታይ አመታት በየአመቱ ከ400 እስከ 500 ሺ ዶላር ያዋጣ ሲሆን፣ ይህ ዉጤት ይገኝ ዘንድ ማህበሩ የላቀ ሚና ተጫዉቷል። ለገበታ ለአገርና ሌሎች ሀገራዊ ፕሮጀክተቶችም ድጋፍ ይገኝ ዘንድ የድርሻዉን አበርክቷል። የተለያየ ችግር ገጥሟቸው በኤምባሲው መጠለያ ይኖሩ ለነበሩ በርካታ ዜጎችን ወደ አገር መግቢያ የአየር ቲኬት እንዲሁም የአስቤዛ ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛል።



ኩዌት ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሆን በቤት ውስጥ የሚሰሩ ሴት እህቶቻችንን ህይወት ለማሻሻል የልብስ ስፌት ማስልጠኛ ማዕከል በማደራጀት፣ የልብስ ስፌት ማሽን ገዝቶ በመስጠትና ለአስልጣኝ በመቅጠር ዜጎች ተጨማሪ ሙያ እንዲያዳብሩ ያደረገ ሲሆን፣ በርካታ ዜጎቻችን የዚህ እድል ተጠቃሚ ሆነዉ ህይወታቸዉን አሻሽለዋል። በኩዌት የኢትዮጵያ ኤምባሲ በተዘጋበት ወቅት በተለያየ የጤና እክል ምክንያት በየሆስፒታሉ ለተኙ ዜጎቻችን ድጋፍ በማድረግና በመጠየቅ የህክምና ወጪቸውን የመሸፈንና የማጽናናት እንዲሁም ወደ አገር ቤት የመሸኘት ስራዎችን አከናውኗል። በተጨማሪም በህግ ጥላ ስር የሚገኙ ዜጎችን በእስር ቤት በመገኘት ጉብኝቶችንም አድርጓል። ኤምባሲው ተዘግቶ በቆየበት ጊዜ የዜጎችን ፓስፓርት ለመስጠት ወደ ኩዌት የመጡ የኢሚግሬሽን ስራተኞች ጋር በመተባበር የፓስፓርት እደላ ቀልጣፋና የተሳካ እንዲሆን የበኩሉን ሚና ተጫውተዋል።



ኩዌት የሚገኝውን ማህበረስብ በማንቀሳቀስ ስለአገራችን ተጨባጭ መረጃ በመስጠት የኖሞር (#Nomore) የበይነ መረብ ዘመቻ እንቅስቃሴ ንቁ ተሳትፎ አድርጓል። የ2015 የኢትዬጵያ አዲስ አመትን መቀበያና የአንድነት ቀንን ከኤምባሲው ጋር በመሆን አክብሯል። የኢትዮጵያን ባህል ለማስተዋወቅ (ለካልቸር ዴይ) ለተዘጋጀ ዝግጅት የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የኢትዮጵያን ባዕል ማስተዋወቅ ተችሏል። እንዲሁም በኩዌት ከሚገኙ የተለያዩ የዕርዳት ድርጅቶችና የኩዌት ዜጎች በተገኙበት የኢትዬጵያን ቡና በስፊው የማስተዋወቅ ስራ ሰርቷል።





## 11. በሊባኖስ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማኅበር

የኢትዮጵያ እና የሊባኖስ ግንኙነት ከተመሰረተ ረዥም ጊዜ ያስቆጠረ ሲሆን፣ በካይሮ በሚገኘው የኤፌዴሪ ኤምባሲ አማካኝነት በዲፕሎማቲክ ውክልና ሊባኖስን በመሸፍን ሲሰራ ቆይቷል። እ.ኤ.አ በ1992 ዓ/ም ወዲህ ግን ኢትዮጵያ ያላትን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማሻሻል እና በሊባኖስ ያሉ የዜጎቻችን የመብት ጥሰት በቅርበት ተከታትሎ መፍትሔ ለማበጀት እንዲቻል የኢትዮጵያ መንግስት በቤይሩት የቆንፅላ ጽ/ቤት በመክፈት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በሊባኖስ ቁጥራቸው 150,000 ያላነሱ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮያውያን እንደሚኖሩ ይገመታል። በሊባኖስ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተለያየ መንገድ በመደራጀት የአድቮኬሲና የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል ዛህሌ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ማህበር፣ ሳይዳ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ማህበር፣ ጠራቢሎስ( ትሪፖሊ) የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ማህበር፣ መስዋዕት ማህበር፣ ፍካት ለኢትዮጵያ ማህበር፣ ሀምሳ ሎሚ ማህበር፣ እጅ ለእጅ ማህበር፣ ህብረት በአንድነት ማህበር፣ ባታ ለማርያም ማህበር ተጠቃሽ ናቸው። ከማህበራቱ መካከል አንዱ የሆነው በሊባኖስ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማኅበር በአንፃራዊነት የተጠናከረና የተሻለ አቅም የፈጠረ አደረጃጀት ነው።

ማህበሩ በሊባኖስ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ እ.ኤ.አ 2009 የተመሰረተ ሲሆን፣ ማህበሩ ከመብትና ጥቅም ማስከበር በተጨማሪ ዜጎች ለአገራዊ የልማት ስራዎች በተለይም ለታላቁ የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ግንባታና ለሌሎች አገራዊ ጥሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ በማስተባበር ላይ ይገኛል።

## በሊባኖስ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ማህበር ሊቀመንበር መልዕክት፤



የኢትዮጵያ መንግስት አገራዊ መሻሻያዎችን በማድረግ በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትጵያውያን ትኩረት አድርጎ በአገር ውስጥ የዳያስፖራ አገልግሎት መ/ቤትን በማቋቋም በውጭ አገራት የሚገኙ የኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትጵያውያን መብትና ጥቅም ለማስከበርና ለአገራዊ ልማት የመኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በማስተባበር ላይ እንዳለ ይታወቃል፡፡

በሊባኖስ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበርም በቤይሩት የኢትዮጵያ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት ድጋፍ በየጊዜው እየተጠናከረ በመምጣት በሊባኖስ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም እያስጠበቀ የሚገኝ ሲሆን፣ ለአገር ገጽታ ግንባታና ልማት የበኩሉን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡

ማህበራችን በቀጣይ ከቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት ጋር በመተባበር የተቋቋመለትን ዓላማ ከማሳካት አንጻር የተጀመሩ የኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም የማስጠበቅ እንዲሁም ዜጎችን በማንቀሳቀስ በአገር ቤት የሚከናወኑ የልማት እና የድጋፍ ስራዎችን አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን በራሴና በማህበሩ ስም ላረጋገጥ እወዳለሁ።
ዲ/ን በኃይሉ ጌታነህ

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

⁜ ማህበሩ ለችግር የተጋለጡ ዜጎቻችን ክብርና ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ ከ200 በላይ የሚሆኑ ሰዎችን በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችልና የመጠለያ አገልግሎት የሚሰጥ ህንጻ በመከራየት በ2014 ዓ/ም ብቻ ለችግር የተጋለጡ 429 ዜጎችን ጉዳያቸው አልቆ ወደ አገራቸው እስከሚመለሱ በአማካይ ከ2-6 ወር ድረስ የመጠለያ፣ ምግብ፣ ህክምና ክትትልና ድጋፍ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የዜጎችን የአእምሮና አካልዊ ደህንነት ለመጠበቅ እንዲያስችል በመጠለያ ቆይታቸው ወቅት ለስልጠና አስፈላጊ ግብዓቶችን (ለምሳሌ የኮምፒዩተር፣ ፀጉር፣ የልብስ ስፌት መሳሪያዎችን) ገዝቶ በማሟላት የተለያዩ የሙያ ስልጠናዎች ሰጥቷል፡፡



⁜ ማህበሩ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠረ ለችግር ለተጋለጡ ዜጎችን የፋይናንስ፣ ቁሳቁስ እና የህክምና ድጋፍ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን፣ በዚህም ለ63 የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸው እና ለ15 የሳምባ ታማሚዎች በድምሩ 78 ሰዎች የህክምና ድጋፍ ተደርጓላቸዋል፡፡ በተለያዩ ማረሚያ ቤቶችና ፖሊስ ጣብያዎች የሚገኙ ዜጎችን ከቆንስላ ጀኔራል ፅ/ቤት እና የሀይማኖት ተቋማት ጋር በመተባበር አስፈላጊ ቁሳቁስ በመያዝ ጉብኝት አድርጓል። ማህበሩ በሊባኖስ በተለያዩ ሆስፒታሎች የሚገኙ ወገኖች ድጋፍ እንዲያገኙ አስተባብሯል፡፡ እንዲሁም በክስ ምክንያት ወደ አገራቸው መመለስ ያልቻሉ ዜጎች የህግ አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፍ በማፈላለግ ጉዳያቸው ውሳኔ እንዲያገኝና ወደ አገራቸው እንዲሳፈሩ አግዟል። በተጨማሪም በሊባኖስ መኖሪያ ፍቃድ የሌላቸው ዜጎችን ወደ አገር ቤት ለመመለስ በተደረገው እንቅስቃሴ የኮሚዩኒቲ ማህበሩ የተለያዩ የቴክኒካል ድጋፎችን በመስጠት አገልግሎቱ ተደራሽ፣ ፈጣንና ቀልጣፋ እንዲሆን አስተዋፆ አድርጓል።

⁜ ከፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስራዎች ጋር በተያያዘም የውጭ አገራት ጣልቃ ገብነትን በመቃወም በሊባኖስ ቤይሩት ከተማ በርካታ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት ደማቅ የ#NoMore ሰልፍ በማድረግ የኢትዮጵያ እውነታ የማስረዳትና የማሳወቅ ስራዎችን ሰርቷል።






⁜ ማኅበሩ አገራዊ ጥሪዎችን ለመደገፍ $35,000 ዶላር፣ በትግራይ እና በመተከል ለተፈናቀሉ ዜጎች $10,000 እንዲሁም በአማራ ክልል ለተፈናቀሉ ዜጎች $10,000 ዶላር ፤ በአጠቃላይ 55,000 የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ አድርጓል፡፡



## በእስራኤል የላቀ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ያሉ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች

እስራኤል በአዲስ መልክ እንደ አገር ከመመስረትዋ በፊት በኢትዮጵያና በእስራኤል መካከል ለዘመናት የቆየ ጠንካራ ግንኙነትና ወዳጅነት እንደነበራቸው ይነገራል፡፡ በተለይም ሁለቱ አገሮች የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል ግንኙነታቸውን እንዲጠናከር በንጉስ ሰሎሞን ዘመን ከኢትዮጵያ በንግስተ ሣባ በተመራው የልዑካን ቡድን በእስራኤል የተደረገው ጉብኝት ለግንኙነቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ መሆኑ በታሪክ ይወሳል፡፡ የሁለቱ አገሮች ግንኙነት ጥንታዊ መሰረት እንዳለው የሚያሳየው እውነታ የቤተ እስራኤል አባላት ለዘመናት በኢትዮጵያ መኖራቸው ነው፡፡ ኢትዮጵያና እስራኤል ይፋዊ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እ.ኤ.አ በ1955 የጀመሩ ሲሆን፣ ይህንን ተከትሎ የእስራኤል መንግስት እ.ኤ.አ በ1956 በአዲስ አበባ የቆንስላ ጽ/ቤት ከዚያም እ.ኤ.አ በ1961 በኤምባሲ ደረጃ ግንኙነቱን ከፍ አድርጓል፡፡ ኢትዮጵያም በዚሁ ጊዜ ግንኙነቷን ወደ ቆንስላ ደረጃ አሳድጋለች።

በተለያየ መልኩ ከኢትዮጵያ ወደ እስራኤል የገቡትን ቤተ-እስራኤላውያንና በእስራኤል የተወለዱትን ጨምሮ ከ160,000 በላይ የኢትዮጵያ አይሁዶች/ቤተ-እስራኤላውያን በእስራኤል እንደሚኖሩ ይህም ከእስራኤል አጠቃላይ የህዝብ ብዛት 1.7 በመቶ ያህሉን እንደሚይዝ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ቤተ-እስራኤላውያን ያልሆኑና በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንም በአገሪቱ እንደሚኖሩ ይታወቃል። ከቤተ-እስራኤላውያኑ መካከል በእስራኤል ፓርላማ እንዲሁም በመንግስት ከፍተኛ የሥራ ሃላፊነት የሚያገለግሉ፣ በተለያዩ የሙያ መስኮች ከፍተኛ የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ያላቸው፣ ለማህበረሰባቸው አገልግሎት የሚሰጡና ለትውልድ አገራቸው ሠላም፣ ልማትና ዕድገት ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ ላይ ያሉ ይገኛሉ፡፡ ባላቸው አቅም በትውልድ አገራቸው በኢንቨስትመንት፣ በንግድ እና የቱሪዝም መስኮች የተሰማሩም አሉ፡፡ በእስራኤል የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመሰረቷቸው ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች በመታገዝ ለአገራዊ ጥሪዎች ምላሽ በመስጠት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ያህልም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የመሰረት ድንጋይ ከተቀመጠበት ጊዜ አንስቶ የትውልድ አገራቸውን የመልማት መብት ከመደገፍ ጀምሮ ከአንድ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ በቦንድ ግዢና ሥጦታ ድጋፍ ማድረጋቸውን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በእስራኤል ከሚገኙና በተለያየ ደረጃ ተሳትፎ ከሚያደርጉ በርካታ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች መካከል በእስራኤል የድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ፣ በእስራኤል የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት (IETV)፣ ስለ ኢትዮጵያ ዝም አንልም ማህበር፣ በእስራኤል የተከለኃይማኖት ማህበር፣ በእስራኤል የትውልደ ኢትዮጵያውያን ምህንድስና ባለሙያዎች ቡድን፣ ጌሸር (ድልድይ) የጤፍ ነጋዴዎች ማህበር፣ በእስራኤል የኢትዮጵያ ማህበረሰብ፣ ኢትዮ-እስራኤል ጮራ የኪነ-ጥበብ ማህበር፣ ሠላም የመረዳጃ ዕድር እንዲሁም በእስራኤል የትውልደ ኢትዮጵያውያን የጤና ባለሙያዎች ቡድን ይገኙባቸዋል። ከእነዚህ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች መካከል የላቀ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ የሚገኙ አደረጃጀቶች ደግሞ ጥቁር አንበሳ ኢትዮ-እስራኤል ግሎባል ዩኒቲ እና በእስራኤል የኢትዮጵያ ህዳሴ ምክር ቤት ናቸው።

## 12. ጥቁር አንበሳ ኢትዮ-እስራኤል ግሎባል ዩኒቲ




ከአንድ ዓመት በፊት ትውልድ አገራችን ኢትዮጵያ ያጋጠማትን ችግር በመገንዘብ በእስራኤል የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ቤተ እስራኤላውያን/ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጥቁር አንበሳ ኢትዮ-እስራኤል ግሎባል ዩኒቲ (Black Lion Ethio-Israel Global Unity) በሚል ስያሜ በ205 (ሁለት መቶ አምስት) አባላት ተቋቋመ። ዋና ዓላማውም በጦርነት ምክንያት ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ፣ ሃብትና ንብረታቸው የወደመባቸው ወገኖቻችን መልሶ በማቋቋም ወደ ቀድሞ ህይታቸው ተመልሰው እንዲኖሩ ድጋፍ ማሰባሰብ እንዲሁም በኢትዮጵያ እና እስራኤል መካከል ያለው የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ግንኙነት እንዲጠናከር አስተዋጽኦ ማድረግ ነው።

## የማህበሩ ሰብሳቢ ራብ ያፌት አለሙ ያስተላለፉት መልዕክት፤

ማህበራችን በትውልድ አገራችን ላይ በተከሰተው ጦርነት ምክንያት ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ፣ ሃብትና ንብረታቸው የወደመባቸው ወገኖቻችን መልሶ ለማቋቋምና ወደ ቀድሞ መደበኛ ህይወታቸው ተመልሰው እንዲኖሩ ለማድረግ ድጋፍ ማሰባሰብ፣ በኢትዮጵያ እና እስራኤል መካከል ያለው  የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት እንዲሁም የሁለቱ አገራት ኢኮኖሚና ማህበራዊ ግንኙነት እንዲጠናከር በመስራት ላይ ይገኛል። ያሉንን ሦስት መቶ የሚጠጉ አባላቶችና ማህበረሰቡን በማስተባበር በአገር ቤት በጦርነት ምክንያት ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ፣ ሃብትና ንብረታቸው የወደመባቸው ወገኖቻችን መልሶ ለማቋቋምና ወደ ቀድሞ ህይዎታቸው መመለስ እንዲቻል አቅማችን የፈቀደውን ለማድረግ ሞክረናል፤  ይህንኑ ለወገኖቻችን የምናደርገውን ድጋፍ አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል።



በኢትዮጵያ እና እስራኤል መካከል ያለው የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት እንዲጠናከር እንዲሁም የሁለቱ አገራት ኢኮኖሚና ማህበራዊ ግንኙነት እንዲዳብር የራሳችን አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጁነን። ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ከመሆኗም በላይ በተለያዩ የተፈጥሮ ሃብት የበለፀገች አገር በመሆኗ፤ እስራኤል ደግሞ በቴክኖሎጂ ያደገች አገር በመሆኗ የሁለቱ አገሮች የተጠናከር ግንኙነት ያለውን ፋይዳ በሚገባ እንረዳለን። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ወጣቶች ወደ እስራኤል አገር  መጥተው  በእስራኤል አገር ያለውን ቴክኖሎጅና እውቀት ልምድ እንዲቀስሙ በእስራኤል አገር የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን/ ቤተ እስራኤላውያን ወይም እስራኤላውያን ወጣቶች ወደ ኢትዮጵያ ሄደው በትውልድ አገራችን ኢትዮጵያ ያለውን የተፈጥሮ ሃብትና የቱሪዝም ሃብቶች እንዲጎበኙ፣ የእውቀት ሽግግር እንዲያደርጉና በሌሎች ዘርፎች ላይም ተሳትፎ ማድረግ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎችን በጥናት በመለየት ወደ ተግባር ለመግባት እየተዘጋጀን እንገኛለን።




ስለሆነም በእስራኤል የምትገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ቤተ እስራኤላውያን/ትውልደ ኢትዮጵያውያን የማህበራችንን ዓላማ ለማሳካት ከጎናችን እንድትሆኑ፣ ወደፊትም በአገር ቤት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ወገኖቻችን የምናደርገውን ድጋፍና አለኝታነት አጠናክረን እንድንቀጥል እንዲሁም በትውለድ አገራችን ኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን የተፈረመው የሰላም ስምምነት እውን እንዲሆን ለተግባራዊነቱ የበኩላችንን ድጋፍ እንድናደርግ ጥሪዬን አቀርባለሁ፤ አመሰግናለሁ።

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

- በ2014 ዓ.ም በአገር ቤት ጥቃት ደርሶባቸው ከቀያቸው ለተፈናቀሉ፣ ሃብት ንብረታቸው ለወደመባቸው ወገኖቻችን ድጋፍ የሚሆን በእስራኤል አገር ከሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን/ቤተ እስራኤላውያን፣ ኢትዮጵያውያን ገንዘብ በማሰባሰብ አንድ ሚለዮን ሁለት መቶ ሺህ ብር ለወገኖቻችን ድጋፍ አድርጓል።

- በ2015 ዓ/ም በተለያዩ ቦታዎች ተፈናቅለው ለሚገኙ ወገኖቻችን ድጋፍ ለማድረግ በእሰራኤል አገር ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን/ቤተ-እስራኤላውያን ያሰባሰቡትን የድጋፍ ገንዘብ የማህበሩ ተወካዮች በአገር ቤት በአካል በመገኘት ለተጎዱ ወገኖቻችን ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ብር የሚገመት የምግብ ዘይትና ዱቄት እርዳታ አድርጓል።

- ወደፊትም በአገር ቤት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ወገኖቻችን ለመደገፍና ለመርዳት እንዲሁም የወደሙ መሰረት ልማቶችን መልሶ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ድጋፍ ለማድረግ በእስራኤል የሚገኙ አበላቱንም ሆነ ከማህበሩ ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን፣ ቤተ እስራኤላውያን/ ትውልድ ኢትዮጵያውያንን አስተባበሮ ለመደገፍ በእቅድ ይዞ እየሰራ ይገኛል።

- በኢትዮጵያ እና እስራኤል መካከል ያለው የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት እንዲጠናከር እንዲሁም ሁለቱ አገራት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች የሚያደርጉት ትብብር ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ እቅድ አለው።

## 13. በእስራኤል የኢትዮጵያ ህዳሴ ምክር ቤት



በእስራኤል የኢትዮጵያ ህዳሴ ምክር ቤት የኢትዮጵያን ህዳሴ ለማረጋገጥ ማህበረሰቡን በማስተባበር ሁለንተናዊ ድጋፍና ተሳትፎ ለማድረግ የተቋቋመ ማህበር ነው።

የምክር ቤቱ አስተባባሪ አቶ ራህሚም አላዛር መልዕክት

በእስራኤል የኢትዮጵያ ህዳሴ ምክር ቤት ከተመሰረተ ጀምሮ ዋነኛ ዓላማው የኢትዮጵያን ህዳሴ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን ነው።

ለምክር ቤቱ አባላትም ሆነ በእስራኤል ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ቤተ እስራኤላውያን/ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆችና እስራኤላዊያን የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ እድገትና ብልጽግና በማፋጠን ህዳሴዋን ለማረጋገጥ ለምናደርገው ጥረት እያደረጋችሁ ስላለው ድጋፍ ምስጋናዬን ማቅረብ እወዳለሁ። በዚህ አጋጣሚም በኢትዮጵያ እየተገነቡ ያሉ እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን የመሳሰሉ ትልልቅ የልማት ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ፣ የኢንቨስትመንትና ንግድ እድሎች ላይ ለመሳተፍ፣ በኢትዮጵያ ያሉ የቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎችን ለመጎብኘት፣ በማህበራዊ ዘርፍ በጤና መስክ የህክምና ሙያ እና መሳሪያዎች ድጋፍ ለማድረግ፣ በእውቀትና ቴክኖሎጅ ዘርፍ ለመሳተፍ የጀመራችኋቸውን ጥረቶች አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ እጠይቃለሁ።

በተጨማሪም የሁለቱን አገራት የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ለማሳደግ፣ ማህበራዊ መስተጋብርን ለማስፋት፣ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ቋንቋና ባህል እንዲሁም እሴትቶቿን ለወጣቶች፣ ለልጆቻችንና ለትውልድ ማሳተላለፍ ሁላችንም የበኩላችን ሁሉ ጥረትና ድጋፍ እንድናደርግ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

አመሰግናለሁ።



## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

- ከተመሰረተ ጀምሮ በኢትዮጵያ  እየተከናወኑ ያሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በመደገፍ አባላቱንና ማህበረሰቡን በማስተባበር የማህበሩ አባላት በየሚኖሩበት ከተማ የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያንና ቤተ እስራኤላውያን/ትውልደ ኢትዮጵያውያን ማህበረሰብን በማስተባበር ድጋፍ እያደረ ይገኛል።

- ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በቦንድ ግዥና በስጦታ፣ ለተለያዩ ሀገራዊ ድጋፎችና ጥሪዎች ማለትም ገበታ ለሀገር፣ ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን ማቋቋሚያ ድጋፍ፣ በኮረና ወረርሽኝ ወቅት ለወገኖቻችን ድጋፍ በማድረግ ረገድ የምክር ቤቱ አባላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

- በተለያዩ ጊዜያት ከእስራኤል አገር ወደ ጎንደርና ባህርዳር ከሚሄደው የህክምና ቡድን ጋር በመተባበር የሙያ ድጋፍ አድርጓል። የህክምና ቡድኑም ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል እየሰራ ይገኛል።

- የሁለቱን አገራት የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን ለማሳደግና ለማጠናከርም በእስራኤል ከሚገኘው የኢፌዴሪ ኤምባሲና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያን ባህል፣ ታሪክ፣ ቋንቋና እሴት በማስተዋወቅ ላይ ይገኛል።

- በእስራኤል ያሉ ትውልደ ኢትዮጵውያን/ቤተ እስራኤላውን ወጣቶችን እና እስራኤላውያን ጎብኝኘዎችን ስለ ኢትዮጵያ የቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎች በማስረዳትና ቱሪስቶችን በመመልመል በርካታ ቱሪስቶችን ወደ ሃገር ቤት በመውሰድ ለቱሪዝም ዘርፉ እድገት አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል።

- በእስራኤል የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ቤተ እስራኤላውያን/ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም እስራኤላዊያን በአገር ቤት እየተካሄዱ ባሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ስራዎች ማለትም በኢንቨስትመንት፣ ንግድ፣ ገጽታ ግንባታ፣ በቴክኖሎጅና እውቀት ሽግግር መስኮች እንዲሳተፉ በመመልመልና በማግባባት አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል።



## በቱርክዬ የኢትዮጵያ አንደነት እና ትብብር ማህበር

ቱርክዬና ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ግንኙነት ያላቸው አገሮች ናቸው። ግንኙነቱ የጀመረው እ.ኤ.አ በ1896 በሱልጣን አብዱልሀሚድ 2ኛ እና በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመን የልዑካን ልውውጥ በማድረግ ነው። ይህን ተከትሎ ቱርክዬ እ.ኤ.አ 1912 ዓ/ም በሐረር ከተማ የመጀመሪያ የክብር ቆንስላ ሾማ የነበረ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ በ1912ዓ/ም በይፋ የቆንስላ ጽ/ቤት ከፍታለች። ሁለቱ አገሮች ይፋዊ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የጀመሩት እ.ኤ.አ በ1925 ሲሆን፣ ይህ ግንኙነት በ1926 ዓ/ም በጉዳይ ፈጻሚ ደረጃ እውን ሆኖ ቱርክዬ ኤምባሲዋን በአዲስ አበባ ከፈተች። ኢትዮጵያም በ1933 ዓ/ም ኤምባሲዋን በቱርክዬ አንካራ ከፍታለች። ኢስታንቡል ታሪካዊ፣ የንግድና ኢንቨስትመንት ማዕከል፣ ኢትዮጵያውያንም የሚኖሩባት ከተማ በመሆኗ የሁለቱ አገራትን የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ማጠናከር ይቻል ዘንድ አገራችንን በኢስታንቡል ቆንስላ ፅ/ቤት እ.ኤ.አ 2018 ከፍታ ነበር። በኢትዮጵያና ቱርክዬ መካከል የንግድ፣ ኢንቨስትመንት፣ የመከላከያ፣ የትምህርት፣ የጤና የሳይንስ እና መሰል ስምምነቶች የተፈረሙ ሲሆን፣ ይህም የሁለቱ አገራት ግንኙነት በመጠናከር ላይ እንዳለ ያሳያል።

በአገሪቱ የሚገኙ ኢትዮጵያውን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከሌሎች የአውሮፓ እና የመካከለኛው ምስራቅ አገራት ጋር ሲነጻጸር ቁጥሩ ከፍተኛ የሚባል አይደለም፡፡ ይሁንንና ወደፊት በከፍተኛ ሁኔታ ሊጨምር የሚችልበት ዕድል እንዳለ ከዕለት ዕለት በህገወጥ ደላሎች በኩል ለስራ ፍለጋ እና ወደ አውሮፓ ለመሻገር በሚል ወደቱርክ የሚገባው የኢትጵያውያን ቁጥር መጨመር አመላካች ነው፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በቱርክ ያሉት የኢትዮጵያዊያን ዳያስፖራ አባላት ስብጥር በአብዛኛው ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ውስን ቁጥር ያላቸው በንግድ ወይም በቱሪዝም ቪዛ የሚመላለሱ እንዲሁም በተለያዩ ዘርፎች ተቀጥረው የሚሰሩ ናቸው፡፡ ይሁንንና ይህ ቁጥር ወይም ስብጥር በፍጥነት እየተለወጠ ይገኛል፡፡

በቱርክዬ በርካታ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች ተመስርተው የሚንቀሳቀሱ ሲሆን፣ የላቀ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ከሚገኙ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች መካከል በቱርክ የኢትዮጵያ አንደነት እና ትብብር ማህበር ይገኝበታል። በተጨማሪም ሀበሽስታን ልማት ኮርፖሬሽን፣ ማክስ ብሪጅ፣ በቡልጋሪያ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ማህበር፣ የኦሮሞ ጥናትና ልማት ማህበር፣ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በቱርክዬ እንዲሁም በቱርክዬ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተሻለ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ አደረጃጀቶች ናቸው።

## በቱርክዬ የኢትዮጵያ አንደነት እና ትብብር ማህበር ሊቀመንበር መልዕክት፤
## (ETHIOPIAN SOLIDARITY AND COOPERATION ASSOCIATION IN TURKYE)




ማህበራችን ከተቋቋመ አጭሮ ግዜ ቢሆንም በቱርክዬ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ተቀባይነቱ እጅግ ላቅ ያለ በመሆኑ በጦርነቱ ምክንያት የተፈናቀሉ ወገኖቻችንን ለመርዳት ባዘጋጀነው የገቢ ማሰባሰቢያ ላይ በነቂስ በመውጣት ከአነስተኛ ገቢያቸው ላይ ለወገናቸው እንዲደርስ 27ሺ ደላር አሰባስበው ወደ አገር ቤት ልከዋል። ይህም ዳየስፖራው ምን ያህል ለአገሩና ለወገኑ ፈጥኖ ደራሽ እንዲሁም የዜግነት ግዴታውን የሚወጣ መሆኑን ያሳያል። ዳያስፖራው ወደፊትም ቢሆን አገሩ በምትፈልገው ጊዜ ሁሉ ከጎኗ ለመቆም ዝግጁ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማረጋገጥ እፈልጋለሁ።

ማህበራችንም ይህንን መልካም ጅማሮ በማጎልበት አገራችንን ወደ ላቀ እድገት ለማምጣት አቅሙ በሚፈቅደው መጠን ድጋፍ በመስጠት የራሱን ሚና ለመወጣት ዝግጁ ነው። ከዚህም ባሻገር ኢትዮጵያ የአፍሪካ መዲና እንደሆንዋ ማህበራችንም በቱርክዬ ከሚገኙ አፍሪካውያን ማህበራት ጋር ያለውን መልካም ወዳጅነት በማጎልበት የጋራ ችግሮችቻችንን በጋራ መፍታት የሚያስችሉ ዕድሎችን ለመፍጠር እንደሚሰራ መግለጽ እወዳለሁ።

ኢትዮጵያ አገራችንን እና ህዝባችንን አምላክ ይባርክ!

አቶ ዮሴፍ ጌታቸው

በቱርክዬ የኢትዮጵያ አንደነት እና ትብብር ማህበር ሊቀመንበር

## ማህበሩ የተቋቋመበት ዓላማና ያከናወናቸው ተግባራት፤

ማህበሩ የሐይማኖት፣ የጾታ የጎሳና የፖለቲካ ልዩነት ሳይደረግ በቱርክዬ የሚኖር ኢትዮጵያዊ የአገሪቱን ህግ እና ስርዓት አክብሮ እንዲኖርና መብትና ጥቅሙ እንዲከበርለት ይሰራል። በተጨማሪም በሞት፣ በህመም፣ በአደጋ፣ በአካል ጉዳት ወይም በስራ ማጣት የኢኮኖሚ ችግር ላጋጠማቸው አባላት ድጋፍ እና እርዳታ ያደርጋል። አባሎች እና ቤተሰቦቻቸው ለትምህርት፣ ለስልጠና፣ ለስፖርት መስሪያ እና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚጠቀሙበት ማዕከል ለመገንባትም ዕቅድ ይዟል። ወደ ኢስታንቡል እና አካባቢው አዲስ ለሚመጡ ኢትዮጵያውያን ከቱርክዬ ባህል እና የአኗኗር ዘይቤ ጋር የሚተዋወቁበትን የምክር አገልሎት እና ድጋፍ ይሰጣል፤ ወጣቶች የሙያ ሰልጠናና የነጻ ትምህርት እድል እና ልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እገዛ ያደርጋል። ለወቅታዊ አገራዊ ጥሪዎችና ፕሮጀክቶች ምላሽ ለመስጠትም  በቱርክዬ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኢምባሲ ጋር በቅርበት በመስራት ሀብት የማሰባሰብ እንዲሆም የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስራዎችን ያከናውናል።






በቱርክዬ የኢትዮጵያውያን አንድነትና የትብብር ማህበር በያዝነው የፈረንጆች አመት የተመሰረተ አዲስ ማህበር ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል አባላትን ማፍራት የቻለ ከመሆኑም በላይ በቱርክዬ አገር በተለይም ደግሞ በኢስታንቡል ከተማና አከባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በማቀራረብና በማገናኘት እንዲሁም ከአትዮ-ቱርካዊያን ጋር ትስስር በመፍጠር ሁለቱ አገራት የጋራ ባህሎቻቸውንና እሴቶቻቸውን ማሳደግና መንከባከብ የሚያስቸሉ የጋራ መድረኮችን በማዘጋጀት ጉልህ ሚና በመጨወት ላይ ይገኛል።

ማህበሩ በወቅታዊ የአራችን ጉደዮች ላይም አባላቱ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የበኩላቸውን ተሣትፎ ማድረግ እንዲችሉ ግንዛቤ የሚያገኙባቸው መድረኮችን ያመቻቻል፤ ተሳትፏቸው እንዲያድግም ይሰራል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በየጊዜው የሚቀርቡ አገራዊ ጥሪዎችን በመቀበል በኢትዮጵያ ላይ የተፈጠሩ አፍራሽ ዘመቻዎችን ለመመከት " #በቃ" ወይም #NOMORE አለም አቀፍ የዳያስፖራ የተቀውሞ እንቅስቃሴን በመቀላቀል ድምጹን አሰምቷል። በተመሳሳይም በአሜሪካ ምክር ቤቶች የቀረቡ የማዕቀብ ረቂቅ ህግች ላይ ያለውን ተቃውሞም ገልጿል። በታለቁ የአገር ቤት ጥሪ ወቅትም ዜጎች ጥሪውን ተቀብለው ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡና ወደ አገር ቤት ሲጓዙም መድሃኒቶችና የህክምና ቁሰቁሶችን ይዘው እንዲሄዱ አስተባብሯል። ከዒድ እስከ ዒድ ጥሪን ተከትሎም ለማህበሩ አባላትም ሆነ ለሌሎች ወቅታዊ መረጃ በማድረስ የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል።

ማህበሩ የትምህርት እድል አግኝተው ወደ ቱርክዬ አገር ለሚመጡት ተማሪዎች አቀባበል በማድረግ የአገሪቱን ባህልና ወግ እንድያውቁ፣ በአገሪቱ ህግ የተካለከሉና የተፈቀዱ ጉዳዮችን እንዲረዱና ራሳቸውን ከአካባቢው ጋር እንዲያለማምዱ አጫጭር ስልጠናዎችን ሰጥቷል። በተመሳሳይ ለሕክምና እየመጡ የሚቸገሩ ዜጎች ጉዳይ እልባት እንዲያገኝ ፍርድ ቤት ድረስ በፈቃደኝነት በመቆምና በመከራከር የማህበሩ አባላት ድጋፍ አድርገዋል። በቱርክዬ የሚገኙ ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ማህበራትን የሚያሰባስብ ጥላ ማህበር ለማቋቋም የሚደረገውን ጥረት በመደገፍም ከኢፌዴሪ ሚሲዮን ጋር በጋራ በመስራት ላይ ይገኛል።



## በዩናይትድ ኪንግደም የላቀ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ያሉ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች

ኢትዮጵያ እና ዩኬ ለረጅም ዘመናት የቆየ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያላቸው አገራት ናቸው። ግንኙነታቸው በባህላዊው የዲሎማሲ ስርዓት ተጀምሮ አሁን ላይ ሉዓላዊነትን ያከበረ፣ በመደጋገፍ እና መተጋገዝ ላይ የተመሰረተ የ21ኛው ክፍለ ዘመን መልካም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ላይ የደረሰ ነው።

ኢትዮጵያና ዩናይትድ ኪንግደም ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ሰፊ የትብብር ማዕቀፎችን በመተግበር በተለይ በኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት መስኮች ውጤታማ ስራዎችን አከናውነዋል።

በዩናይትድ ኪንግደምና ሰሜን አየርላድ የሚገኙ ኢትዮጵዊያንና ትውልደ ኢትዮጵዊያን ቁጥር በውል ባይታወቅም 60 ሺህ እንደሚደርስ ይገመታል። ከእነዚህም በአብዛኛው በለንደን፣ በማንቸስተር፣ በሊቨርፑል፣ በሊድስና በበርሚንግሀም የሚኖሩ ሲሆን፣ የተቀሩት በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች ተበታትነው እንደሚኖሩ መረጃዎች ያሳያሉ።

የዩኬ የዳያስፖራው አደረጃጀትና ሀገራዊ ተሳትፎ

በዩናይትድ ኪንግደምና ሰሜን አየርላንድ 8 የኮሚኒቲ አደረጃጀቶች፣ 10 የሲቪክ ማህበራት እንዲሁም ወደ 30 የሚጠጉ ሀይማኖትን መሠረት ያደረጉ በአጠቃላይ ወደ 50 የሞሆኑ አደረጃጀቶች የሚገኙ ሲሆን፣ በተሻለ ጥንካሬና እንቅስቃሴ ላይ የሚገኙና የጎላ እንቅስቃሴ እያደረጉ ያሉት 17 የሚሆኑ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች ናቸው፡፡

የኮሚኒቲ አደረጃጀቶችና የሲቪክ ማህበራት እንቅስቃሴ በአጠቃላይ ሲታይ ሰፊውን የለንደን ማህበረሰብ በማቀፍ ለኮሚኒቲው አባላት ድጋፍ የመስጠት፣ የአገራችንን ብሔራዊ ጥቅም መሠረት ያደረጉ ሰላማዊ ሰልፎችንና የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞችን የማስተባበር፣ አንድነት ሊያጎለብቱ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ መድረኮችን የማመቻቸት፣ የህዳሴ ግድብ ግንባታን አስመልክቶ በአለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ስለአገራችን አቋም ግንዛቤ የመፍጠርና ለግድቡ ማጠናቀቂያ የገንዘብ ድጋፍ የማሰባሰብ፣ በአገራችን ለሚገኙ የጤና ተቋማት ድጋፍ የመስጠት፣ በጦርነት የተጎዱ የጤና ተቋማትን መልሶ ለማቋቋም የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፎችን የማድረግ፣ በየአመቱ ወደ ትውልድ አገራቸው ኢትዮጵያ በመጓዝ ከፍለው መታከም ለማይችሉ ዜጎች ነጻ የአይን ህክምና አገልግሎት የመስጠትና ለአገር ጠቃሚ የሆኑ ትምህርታዊ ኮንፈረንሶችን የማዘጋጀት ተግባራትን ያጠቃልላል፡፡

በዩናይትድ ኪንግደም የኢትዮጵያን እናድን ግብረ ኃይል እና የኢትዮጵያ ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን በዩኬ የተሻለ እንቅስቃሴ ካላቸው የዳያስፖራ አደረጃጀቶች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በዩናይትድ ኪንግደም የኢትዮጵያን እናድን ግብረ ኃይል ዲፌንድ ኢትዮጵያ ታስክፎርስ አውሮፓ እንዲፈጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉ ይነገራል። ሆኖም ግሎባል ኖሌጅ ኤክስቼንጅ ኔትወርክ፣ የተባበረች ኢትዮጵያ ለሰላምና ዕርቅ፣ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ በማንችስተር፣ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ በኒውካስል፣ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ በእንግሊዝ፣ በታላቋ ብሪታንያ የኢትዮጵያ ታሪክ ማህበር እንዲሁም የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ በበርኒንግሀም የተሻለ ተሳትፎ በማድረግ ላይ የሚገኙ አደረጃጀቶች ናቸው።

## 15. “ኢትዮጵያን እናድን ግብረ ኃይል” (Defend Ethiopia Taskforce UK)






በዩናይትድ ኪንግደም የኢትዮጵያን እናድን ግብረ ኃይል አስተባባሪ መልዕክት፤

በዩናይትድ ኪንግደም ኢትዮጵያን እናድን ግብረ ኃይል እ.ኤ.አ ኦክቶበር 2020 የአገራችንን ሰላም፣ ክብርና ሉዓላዊነት ለመከላከል የተቋቋመ የሲቭክ ማህበር ነው፡፡ በዩናይትድ ኪንግደም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ለትውልድ- አገራቸው የተለያዩ ተስፋና ምኞት፣ ስለ ኢትዮጵያ መንግስት የተለያዩ አመለካከት ቢኖራቸውም በየትኛውም ዓለማት ጥግ የሚኖሩ በትውልድ አገራቸው አንድነትና ሉዓላዊነት ተመሳሳይ ሀሳብ ይጋራሉ፡፡ የአገርን ብሔራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅና ለመከላከል ኢትዮጵያውያን በጋራ ይቆማሉ፡፡

ኢትዮጵያን እናድን ግብረ ኃይል በዩናይትድ ኪንግደም ባለፉት ሁለት አመታት የአገራችንን ክብርና ሉዓላዊነት በመከላከል ረገድ ሰፊ ሕዝባዊ ዲፖሎማሲና የፋይናንስ ድጋፎችን በማሰባሰብ የልማት ስራዎችን በማገዝና፣ በሰሜን ኢትዮጵያ በጦርነት የወደሙ ተቋማትን መልሶ ለመገንባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቷል።

በቀጣይም በዩናይትድ ኪንግደም የምንገኝ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች በሙሉ ዛሬም አንደ ትናንቱ የአገርን ክብርና ሉዓላዊነት የመከላከል፣ ወገንን የመርዳትና ልማትን በማስቀጠል ተግባራት ላይ ከአጋር አደረጃጀቶች ጋር በመተባበር በሰፊው እንድንሳተፍ ኢትዮጵያን እናድን ግብረኃይል በዩናይትድ ኪንግደም ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አቶ ዘለዓለም ተሰማ

ኢትዮጵያን እናድን ግብረ ኃይል በዩናይትድ ኪንግደም አስተባባሪ

## የግብረ ኃይሉ ተሳትፎዎች፤

ኢትዮጵያን እናድን ግብረ ኃይል ዩኬ (Defend Ethiopia Taskforce UK) 76 የሚሆኑ ተጽዕኖ ፈጣሪ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላትን ያካተተ እ.ኤ.አ. በ2020 የተመሠረተ ሲሆን ሰፋ ያሉና ለሌሎች መሠል አደረጃጀቶች አርአያና ፈር ቀዳጅ የሆኑ የአገርን ገጽታ የመገንባትና ብሔራዊ ጥቅምን የማስጠበቅ ተግባራትን ሲያከናውኑ ቆይቷል፡፡ ኢትዮጵያን እናድን ግብረ ኃይል ዩኬ (Defend Ethiopia Taskforce UK) ግብረ-ኃይል የዲፕሎማሲና የሎቢ፣ የ"Mainstream Media"፣ የሶሻል ሚዲያ እና የአደረጃጀትና የሎጀስቲክ ቡድኖችን በማደራጀት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ ባለፉት ሁለት አመታት በርካታ እንቅስቃሴዎችን ሲያደረግ ቆይቷል፡፡

❖ ሀገራችን የተመለከቱ ትክክለኛ መረጃዎችን ለዩኬ ማህበረሰብ በማሰራጨት ግንዛቤን እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

❖ ለዩኬ የሥራ ኃላፊዎች፣ የህዝብ እንደራሴዎች እንዲሁም ለአውሮፓ ፓርላማ አባላት በኢትዮጵያ ስላለው እውነታ የሚያሳዩ ጽሁፎች አዘጋጅተው ከማቅረብ አልፎ በአካልም በማግኘት የማስረዳት ሥራዎችን አከናውኗል፡፡

❖ በግብረ- ኃይሉ አስተባባሪነት የማህበረሰቡን አንድነት እና ትብብር ያጠናከሩ ብሎም የትውልድ አገራቸው ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብሩ በአውሮፓ የሚገኙ ዳያስፖራዎችን በማስተባበር ህዝባዊ ድጋፍ ለዩኬ መንግስትና ህዝብ ያስገነዘቡ ደማቅ ሰላማዊ ሰልፎች አካሂዷል፡፡

❖ የዩኬ የመንግስት አካላትና የአውሮፓ ህብረት ትክክለኛ መረጃ እንዲይዙና መንግሥታቱ አገራቸው ኢትዮጵያ የጀመረችውን የለውጥ ሥራ እንዲደግፉ የሚያሳስብ ፔቲሽንና ደብዳቤዎችን ማሰራጨት ችሏል፡፡

❖ የአገራችን ወቅታዊ ጉዳይ ዝርዝር መረጃ የያዘ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁኔታ፣ አንደንድ ምዕራባዊያን በአገራችን ላይ እያደረጉ ያለው ጫና እንዲቆምና የአገራችን ሉዓላዊነት እንዲከበር የሚጠይቅ ደብዳቤ ተዘጋጅቶ ለ8 ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ ለ13 የአውሮፓ አገራትና ለ 9 የናይል ቤዚ አገሮች ማሰራጨት ችሏል፡፡

❖ በተመድ ጸጥታው ምክር ቤት የአገራችንን ጉዳይ በተመለከተ አሉታዊ ውሳኔ እንዳይተላለፍ ደብዳቤ አዘጋጅቶ በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ለአባል አገራቱ አምባሳደሮች ማድረስ ችሏል፡፡

❖ Diaspora Information Center of Ethiopians (DICE) የተሰኘ ብሎግ በመክፈት በትውልድ ሀገራቸው ኢትዮጵያ መሬት ላይ ያለውን እውነታ የሚያሳዩና ለአፍራሽ ዘጋባዎች ምላሽ የሚሰጡ የተለያዩ ጽሑፎች እንዲወጡ አድርጓል።

❖ በተለያዩ አገራት ማለትም በዩኬ፣ በአሜሪካ፣ በደቡብ አፍሪካ እና በካናዳ የሚገኙ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በሰፊው የሚታወቁ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያንን በማካተት Ethiopian Patriots በሚል ስያሜ instagram ላይ ገጽ በመክፈት የኢትዮጵያ እውነታን የማስረዳት ሥራ አከናውኗል፡፡

❖ ግብረ-ኃይሉ የተ.መ.ድ. ሰብዓዊ መብት ም/ቤት በጄኔቫ ስለአገራችን ያሳለፈውን ውሳኔ በተመለከተ ከ Network of Ethiopians in Geneva for Action Taskforce (NEGAT) ጋር በመቀናጀት የተቃውሞ ደብዳቤ በማዘጋጀት ሌሎች 12 በተለያዩ አገራት የሚገኙ የዳያስፖራ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድኖችን በማሳተፍ ለምክርቤቱ አባል አገራት ልኳል፡፡

❖ ለሀገራዊ ጥሪና በግጭት ለተፈናቀሉ ወገኖች ከዳያስፖራው ድጋፍ ማሰባሰብን በተመለከተ "እኔም ለኢትዮጵያ" በሚል መርህ የበይነ-መረብ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም በማዘጋጀት £45,900 (ከ2.2 ሚሊዮን ብር በላይ) በመሰብሰብ ወደ አገር ቤት የተላከ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 21 ቀን 2020 እስከ ጃንዋሪ 10 ቀን 2021 "የገና እና የአዲስ አመት ስጦታ ለወገን እርዳታ" "A Festive Season Appeal to Our People" በሚል መርህ ለተፈናቀሉ ሰዎች ማቋቋሚያ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም በማካሄድ £30,200 (ከ1.5 ሚሊዮን ብር በላይ) ተሰባስቦ ወደ አገር ቤት ልኳል፡፡

❖ እ.ኤ.አ ኖቨምበር 2021 የጫና እና ገጽታ ማጠልሸት የሚቃወምና #NOMORE #በቃ ዘመቻ ኢትዮጵያን እናድን ግብረ ኃይል ከሌሎች ጋር በመቀናጀት ሠላማዊ ሠልፍ አካሂዷል።



❖ ግብረ-ሃይሉ የድጋፍ ሰልፎችን ከማስተባበር አንጻር ከሌሎች ቡድኖችና የኮሚኒቲ አደረጃጀቶች ጋር በመቀናጀት እ.ኤ.አ. ሜይ 3 ቀን 2021 በትግራይ ክልል የተካሄደውን የህግ የማስከበር ዘመቻን፣ የህዳሴ ግድብ ግንባታን እና ምዕራባዊያን በአገራችን እያደረሱት ያለውን ጫናና የሚዲያ ዘመቻ በመቃወም፣ ሜይ 21 ቀን 2021 በአገር ቤት ምዕራባዊያን በአገራችን ላይ እያሳደሩት ያለውን ጫና እንዲያነሱ የሚጠይቅ፣ የዓለማችን ታላላቅ መንግስታት ያካተተው የG7 መሪዎች ስብሰባ በእንግሊዝ Cornwall ከተማ በተካሄደበት ወቅት የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት ከ400 ኪሜ በላይ በመጓዝ ጁን 12 ቀን 2021 የአሜሪካ መንግስት በአገራችን መንግስት ላይ እያደረሰ ያለውን ጫና እንዲያነሳ የተጠየቀበት ታላቅ ሰላማዊ ሰልፎች በዩኬና በስኮትላንድ በአካል እንዲሁም በአየርላንድ በበይነ መረብ አካሂደዋል፡፡

❖ በሌላ በኩል ዳያስፖራው በግሉ ከአገሩ ልማት ጋር ያለው ትስስር ሲታይ በንግድና ኢንቨስትመንት፣ በውጭ ምንዛሪ ፍሰትን በማሳደግ እንዲሁም አገሪቱ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ችግሮች ስትጠቃ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ በመለገስ ረገድ የራሱን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል፡፡

❖ የኢትዮጵያን እውነታን ለአለም ማህበረሰብ ለማሳየትና ብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዓብይ አህመድ የተላለፈውን የእናት አገር ጥሪ አንደንድ አገሮች አምባሰደሮቻቻውን "ኢትዮጵያ ውስጥ ሠላም የለም፣ ለቃችሁ ውጡ" በሚሉበት ወቅት ኢትዮጵያ ላይ የሚነዙ ትርክቶች መሰረተ ቢስና ውሸት ስለመሆናቸው በተጨባጭ ለማሳየት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ወደ አፋርና አማራ ክልሎች በመሄድ በግጭት ምክንያት ለተፈናቀሉ ዜጎች £219,000 (ፓውንድ) የሚገመት አልሚ ምግቦችና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎችን ድጋፍ አድርጓል፡፡ ግብረ-ኃይሉ በአማራና አፋር ክልሎች የወደሙ መሰረተ- ልማቶችን በተለይም የትምህርት ተቋማትን መልሶ ለመገንባት እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡





## 16. የኢትዮጵያ ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን በዩኬ - Ethiopian Sports and Culture Federation in UK (ESCF-UK)

### የኢትዮጵያ ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን በዩኬ ዋና ስራ አስኪያጅ መልዕክት፤

የኢትዮጵያ ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን በዩናይትድ ኪንግደም እ.ኤ.አ. በ2011 የተመሰረተ ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበራዊ ድርጅት (Social Enterprise) ነው። ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ በታላቋ ብሪታንያ በተለይም በለንደን ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ብሎም የኢትዮጵያ ወዳጆችን ዘር፤ ሀይማኖት፤ ፖለቲካ ሳይገድባቸው በአንድ የስፖርትና ባህል ጥላ ሥር ኢትዮጵያዊነት በሰፊው የሚንፀባረቅበትና የሚገናኙበትን መድረክ በመፍጠር ማህበረሰቡን በሰፊው ያሳተፈ፣በስፖርትና ባህላዊ እንቅስቃሴ አማካኝነት ቤተሰባዊ የሆነ አስተሳሰብ በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲሰርጽ ማድረግ የቻለ ብቸኛ ተቋም ወይም ድርጅት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በተለይም ስፖርት ሁሉን አሳታፊ ከመሆኑ የተነሳ ዩናይትድ ኪንግደም አገር ተወልደው ያደጉትን ልጆች የሀገራቸውን ኢትዮጵያ ባህልና ቋንቋቸውን ብሎም ወጉን እንዳይረሱ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ያለና የኢትዮጵያዊነት መንፈስ በማጠናከር የበኩሉን አስተዋፅኦ እያደረገ ያለ ግንባር ቀደም ማህበራዊ ድርጅት ነው።




የኢትዮጵያ ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን የተቋቋመው የኢትዮጵያውያን ቀን በድምቀት በማክበር ለህፃናት እና ወጣቶች የኢትዮጵያን የባህልና እሴቶችን በማስተዋወቅ የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ ለማጠንከር በመሆኑ ፌዴሬሽኑ በህብረተሰቡ ሊበረታታና ሊጠናከር ይገባል። አዳዲስ ክህሎቶች እና ተሰጥኦ (በተለይ በንግድ፣ በአስተዳደር እና በገበያ) ያላቸው ግለሰቦች ፌዴሬሽኑን በመቀላቀልና አባል በመሆን የድርሻችሁን እንዲትወጡ እንጋብዛለን፡፡

አቶ ተሾመ አለሙ ቦጋለ- ዋና ስራ አስኪያጅ

## የፌዴሬሽኑ ተሳትፎዎች፤

የኢትዮጵያውያን ስፖርት እና ባህል ፌዴሬሽን በዩኬ (ESCFUK) ህጋዊ መሰረት ያለው እ.ኤ.አ በ 2011 ዓ/ም ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበራዊ ድርጅት ነው። በዩኬ የኢትዮጵያውያን ስፖርት እና ባህል ፌዴሬሽን ኮሚቴዎች ከፕሮፌሽናል አትሌቶች፣ የቴኒስ ተጫዋቾች፣ አማተር እግር ኳስ ተጫዋቾች፣ ሙዚቀኞች እና የግል ባለሙያዎች የተውጣጡ በጎ ፈቃደኞችን ያቀፈ ሲሆን በመላው እንግሊዝ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን አንድ ላይ የማሰባሰብ የጋራ ግብን ለማሳካት የሚሰሩ ናቸው። ፌዴሬሽኑ ጥብቅ የገለልተኛነት ፖሊሲ አለው፡፡ ይህም ከፌዴሬሽኑ ባህሪያቶቹ ዋናኛ እንደመሆኑ የዳያስፖራ ማህበረሰቡን ሊጠቅም የሚችል ጠንካራ እና አስተማማኝ ድርጅት ያደርገዋል።



ፌዴሬሽኑ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር፣ ስፖርታዊ እና ባህላዊ እንቅስቃሴዎችን በማዳበር እንዲሁም በተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ በማሳተፍ ትልቅ ሚና እየተጫወተ የሚገኝ ማህበራዊ ድርጅት ነው። በተጨማሪም የስደተኞች ኮሙዩኒትን ከዩኬ ማህበረሰብ ጋር ማገናኘት የፌዴሬሽኑ አንዱ ትልቁ አላማ ነው።

❖ በዩኬ የኢትዮጵያውያን ስፖርት እና ባህል ፌዴሬሽን በእንግሊዝ ከኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ውስጥ ግንባር ቀደም ድርጅት በመሆን ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር፣ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን እና ባህላዊ እንቅስቃሴዎችን በማዳበር ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

❖ ድርጅቱ በተለያዩ የዳያስፖራ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል ህብረትና ቅንንጅት በመፍጠርና በማስተባበር ቁልፍ ሚና ተጫውቷል፡፡

❖ ባለፉት አስር አመታት ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ብሎም የኢትዮጵያ ወዳጆችን በአንድ የስፖርትና ባህል ጥላ ሥር በማሰባሰብ፣ የኢትዮጵያ የባህል እሴቶችን ለማስተዋወቅና የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ ለማጠናከር በፌዴሬሽኑ በርካታ ሁነቶች ተዘጋጅተዋል፡፡ የመጀመሪያ አመታዊ ፌስትቫልን እ.ኤ.አ ጁን 2011 በሎንደን (Borough of Harrow) በሂቭ ስታድየም ያካሄደ ሲሆን በቀጣይ አመታትም 9 ፌስትቫሎችን በማካሄድ ኢትዮጵያውያንንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ጾታ፣ ዘር፣ ሃይማኖትና ፖለቲካ ሳይገድባቸው በአንድ ላይ በማሰባባብ ቤተሰባዊ የሆነ አስተሳሰብ በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲሰርጽና የኢትዮጵያ አንድነት እንዲጠናከር አድርጓል፡







## እ.ኤ.አ ከ2011-2022 በፌዴሬሽኑ የተከሄዱ ሁነቶች

| | |
|---|---|
| 2011 | Hive Stadium |
| 2012 | Barnet Stadium |
| 2013 | Linford Christie Stadium |
| 2014 | Burlington Danes Academy |
| 2015 | West Ham Memorial Ground |
| 2016 | West Ham Memorial Ground |
| 2017 | West Ham Memorial Ground |
| 2018 | West Ham Memorial Ground |
| 2019 | Barn Elms, Queen Elizabeth |
| 2022 | New River Sports and Fitness Centre |

## 17. ግሎባል ኖሌጅ ኤክስቼንጅ ኔትወርክ (Global Knowledge Exchange Network – GKEN)

## የግሎባል ኖሌጅ ኤክስቼንጅ ኔትወርክ ሊቀመንበር ፕሮፌሰር አማረ ደስታ መልዕክት፤



በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ ተመራማሪዎች እና ባለሙያዎችን በማቀራረብ አገራችንን በትምህርት መስክ ለመደገፍ ተሳታፊ በመሆናችን የተሰማንን ደስታ ለመግለጽ እንወዳለን። ላለፉት አስራ ሁለት ዓመታትም በትጋት፣ በስራ ወዳድነት እና ያለክፍያ በሚሰሩ በጎ ፈቃደኛ አባላቶቻችን አማካኝነት ግዜያቸዉን እና ሙያቸዉን ያለስስት በመለገስ የኢትዮጵያን የትምህርት ጥራት ለማሻሻል ስንሰራ ቆይተናል። እአአ በ2010 በሎንዶን ከተመሰረትንበት ጊዜ ጀምሮ ተከታታይ የሆኑ የዕውቀት ሽግግር ስራዎች በኢትዮጵያ እና በዉጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች መካከል እንዲከናወን ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር በመቻላችን ደስታ ይሰማናል።

በሰሜናዊም ይሁን በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን በአግባቡ እንዲቀናጁ እና እንዲሰሩ ከተደረገ አገርን መቀየር የሚችል በቂ የሆነ ዕዉቀት እና ችሎታ አላቸዉ ብለን እናምናለን። ይህንን ዕምቅ አቅም በመጠቀም የአገራችንን የትምህርት ጥራት ማሳደግ እንዲቻል የዳያስፖራውን አቅም በማስተባበር እንዲሁም ቀጣይነት ያለዉ ምርምር እና ዉጤታማ አስተሳሰብን በመገንባት ረገድ የበኩላችንን አስተዋጽኦ ለማበርከት በመስራት ላይ እንገኛለን።

የድርጅታችን ተልዕኮም ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ማለትም ተመራማሪዎችን፣ ባለሙያዎችን፣ የልማት ስራተኞችን፣ ፖሊሲ አዉጭዎችንና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ዉስጥ የሚገኙ ባለሙያዎችን እና ሰራተኞችን  በማስተባበርና በማስተሳሰር በፈጠራ በታገዘ ሁኔታ የኢትዮጵያዉያን የኑሮ በዘላቂ ሁኔታ እንዲቀየር  መስራት ነው።

ድርጅታችን የጅማ ዩኒቨርስቲን መነሻ በማድረግና በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ትውድደ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ምሁራንን በማስተባበር በኢትዮጵያ የሚገኙ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን በማገዝ ላይ ይገኛል። ከምስረታችን ጀምሮ በማስተማር፣ በክትትል፣ በምርምር፣ በአማካሪነት እና በትምህርታዊ ሰሚናሮችን፣ በኮንፍረንሶችን፣ በወርክሾፖችን እና በሲምፖዝየሞችን በማዘጋጀት በንቃት በመሳተፍ ላይ እንገኛለን።

በሰሜናዊም ሆነ ደቡባዊ የዓለም ክፍሎች የሚገኙ ዕዉቀቶችን፣ ተመራማሪዎችን እና ባለሙያዎችን  በማስተባበር ዓለም አቀፍ ብሎም አገር አቀፍ ለሆነ የትምህርት ጥራት ዕድገት እንሰራለን። ለዚህም ፈጠራ የታከለባቸው የትምህርት ስትራቴጂዎችን በመጠቀም አካባቢ በቀል ዕውቀቶችን ማምረት የሚችሉ ተመራማሪዎችና ምሩቃንን ማፍራት እንዲሁም የትምህርት ተቋማት ውጤታማ የጥናትና የመማር ማስተማር ከባቢዎች እንዲሆኑ ድጋፍ እናደርጋለን።










## የድርጅቱ ተሳትፎዎች፤

⁜ከ1500 በላይ በዳያስፖራ ያሉ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች የሆኑ የትምህርት ባለሙያዎችንና ተመራማሪዎችንና አስተባብሯል።

⁜ ከአስር በላይ ከሚሆኑ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎችና ተቋማት ጋር የመግባቢያ ስምምነቶችን በመፈራረም የተለያዩ የፈጠራና የዕውቀት ሽግግር ተግባራትን አከናውኗን።

⁜ ዘጠኝ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችንና ወርክሾፖችን አካሂዷል።

⁜ የኢትዮጵያ የዶክትሬትና ማስተርስ አማካሪዎች አካዳሚን በማቋቋምና  ከ1500 በላይ የበጎ ፈቃድ አገልጋይ ምሁራንን በማሰባሰብ በኢትዮጵያ  የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን በመደገፍ ላይ ይገኛል።

⁜ ለጅማ ዩኑቨርሲቲ ከፍተኛ አመራሮች ሶስት ተከታታይ አመታትን የፈጀና በተቋሙ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ስልጠናዎችን ሰጥቷል።

⁜ በመረጃ ሳይንስና በዕውቀት አስተዳደር የሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራም በጅማ ዩኒቨርሲቲ እንዲጀመር ከማድረግ ባሻገር  የሁለት ተማሪዎች ወጪ ሙሉ በሙሉ እንዲሸፈን አድርጓል፤

⁜ ለአዲስ አበባ የቢዝነስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኮሌጅ በቢዝነስ አስተዳደር የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ቀርጾ አቅርቧል፤

⁜ ለከፍተኛ ትምህርት ልህቀት ማዕከል የመረጃ አስተዳደር የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ቀርጾ አቅርቧል፤

⁜ ለባህርዳር ዩኒቨርሲቲ 30 የሶስተኛ ዲግሪ ዕጩ ተመራቂዎች ድጋፍ አድርጓል፤

⁜ በስራው አማካኝነት የሌሎች አፍሪካውያን አገራትን ምሁራን ፍላጎት ከማነሳሳት ባለፈ የጥናትና ምርርም ፕሮጀክቶችን በማካሄድ የኢትጵያና ናይጄሪያ ዩኑቨርሲቲዎች የትምህርት ጥራትን የሚያሻሽል ስራ እንዲያቀርብ ተመርጧል፣

⁜ የኮሮና ቫይረስን መከላከል የሚያስችልና ፈጠራ የታከለበት መፍትሔ የሚያፈላልግ ዓለም አቀፍ ቡድንን አቋቁሟል፤

## በቤልጂየም እና በኔዘርላንድስ የኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አደራጃጀቶች ተሳትፎ

የቤልጂየም ዋና ከተማ ብራሰልስ የአውሮፓ ህብረት እና የአውሮፓ ፓርላማ እንዲሁም በርካታ የዓለም አቀፍ ባንኮችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች መቀመጫ ናት፡፡ ኢትዮጵያ እና ቤልጂየም ከመቶ አመታት በላይ ያስቆጠረ የቆየ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አላቸው። የቤልጂየም እና የኢትዮጵያ ግንኙነት የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1906 በሁለቱ ሀገሮች መካከል የንግድ ስምምነት በተፈራረሙበት ጊዜ ሲሆን፣ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱም እ.ኤ.አ በ1919 መጀመሩን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በብራስልስ የኢትዮጵያ ኤምባሲ የተከፈተው እ.ኤ.አ በ1979 ነው፡፡ ኢትዮጵያ እና ቤልጂየም ጠንካራ የፖለቲካ እና የልማት ትብብር አላቸው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ኔዘርላንድስም ከኢትዮጵያ ጋር የረጅም ጊዜ ግንኙነት ያላት ሀገር ናት። በኔዘርላንድስ መንግስት ለልማት ትብብር ከተመረጡት ስድስት የአፍሪካ ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ በግንባር ቀደምነት የምትጠቀስ ሀገር ስትሆን፣ ኔዘርላንድስም ለኢትዮጵያ የልማት ድጋፍ በማድረግ  ቀዳም ከሆኑ አገሮች አንዷ ናት። የኔዘርላንድና የኢትዮጵያ ግንኙነት በልማት፣ በተራድኦ፣ በንግድ፣ በኢንቨስትመንት እና ግብርና ትብብሮች ላይ ያተኮረ  ነው፡፡ ምንም እንኳን ኔዘርላንድስ ጥብቅ የኢሚግሬሽን ፖሊሲ ቢኖራትም  ወደ 27 ሺህ የሚጠጉ  ኢትዮያውያንና ትውልደ ኢትትዮጵያውያን ይኖሩባታል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ብራሰልስ ሚሲዮን ከተወከለባቸው ሀገሮች በቤልጂያምና በኔዘርላንድስ  የዲያስፖራ አባላት በተለያዩ አደረጃጀቶች በመደራጀት  ባላቸዉና ባካበቱት ሀብት፣ እውቀት፣ ሙያና ልምድ ከትውልድ አገራቸው ጎን በመሆን በተደራጀ አግባብ የሚጠበቅባቸዉን የዜግነት ግዴታቸውን እየተወጡ የሚገኙ በርካታ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች አሉ፡፡ ለአብነት ያህልም ዲፌንድ ኢትዮጵያ ቤልጂየም ቻፕተር፣ ኮሚኒቲ ማህበራት፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አስተባበረ ኮሚቴ፣ የአልማ ህብረት ለልማት ማህበር፣ የሉቅማን የሙስሊሞች ማህበር ይገኙባቸዋል፡፡ በኔዘርላንድስም  ዲፌንድ ኢትዮጵያ ኔዘርላንድስ ቻፕተር፣ ኮሚኒቲ ማህበራት እና የአዲቮከሲና ማህበራዊ ድጋፍ አስተበበሪ ኮሚቴ መጥቀስ ይቻላል፡፡

በቤልጂያምና በኔዘርላንድስ  ካሉ የደያስፖራ አደረጃጀቶቹ መካከል በቤልጂየም የአድቮኬሲና ማህበራዊ ድጋፍ አስተበበሪ ኮሚቴ እና  በኔዘርላንድስ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አስተባበረ ኮሚቴ ግንባር ቀደም አደረጃጀቶች ናቸው፡፡



## በቤልጂየም የአድቮኬሲና ማህበራዊ ድጋፍ አስተበበሪ ኮሚቴ
## በቤልጂየም የአድቮኬሲና ማህበራዊ ድጋፍ አስተበበሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ መልዕክት፤



ባለፉት 15 ዓመታት በአገራችን ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተወግዶ ለውጥ እንዲመጣ ከሁሉም ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን ስንታገል ቆይተናል፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት ደግሞ በጦርነቱ ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ ለማሰባሰብ፣ በአገራችን ላይ የተከፈተውን ፕሮፖጋንዳ ለመመከት የአለም መንግስታት እውነታውን እንዲያውቁ የማድረግ፣ በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ በመቅረብ በአገራችን ላይ የተከፈተውን ፕሮፖጋንዳ ለመቀልበስ ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን። በአውሮፓ እንዲሁም በቤልጅየም ደረጃ በተደጋጋሚ ሰላማዊ ሰልፎችን ያማካሄድን ሲሆን፣ በአጠቃላይ  በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ዳያስፖራውን የማስተባበር ሰራዎችን በማከናወን ላይ እንገኛለን፡፡

በቀጣይም ኢትዮጵያ አገራችን ሰላሟ እና ብልጽግናዋ እንዲረጋገጥና በኢኮኖሚ ከፍ ብላ የህዝቧ ኑሮ እንዲሻሻል አገራችን  በምትፈልገን ቦታ ሁሉ ለማገልገል ዝግጁ መሆናችንን ማረጋገጥ እወዳለሁ።

አቶ ገአስ አህመድ

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

❈ በግጭትና በተለያዩ ተፈጥሮአዊ ችግሮች ሳቢያ ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎች ለማቋቋም የዳያስፖራ ማህበረሰብን በማስተባበር ድጋፍ የማሰባሰብ ተግባራትን አከናውኗል።

❈ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

❈ የተለያዩ የድጋፍ ሰልፎችን የማስተባበር ስራ ሰርቷል፡፡

❈ የታላቁ ጥሪ ጉዞ ወደ ሀገር ቤት እና ከኢድ እስከ ኢድ ጉዞ ወደ ሀገር ቤት ጥሪዎችን የማስተባበሪ ስራ አከናውኗል፡፡

❈ በአገራችን ከተከሰተው ግጭት ጋር በተያያዘ ምዕራባዊያን በአገራችን ላይ የያዙትን የተዛባ አቋምና የምዕራባዊያን የሀሰት ሚዲያ ዘመቻ በመቃወም እየደረሰ ያለውን ጫና እንዲነሳ የአድቮኬሲና ማህበራዊ ድጋፍ በተለያዩ ወቅት ጠይቋል፡፡

❈ ችግር ያጋጠማቸውና  በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወደ ሀገራቸው የሚመለሱ ወገኖች እንዲሁም በውጭ ሀገር በተለያዩ ምክንያቶች ሕይወታቸው የሚያልፍ  ዜጎች ወደ ትውልድ ሀገራቸው ለመሸኘት ድጋፎችን የማሰባሰብ በጎ ተግባራትን ሲሰራ ቆይቷል፡፡

❈ በብራስል ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጋር በመተባበር ለተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ዳያስፖራውን የማስተባበር ስራ ተሰርቷል፡፡



## 19. በኔዘርላንድስ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አስተባባሪ ኮሚቴ
## በኔዘርላንድ የኢትዮጵያ ህዳሴ ምክር ቤት የስራ አስፈጻሚ ከሚቴ መልዕክት፤



በኔዘርላንድ የህዳሴ ምክር ቤት የተቋቋመው እ.ኤ.አ በ2018 ሲሆን፣ የህዳሴ ምክር ቤቱ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሃብት የማሰባሰብ ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

አርማችን  እና ለወገኖቻችን ከድህነት መውጫ ተስፋችን የሆነው የህዳሴ ግድብ የእኛ የሁሉም ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ሙያዊና የገንዘብ ድጋፍ ስለሚያስፈልገው እናምናለን። ኢትዮጵያውያን ዓላማችን ህዳሴና ተመሳሳይ አገራዊ ፕሮጀክቶች አልቀው የአካባቢ ደህንነት ጥበቃን የማያቃውሱ ፋብሪካዎች፣ ኢንደስትሪዎች እንዲሁም በቴክኖሎጂ የታገዙ ሰፋፊ የእርሻ ስራዎች ተስፋፍተው፣ ለወጣቶች ስራ እና ለአረጋውያን መጦሪያ ሳይጎለን ማየት ነውና ድጋፋችንን አጠናክረን እንቀጥል ስል መልዕክቴን አቀርባለሁ፡፡

ዶ/ር አዜብ አምሃ

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

- ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ላይ አገራችን ከምታካሄደው ድርድር ጋር በተያያዘ በግብጽና ሱዳን የሚራመዱ አፍራሽ ፕሮፖጋንዳዎችን በመከታታል ምላሽ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

- የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ድርድርን በተመለከተ ምዕራባዊያን አገሮች በተለይም የአሜሪካ መንግስት የሚያራሚደውን አድሎአዊ አቋም በመቀወምና ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ የማጋለጥ በርካታ ስራዎችን ሰርቷል፡፡

- ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የዳያስፖራ ማህበረሰቡ በቦንድ ሽያጭና በስጦታ የሚያደርገውን ድጋፍ በማስተባበር የላቀ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

- ያልተገባ የውጭ ጫናዎችን በመቃወም በግል በቲዊተር እንዲሁም በቡድን በተቋቋመው አዲቮከሲ ቡድን በኩል በአውሮፓ ዩኒየን ውስጥ ለተለያዩ ኮሚሽኖች፤ የኮሚሽን አባላት እና የተለያዩ ቢሮዎች፤ እንዲሁም በኔዘርላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ለፓርላማ አባላት የኢትዮጵያን እውነት የሚያስረዱ በርከት ያሉ ደብዳቤዎችን በተለያዩ ጊዜያት በማስገባት እና በመከታተል ሲሰራ ቆይቷል፡፡

- የኔዘርላንድ የቴለቪዥን ቻናሎች እና ጋዜጦች እንዲሁም BBC በተሳሳተ መረጃ የአገራችንን ገጽታ የሚጎዳ ስራ በሚዘግቡ ጊዜ ይህን እንዲያስተካክሉ በመጠቆምና በማስረዳት ወሳኝ ትግል ተካሄዷል፡፡

- የኢትዮጵያ ወዳጅ የሆኑ የኔዘርላንድ አገር ሰዎች ለወገኖቻቸው የኢትዮጵያን እውነት እንዲያሳውቁ እና ያለአግባብ አገራችን ኢትዮጵያ የሚደርስባትን ፍረጃ እና ጫና እንዲመክቱ የማስተባበር ስራ ተከናውኗል፡፡

- የጣልቃገብነት፣ የሀሰት ዘመቻ እና ገጽታ ማጠልሸት የሚቃወም በብራስልስ እና በሄግ_ኔዘርላንድ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና አጋሮችን በማስተባበር ሰላማዊ ሰልፍ በማዘጋጀት ድምጻቸውን አሰምተዋል፡፡

- በኔዜርላንድ የትውልደ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ማህበር እንዲመሰረት በማድረግ ሴቶች እህቶች በዝቅተኛ ገቢ ራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩ ቋሚ የሆነ መተዳደርያ የሚሆናቸውን የስራ እድል ለማመቻቸት፣ የኢትዮጵያን ባህል፤ ቋንቋ እና ትውፊት ለተተኪ ትውልድ ለማስተዋወቅ እና በአገራቸው ጉዳይ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማቸው ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡

## በጣሊያን አገር የላቀ አበርክቶ እያደረጉ የሚገኙ የኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አደረጃጀቶች

በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል ኦፊሴላዊ ዲፕሎማቲክ ግንኙነት የተጀመረው እ.ኤ.አ በ1889 ሲሆን ይሄም ጣሊያን በኢትዮጵያ ኤምባሲዋን በመክፈት የመጀመሪያ ያደርጋታል፡፡ ይሁንና ይህ ኦፊሴላዊ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከመመስረቱ በፊት አጼ ሚኒሊክ የሸዋ ንጉስ ሆነው አንድ የጣሊያን ሚሽን ኢትዮጵያ ውስጥ መጥቶ ከአንኮበር ብዙም ሳይርቅ ለመታፈፊያ የሚባል አካባቢ መመስረቱንና ከዚያም ሌላ የጣሊያን መልዕክተኛ በአንኮበርና በእንጦጦ በአጼ ሚኒሊክ ችሎት ውስጥ ያገለግል እንደነበርና አጼ ሚኒልክ ዋና ከተማውን ወደ አዲስ አበባ ሲያዞሩም ይኸው መልዕክተኛ አብሮ መዛወሩን የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ። ይኸው ግንኙነት ጣሊያን ኢትዮጵያ እስከ ወረረችበት እስከ 1935 ድረስ ቆይቶ በወረራው ምክንያት የተቋረጠ ሲሆን፣ እንደገና የሁለተኛ የዓለም ጦርነት በፋሽዚም ተሸናፊነት ከተፈጸመ በኋላ በጠላትነት አመዝኖ የነበረው የሁለቱ ሃገራት ግንኙነት ተለውጦ ጤናማ ግንኙነት በመጀመሩ እ.ኤ.አ በ 1952 ዓ/ም በሮም የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሊከፈት ችሏል።

በጣሊያን ቁጥራቸው ከ 7 እስከ 9 ሺህ በላይ የሚገመቱ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚገኙ ሲሆን፣ ከ20 በላይ በሚሆኑ አደረጃጀቶች በመሰባሰብ በልማት እና አድቮኬሲ ስራዎች የትውልድ አገራቸውን በመደገፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ  በንቃት ከሚሳተፉ አደረጃጀቶች መካካል የኢትዮጵያ ፍቅርና አንድነት መረዳጃ ማህበር እና የሞዴና እና የአካባቢዋ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን የበጎ አድራጎት ማኅበር ይገኙባቸዋል። ዲፌንድ ኢትዮጵያ በጣሊያን እና ወገን ለወገንም የተሻለ አፈጻጸም ካላቸው አደረጃጀቶች መካከል ናቸው። በተጨማሪም ኢትዮ-ሮማ ባህልና ስፖርት ማህበር፣  በግሪክ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ማህበር፣ በቶሪኖ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ማህበር፣ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ማህበር በሉምባርዲያ፣ በባሪ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ማህበር፣ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ በሳይፐረስ፣  በፍሬንሴ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ማህበር፣  የኢትዮጵያ ፍቅርና መረዳጃ ማህበር በፓርማ እንዲሁም በሞዴና የኢትዮጵያ መረዳጃ ማህበር  ሚሲዮኑ በሚሸፍናቸው አካባቢዎች የሚገኙ የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው አደረጃጀቶች ናቸው። እነዚህ አደረጃጀቶች በጣሊያን የኢፌዲሪ ኤምባሲ ጋር በመቀናጀት በህዳሴ ግድብ፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች ድጋፍ እና በአድቮኬሲ ስራዎች ንቁ ተሳትፎ በማድረግ  ላይ ይገኛሉ፡፡

## 20. የኢትዮጵያ ፍቅርና አንድነት መረዳጃ ማህበር
## የኢትዮጵያ ፍቅርና አንድነት መረዳጃ ማህበር ሊቀ መንበር መልእክት፤



የኢትዮጵያ ፍቅርና አንድነት መረዳጃ ማህበር እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 01 ቀን 2020 የተመሰረተ ሲሆን፣ ከተመሰረተ አጭር ጊዜ ቢሆነውም በሀገራችን በተለያዩ ምክንያቶች ችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ለመደገፍ ጥረት የሚያደርግ እና በሰብአዊነት ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ማህበር ነው። በቀጣይም ማህበሩን የበለጠ በማጠናከር በሀገራችን እርዳታ ለሚሹ ዜጎች አቅም በፈቀደ መጠን ለመድረስ ጠንክረን እንደምንሰራ ያለኝን እምነት እገልጻለሁ።

አቶ ሮቤል አስፋው ተገኝ

የኢትዮጵያ ፍቅርና አንድነት መረዳጃ ማህበር ሊቀ መንበር

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

◈ ኮቪድ-19 በተከሰተበት ወቅት 8,200 ዮሮ ከአባላቶች በማሰባሰብ በፓርማ ከተማ ለሚገኘው ሆስፒታል በመርዳት በችግሩ ጊዜ ከጣሊያኖች ጎን መሆኑን ማሳየት ችሏል።

◈ በአገራችን ለተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከላከያ እንዲሆን 10,200 ዩሮ የገንዘብ ድጋፍ አድጓል።

◈ ከ35,000 ዩሮ በላይ የሚያወጣ አንድ ኮንቲኔር ሙሉ የህኪምና እና ሌሎች ቁሳቁሶችን በማሰባሰብ በግጭት ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት የአጣዬ ከተማ  ድጋፍ አድርጓል።



◈ በተለያዩ የአገራችን አከባቢዎች በትምህርት መሳሪያዎች  እጦት ትምህርታቸውን መቀጠል ላልቻሉ 205 ተማሪዎች 100,500 ብር የሚያወጣ የትምህርት መሳሪያዎችን በማሟላት ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ችሏል።

◈ 23,000 ዩሮ የገንዘብ ድጋፍ በማሰባሰብ በጦርነት ምክንያት የምግብ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው የአፋር ክልል ነዋሪዎችን ረድቷል።

◈አንድ ዳያስፖራ ለአንድ ቤተሰብ በሚል ለተጀመረው ፕሮግራም 13,900 ዩሮ እንዲሁም 253,900 ብር በማሰባሰብ  በአፋር ክልል በጦርነት ንብረት ለወደመባቸውና ለተዘረፈባቸው 82 ቤተሰቦች ለእያንዳንዳቸው  ሶስት ሶስት ፍየሎችን /246 ፍየሎች/ እንዲያረቡ እና ቤተሰባቸውን በኢኮኖሚ እንዲደግፉ አድርጓል።





## የሞዴና እና የአካባቢዋ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን የበጎ አድራጎት ማኅበር
## የሞዴናና የአካባቢዋ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን የበጎ አድራጎት ማኅበር መልእክት፤

የሞዴናና የአካባቢዋ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን የበጎ አድራጎት ማኅበር እ.ኤ.አ ሜይ 07/2019 የተመሰረተ ሲሆን፣ በተለያዩ ምክንያቶች ችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ለመደገፍ ጥረት ላይ ይገኛል። በቀጣይ በጣሊያን አገር ከሚገኙ ሌሎች ተመሳሳይ አላማ ካላቸው ድርጅቶችና ማህበራት ጋር በመቀናጀት በአገራችን ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ዜጎች ለመርዳት ጠንክረን እንደምንሰራ ያለኝን እምነት እገልጻለሁ።

አቶ ዘውዱ ደምሰው ዘለቀ
የሞዴናና የአካባቢዋ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን የበጎ አድራጎት ማኅበር

## የማኅበሩ ተሳትፎዎች፤

❈ በሃገራችን ተከስቶ በነበረው የኮቪድ -19 ወረርሽን ወቅት 4,000 ዩሮ ከአባላቶች በማሰባሰብ ለሀገራችን የኮቪድ-19 መከላከያ ስራዎች የሚውል የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።

❈ እ.ኤ.አ 2022 ሌሎች የእርዳታ ድርጅቶችን በማስተባበር እንዲሁም የትራንስፖርት ወጪውን ከአባላቱ በማሰባሰብ ሙሉ የህክምና መሳሪያ የተገጠመለትና ግምቱ ከ12 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ አምቡላንስ ለዘውዲቱ ሆስፒታል አበርክቷል።

## በጀርመን የላቀ አበርክቶ እያደረጉ የሚገኙ የኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አደረጃጀቶች

የኢትዮጵያና ጀርመን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። እ.ኤ.አ. በማርች 1905 የሁለቱ አገራትን የዲፕሎማሲያዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ለማፋጠን ያስችላል ተብሎ የታሰበው የወዳጅነት ስምምነት ተፈርሟል። ቀጥሎም እ.ኤ.አ. 1907 የኢትዮጵያ ንጉስ የነበሩት ዳግማዊ ሚኒሊክ ለጀርመን መንግስት ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን የሚሆን መሬት በአአዲስ አበባ ሰጥተዋል።

የኢትዮ-ጀርመን ግንኙነት በፖለቲካ መስክ መግባባት የሚታይበት ሲሆን፣ አገራችን የጀርመን የልማት ትብብር የትኩረት አገር ናት። በንግድና ኢንቨስትመንት መስክ ያለው የሁለትዮሽ ግንኙነትም መሻሻል እያሳየ ይገኛል። የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር በየጊዜው የሚካሄዱት የከፍተኛ ባለስልጣናት ጉብኝቶች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ይታመናል።

በጀርመን አገር ከ30,000 ሺህ በላይየሚሆኑ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከ40 በላይ በሚሆኑ አደረጃጃቶች በመሰባሰብ በልማት እና አድቮኬሲ ስራዎች የትውልድ ሃገራቸውን በመደገፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ በንቃት ከሚሳተፉ አደረጃጀቶች መካካል የኑረንበርግ ኢትዮጵያውያን ባሕል ማህበር እና የኢትዮጵያውያን መገናኛ ድልድይ በሽቱትጋርት አደረጃጀቶች በበርሊን ከሚገኘው የኢፌዴሪ ኤምባሲው ጋር በመቀናጀት በህዳሴ ግድብ፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች ድጋፍ እና በአድቮኬሲ ስራዎች ላይ አስተዋጽኦቸውን በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያውያን የውይይትና የትብብር መድረክ፣ የጀርመንና የአካባቢው ሀገሮች የዳያስፖራ በፐሊክ ዲፕሎማሲ ቅንጅት፣ የህዳሴ ም/ቤት፣ አውግስበርግ የኢትዮጵያ ማህበር፣ የኢትዮጵያ ማህበር በሙኒክ፣ በቼክ የኢትዮጵያውያን ማህበር፣ ኢትዮ ፖሊሽ ሰላም ማህበር፣ የኢትዮጵያ የባህል ማህበር ሀምቡርግ እንዲሁም በጀርመን የኢትዮጵያውያን የጤና ባለሙያዎች ማህበርም የተሻለ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኙ አደረጃጀቶች ናቸው።





## 22. የኑረንበርግ ኢትዮጵያውያን ባሕል ማህበር የኑረንበርግ ኢትዮጵያውያን ባሕል ማህበር ሊቀመንበር መልእክት፤

**የኑረንበርግ ኢትዮጵያውያን ባሕል ማህበርን ወክዬ መልክት እንዳስተላልፍ እድሉን ስላገኘው የተሰማኝን ክብር ለማቅረብ እንወዳለው።**



የኑረንበርግ ኢትዮጵያውያን ባሕል ማህበር አባላት በነጻነት ራሳቸውን አደራጅተው ወገናቸውንና አገራቸውን ለማገልገል ተነሳሽነትና አቅም ያላቸው፣ ምኞትና ፍላጎታቸው የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ስኬትና ከፍታ ብቻ የሆነ አገር ወዳድ ዜጎች ተሰባስበው የፈጠሩት አደረጃጀት ነው። በመሆኑም ማህበራችን በአገራችን በተለያዩ ምክንያቶች ችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ለመደገፍ ጥረት የሚያደርግ እና በሰብአዊነት ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ሲሆን፤ በቀጣይም ማህበሩን የበለጠ በማጠናከር በአገራችን እርዳታ ለሚሹ ዜጎች አቅም በፈቀደ መጠን ለመድረስ ጠንክረን እንደምንሰራ ያለኝን እምነት እገልጻለሁ።

ኢትዮጵያዊነት ይለምልም!

ትርፌ ፍቃዱ
የኑረንበርግ ኢትዮጵያውያን ባሕል ማህበር ሊቀ መንበር

እኤአ በ1980ዎቹ መጨረሻ በስደት ከአገራቸው ወጥተው በኑረንበርግ ከተማና ዙሪያዋ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቁጥር እየጨመረ መምጣት ጋር ተያይዞ በማያውቁት አዲስ ዓለም የሚሠማቸውን ብቸኝነትና የባይተዋርነት ስሜት ለማሸነፍ እርስ በርስ እየተፈላለጉ ይጠያየቁም ነበር። ምንም እንኳን ይህ በትንሹም ቢሆን የዘመድ አዝማድንና የወገንን ናፍቆት ቢያስታግስም ዕለት ተዕለት ለሚገጥሟቸው ዘርፈ ብዙ ችግሮች ግን ደጋፊና አይዞህ የሚል አልነበራቸውም። በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ አንዲት ኢትዮጵያዊት ስደተኛ ከመሃከላቸው በሞት ተለየች። በዚህ የሃዘን ወቅት የሷን ቤተሠቦች ለማስተዛዘን የተገናኙት ኢትዮጵያውያን እንዲህ አይነቱንና መሠል የጋራ ችግሮች በተናጠል ከመጋፈጥ ተሠባስበን ብንደራጅ ይሻላል የሚል ሃሳብ አነሱ። ይህ ሃሳብ ትልቅ ድጋፍ በማግኘቱም ሥለ ምሥረታው ለመምከር ለመጀመሪያ ጊዜ ተሠባሠቡ። እንዲህ የተጀመረው ምክክር ለሶስት ወራት ቀጥሎ እኤአ በዲሴምበር ወር 1990 የመጀመሪያው የኑረንበርግ ኢትዮጵያውያን ድርጅት በቀዳሚ ሥሙ የኑረንበርግና አካባቢው ኢትዮጵያውያን መገናኛ ማህበር በሚል ስያሜ ተመሰረተ።

## የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

ማህበሩ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ዓባላቱ ቅድመ ሥደት ማንነታቸው ሳያግዳቸው በኢትዮጵያውነት ጥላ ሥር ብቻ ተሠባስበው እዚህ ለሚገጥሟቸው ማህበረሰባዊ ተግዳሮቶችና ክንውኖች የመተባበሪያ መድረክ ለመሆን ሢጥር ቆይቷል። በተለይ በመጀመሪያዎቹ 12 ዓመታት ትኩረት ያደርግባቸው የነበሩትን እንቅስቃሴዎች ለአብነት ያህል ለማንሳት የታመሙ መጠየቅና አይዞህ ማለት፣ ዘመድ የሞተበትን በማስተዛዘን፣ በሞት የሚለዩንን ወገኖች አሥከሬን ወደ አገር ቤት በመላክ ወይንም እዚሁ በክብር እንዲቀበር በማድረግ፣ የታሠሩ ወንድምና እህቶች በመጠየቅና በማበረታታት፣ የበጎ ተግባር አድማሱን እስከ አገር ቤት ድረስ በማስፋት የጎዳና ተዳዳሪ ህጻናትን ከመደገፍ እስከ ለሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች የሞራልና ይፋይናንስ ድጋፍ ማሠባሠብን ያካተተ ወገናዊና ማህበረሠባዊ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል። የስደተኛ ኢትዮጵያውያን ጥያቄዎች ከባለሥልጣኑ መ/ቤት በጎ ምላሽ ያገኙ ዘንድ በየጊዜው ሠላማዊ ሠልፎችን በማዘጋጀት፣ የቢሮ ሃላፊዎችን ቀርቦ በማነጋገርና ከሌሎች የመብት ተሟጋች ድርጅቶች ጋር ተባብሮ ጫና በመፍጠር የብዙ ወገኖች የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል አስተዋጾ አድርጓል።

ከዚህ ጎን ለጎን ማሕበራችን በሚያገኛቸው መድረኮች ሁሉ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ታሪክ፣ ባሕልና የኑሮ ዘይቤ ለሚንኖሩበት ማህበረሠብ ለማስተዋወቅ በየከተማዎቹ በሚዘጋጁ ህብረ ባህል ዝግጅቶች በመሳተፍ፣ ምርኩዝ የተሠኘ መጽሄት በየሶስት ወሩ በማሳተም የሥነ ጽሁፍ ሥራዎችን በመደገፍ፣ በስፖርቱም በኩል በከተማቸው ኤፍ ሲ ዋሊያ የተሠኘ የእገር ኳስ ክለብ እንዲቋቋም ድጋፍ በማድረግ አሁን ላይ ወሳኝ የአውሮፓ ኢትዮጵያውያን መሠባሠቢያ የሆነው የስፖርትና ባሕል ፌዴሬሽን እዚህ ደረጃ እንዲደርስ የበኩሉን አስተዋጾ አበርክቷል። በፖለቲካውም መሥክ ማህበራችን የሕዝብ አጋርነቱን ለማሳየት ለአገራችን ችግሮች መፍትሄ አለን የሚሉ ታላላቅ ምሁራንና የመብት ተሟጋቾችን እየጋበዘና የማህበረሠብ ማንቂያ መድረኮችን እያዘጋጀ ከኢትዮጵያውያን ጋር እንዲገናኙ በማድረግ አዎንታዊ ተጽዕኖ ለመፍጠር ጥረት ያደርግ ነበር። እንደየጊዜው አመራሮቹ ብቃትና ችሎታም ለተመሠረተበት ራዕይ ከአካባቢው አልፎ ከአቻ ማህበራት ጋር በፍራንክፈርትና ሆላንድ ላይ በመገናኘት በጀርመንና በአውሮፓ ደረጃ የኢትዮጵያውያን ሕብረት እንዲፈጠር ጥረት አድርጓል።

ዓመታት እያለፉ ዓመታት ሲተኩ የማህበሩ ዓባላትና በከተማው ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ሕይወት እየተለወጠ መጣ። ብዙዎች ቤተሠብ መሠረቱ፣ የመጀመሪያዎቹ ትውልደ ኑረንበርግ ኢትዮጵያውያን ታዳጊዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። ከዚህ የሂደት ክስተት ጋር ኮሚኒቲውን ማጣጣም ስለነበረብን ከሌሎች አገራት ዜጎች የቀደመ ልምድ ትምህርት በመውሰድ እዛው ለተወለዱ ህጻናት በማንነታቸው እንዲኮሩ፣ ሥለኢትዮጵያ የበለጠ አዎንታዊ ግንዛቤ እንዲይዙ ለማድረግና ማህበረሠባዊ ውህደት ለማገዝ የተለያዩ ዓመታዊና ወርሃዊ የመገናኛ ፕሮግራሞች በማዘጋጀት፣ ባሕላዊና ባሕል ተሻጋሪ ፕሮጀክቶችን በመንደፍና በመተግበር፣ የታዳጊዎችና የሕጻናት ፕሮጀክቶች በመቅረጽ ልጆች ሁለንተናዊ ድጋፍ እንዲያገኙና ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች እንዲቀራረቡ ስንሰራ ቆይተናል። በተለይ ደግሞ በ2018 በአገራችን የተፈጠረውን አዎንታዊ ለውጥ ተከትሎ ከዛ በፊት ስናደርግ የነበረውን ሠብዓዊነት ላይ ብቻ ያጠነጠነ የድጋፍ እንቅስቃሴ አድማስ በማስፋት ለመሠረታዊ የልማት ሥራ ፕሮጀክቶች ጭምር ድጋፍ ማድረግ የሚቻልበት ሕጋዊ ማዕቀፍ በማዘጋጀት እኤአ ከ 2018 ጁላይ ወር ጀምሮ የኑረንበርግ ከተማን አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በማስተባበር ለአገራዊ ፕሮጀክቶችና በጦርነት ለተጎዱ ወገኖቻችን ድጋፍ የሚውል በድምሩ 90,954,38 (ዘጠና ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አራት ከ ሰላሳ ሥምንት ሣንቲም) አይሮ ድጋፍ ማድረግ ችለዋል፡፡








❖ የአደረጃጀቱ የስፖርት ማህበር ኤፍ ሲ ዋሊያ ጋር በመተባበር እኤአ 2011 ከጁላይ 29 እስከ ጁላይ 31 በከተማቸው የተዘጋጀው 9ኛው የአውሮፓ ኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ፌስቲቫል






❖ በሆላንድ አገር በ 2013 በጋ ወራት በተካሄደው 11ኛው የአውሮፓ ኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ፌስቲቫል ላይ በባህል አልባሳት ያሸበረቁ የዚያን ጊዜ ታዳጊዎች የባህል እንቅስቃሴዎቻችንን አጥንተው ያካሄዱት የባህላዊ ዳንስ ትእይንት




❖ የቴዎድሮስ ራዕይ የተሠኘውን በታዋቂ የቲያትር ጥበብ ባለሙያዎች የተከወነ ተውኔት በ 2018 ዓም ወደ ወደ ከተማቸው ጋብዘው እንዲታይ እና ስለ አገራው ባህል እንዲያውቁ መደረጉ






❖ በከተማቸው በየዓመቱ በሚካሄደው የአፍሪካ ፌስቲቫል ላይ የኢትዮጵያ የባህል አምባሳደሮች በመሆን አገራቸውን ወክለው ባሕላቸውን ሲያስተዋውቁ







❖ የተለያዩ የአዋቂና የታዳጊ ህጻናት ዝግጅቶች፣ ዎርክ ሾፖችና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽና በመተግበር ሕጻናት ከጅምሩ ብዝሃ ማንነትን እንዲለማመዱ፣ ለፈጠራ ፍላጎት እንዲያድርባቸውና በትምህርታቸውም እንዲጎብዙ ለማድረግ ባህላችውን የማስተዋወቅና ከሌሎች ጋር የማዛመድ ሥራ ሲያከናውኑ




## 23. የኢትዮጵያውያን መገናኛ ድልድይ በሽቱትጋርት



## የኢትዮጵያውያን መገናኛ ድልድይ በሽቱትጋርት ሊቀ መንበር መልክት

የኢትዮጵያውያን መገናኛ ድልድይ በሽቱትጋርት ወክዬ መልክት እንዳስተላልፍ እድሉ ስለተሰጠን የተሰማኝን ክብር መግለጽ እንወዳለው።

አገራችን ኢትዮጵያ ለረዥም ዘመናት ነጻነቷን አስከብራ የኖረች ጥንታዊ አገር ናት። ኢትዮጵያ በተለይ ባለፉት አራት አመታት ውስጣዊ እና ውጫዊ ጫናዎችን በመቋቋም ከፍተኛ የልማት ስራዎችንና ትልልቅ የግንባታ ስራዎችን እያከናወነች ትገኛለች፡፡ ከነዚህ ውጤታማ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የህዳሴው ግድብ 3ኛው ውሃ ሙሌት እና ሃይል ማመንጨት ስኬታማ ስራዎችን ጨምሮ፣ ለተከታታይ ዓመታት የተከናወነው የአረንጓዴው አሻራ ችግኝ ተከላ ይገኙበታል።

ኢትዮ ብሪጅ ሽቱትጋርት (የኢትዮጵያውያን መገናኛ ድልድይ በሽቱትጋርት) ከህዝባችን ጎን በመሆን የተጀመሩት የልማትና ትልልቅ የግንባታ ስራዎች ከፍጻሜ እንዲደርሱ፣ በብሄራዊ ጥቅሞቻችን በተጻራሪ ጎን የቆሙትን አካላት ጫና በመቋቋም ከአገራችንና ከህዝባችን ጎን መቆማችንን ማረጋገጥ እወዳለሁ።

ኢትዮጵያ ሰላሟ ተጠብቆ በአንድነትና በፍቅር ትኖራለች።

በላይ ንጉሴ

የኢትዮ ብሪጅ ሽቱትጋርት ሊቀመንበር

ማህበሩ እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር በ1997 ዓ/ም ወይም  እነደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ2007 ዓ/ም ከሽቱትጋርትና አካባቢው በተሰባሰቡ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ በጀርመን አገር ህግ መሰረት የተቋቋመ ህጋዊ ማህበር ሲሆን፣ ዓላማውም ማንኛውንም የፖለቲካ ድርጅት ሳይወክል፣ በአገራችን ውስጥ ለሚፈጠሩ ማህበራዊ ችግሮች፣ አስፈላገ የሆነውን የሞራል፣ የማቴርያልና የገንዘብ እርዳታ በማድረግ የአገራችንና የህዝባችንን ዘርፈ ብዙ ችግር ለመቅረፍና ወገናችንንም ለመርዳት ነው።

የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

◈ በኢትዮጵያ ላይ የሚደረጉ ያልተገቡ ጫና እና የሙብት ጥሰቶችን በመቃወም ማህበሩ  በተለያዩ ጊዜያት ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ፣ ሻማ በማብራት፣ ፔትሽን በመፈረም ብሄራዊ ጥቅምን የማስጠበቅ ስራ በሰፊው ሲያከናውን ቆይቷል፣

◈ በጀርመን አገር የተወለዱና እዚያው በማደግ ላይ ላሉ ልጆች ቋንቋቸውንና ባህላቸውን እንዳይረሱ በማስተማር ላይ ይገኛል፤

◈ በወጣት ችግረኞች መርጃ ማህበር በኩል በኢትዮጵያ ለሚገኙ አሳዳጊ ለሌላቸውና ለችግረኛ ህጻናት በቋሚነት በማህበሩ አባላት ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፤

◈ ለአገርና ለወገን ድምጽ ለሆኑ የሚዲያ አካላት እና ለተፈናቀሉ ወገኖች ከፍተኛ ድጋፍ ተደርጓል፤
◈ ኢትዮጵያውያን በሳውዲ አረቢያ መንግስት በግፍ እንዲወጡ መደረጉን ተከትሎ ከፍተኛ የገንዘብ እርዳታ በማስተባበር ድጋፍ በማድረግ ወደ እናት አገራቸው እንዲመለሱ ድጋፍ ተደርጓል፤

◈ ሽቱትጋርትና አካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር በጦርነትና በተፈጥሮ አደጋ ለተጎዱ ወገኖቻችን  ከፍተኛ የገንዘብና የቆሳቁስ እርዳታ ተደርጓል፣

◈ የሽቱትጋርትና አካባቢው ኢትዮጵያውያናና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር የውጭ ምንዛሪ እንዲልኩና በትዊተር ዘመቻ እንዲሳተፉ ተደርጓል፤

◈ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፍ የሚሆን ገንዘብ አሰባስቦ አስረክቧል።

















## 24. ዲፌንድ ኢትዮጵያ የፈረንሳይ ቻፕተር

ኢትዮጵያና ፈረንሳይ ይፋዊ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት የጀመሩት በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት (ከአድዋ ጦርነት በኃላ) እ.ኤ.አ. 1897 ዓ/ም ፈረንሳይ ሌጋሲዮኗን በአዲስ አበባ መመስረቷን ተከትሎ ነው። ከዚህ በኃላ በተለይ በመገናኛ ዘርፍ፣ በመንገድ ዝርጋታና በትምህርት መስኮች የነበረው ግንኙነት ከፍተኛ ትኩረት በማግኘቱ እየተጠናከረ መጥቶ ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ (781 ኪ.ሜ) በፈረንሳይ ድጋፍ የተዘረጋው የባቡር ሃዲድ የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ከፍ ወዳለ ደረጃ አድርሶታል። በፖለቲካው መስክም ፈረንሳይና ኢትዮጵያ መልካም ግንኙነት ያላቸው አገሮች ሲሆኑ፣ ሁለቱ አገሮች የቢዝነስ ፎረሞችን በተከታታይ በማካሄድ በንግድ፣ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም ዘርፎች ያላቸውን ግንኙነት በማሳደግ ላይ ይገኛሉ።

ለአብነት ያህልም ከ2014 ወዲህ ኢትዮጵያ ከሰሀራ በታች ካሉ አገራት መካከል ከፈረንሳይ ለሚላኩ ዋና ዋና የትራንስፖርት መሳሪዎች፣ መካኒካልና ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ የፋርማሲቲካል ውጤቶች እና ለምግብነት የሚውሉ የግብርና ምርቶች ዋነኛ መዳረሻ ስትሆን፣ ኢትዮጵያም በአብዛኛው የግብርና እና የጨርቃ ጨርቅ ምርቶችን ወደ ፈረንሳይ ትልካለች። በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ካሉ የአውሮፓ ኢንቨስትመንቶች መካከል የፈረንሳይ በአራተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ለበርካታ ዜጎችም የስራ እድል መፍጠር ችለዋል።

የኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሁኔታ በፈረንሳይ

የፈረንሳይ መንግስት የመረጃ አሰባሰብን እና ነፃነትን አስመልክቶ እ.ኤ.አ ጃኑዋሪ 6 ቀን 1978 ዓ/ም ያወጣው ህግ በአገሪቱ ውስጥ ዘርን ወይም ብሔርን እና ሐይማኖታዊ ትስስርን የተመለከቱ የግለሰብ መረጃዎችን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ማሰባሰብን የሚከለክል በመሆኑ በፈረንሳይ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎችን የተመለከተ ኦፍሴላዊ መረጃ ለማግኘት ያዳግታል። ይሁን እንጂ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ዲፓርትመንት የስነ-ሕዝብ ክፍል ባወጣው ስታትስቲክሳዊ ዳታ እ.ኤ.አ በ2019 ቁጥራቸው 9,551 የሚገመት ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በፈረንሳይ አገር እንደሚኖሩ ያመለክታል።

የዳያስፖራውን አደረጃጀት በተመለከተም በፈረንሳይ የኢትዮጵያውያን ኮሙዩኒቲ ማህበር፣ በስፔን የኢትዮጵያውያን ኮሙዩኒቲ ማህበር፣ ሰላም ኢትዮጵያ ማህበር በደቡብ ፈረንሳይ፣ በካታሎኒያ የኢትዮጵያውያን ማህበር፣ በፈረንሳይ ዲዮን የኢትዮጵያ ማህበር እና ኢትዮ-ፈረንሳይ ለኢትዮጵያ ልማት የተባሉ አደረጃጀቶች ሲኖሩ፤ እምነትን እና አካባቢነትን ወይም ብሔርን መሰረት አድርገው በውስን አባላት የተመሰረቱ በርካታ ስብስቦች በዋና ዋና የፈረንሳይ ከተሞች መኖራቸውም ይታወቃል። ሆኖም በአካባቢው የላቀ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ያለው ዲፌንድ ኢትዮጵያ የፈረንሳይ ቻፕተር ነው።

በፈረንሳይ የሚኖሩ አብዛኞቹ የዳያስፖራ አባላት በአገር ውስጥ የሚካሄደውን የሪሮርም ሂደት በመደገፍ  በተለያዩ መንገዶች ተሳትፎ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል  በአገር ገፅታ ግንባታ፣ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የገንዘብ ስጦታና ቦንድ በመግዛት፣ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎችን መልሶ በማቋቋም፣ የውጭ ሃይሎች በአገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የሚያሳርፉትን ጫና በመቃወም የሚያደርጓቸው ተሳትፎዎች ተጠቃሾች ናቸው።

## ዲፌንድ ኢትዮጵያ የፈረንሳይ ቻፕተር ሊቀመንበር ከአቶ ኤሊያስ አጥላባቸው የተላለፈ መልዕክት፤

## 24. ዲፌንድ ኢትዮጵያ የፈረንሳይ ቻፕተር

ኢትዮጵያና ፈረንሳይ ይፋዊ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት የጀመሩት በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት (በ[illegible] እ.ኤ.አ 1897 [illegible]) ተከትሎ ነው። ከዚህ በኃላ በተለይ በመገናኛ ዘርፍ፣ በመንገድ ዝርጋታና በትምህርት መስኮች የነበረው ግንኙነት ከፍተኛ ትኩረት በማግኘቱ [illegible] (781 ኪ.ሜ) በፈረንሳይ ድጋፍ የተዘረጋው የባ[illegible] ደረጃ አድርሶታል። በፖለቲካው መስክም ፈ[illegible] አገሮች ሲሆኑ፣ ሁለቱ አገሮች የቢዝነስ [illegible] ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም ዘርፎች ያላቸውን [illegible]



ለአብነት ያህልም ከ2014 ወዲህ ኢትዮጵያ [illegible] ለሚላኩ ዋና ዋና የትራንስፖርት መሳሪ[illegible] የፋርማሲቲካል ውጤቶች እና ለምግብነት የሚ[illegible] ኢትዮጵያም በአብዛኛው የግብርና እና የጨር[illegible] በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ካሉ የአውሮፓ [illegible] ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ለበርካታ ዜጎችም [illegible]

የኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያው[illegible] ለማግኘት ያዳግታል። ይሁን እንጂ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢኮኖሚና ማህበራዊ [illegible]ፓርትመንት የስነ-ሕዝብ ክፍል ባወጣው ስታትስቲክሳዊ ዳታ እ.ኤ.አ በ2019 ቁጥራቸው 9,551 የሚገመት ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በፈረንሳይ አገር እንደሚኖሩ መለከታል።

ዳያስፖራውን አደረጃጀት በተመለከተም በፈረንሳይ የኢትዮጵያውያን ኮሙዩኒቲ ማህበር፣ ስፔን የኢትዮጵያውያን ኮሙዩኒቲ ማህበር፣ ሰላም ኢትዮጵያ ማህበር በደቡብ ፈረንሳይ፣ ካታሎኒያ የኢትዮጵያውያን ማህበር፣ በፈረንሳይ ዲዮን የኢትዮጵያ ማህበር እና [illegible]ትዮ-ፈረንሳይ ለኢትዮጵያ ልማት የተባሉ አደረጃጀቶች ሲኖሩ፤ እምነትን እና አካባቢነትን [illegible]ይም ብሔርን መሰረት አድርገው በውስን አባላት የተመሰረቱ በርካታ ስብስቦች በዋና ዋና [illegible]ፈረንሳይ ከተሞች መኖራቸውም ይታወቃል። ሆኖም በአካባቢው የላቀ አስተዋጽኦ ማበርከት ላይ ያለው ዲፌንድ ኢትዮጵያ የፈረንሳይ ቻፕተር ነው።

ፈረንሳይ የሚኖሩ አብዛኞቹ የዳያስፖራ አባላት በአገር ውስጥ የሚካሄደውን የሪሮርም ሂደት መደገፍ በተለያዩ መንገዶች ተሳትፎ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል በአገር [illegible]ቃታ ግንባታ፣ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የገንዘብ ስጦታና ቦንድ በመግዛት፣ በሰው [illegible]ራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎችን መልሶ በማቋቋም፣ የውጭ ሃይሎች በአገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የሚያሳርፉትን ጫና በመቃወም የሚያደርጓቸው [illegible]

ኢትዮጵያውያን ከተባበርን [illegible] ዕድሎችን [illegible] ከዚህም በላይም በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በበርካታ የልማት ዘርፎች ተስፋ ሰጪ [illegible] ህዳሴ ግድብ ሙሌት በስኬት መጠናቀቁ፣ እያደገ ያለው የዴሞክራሲ ሂደትና ህዝባችን አገሩን ለማፍረስ [illegible]ቻላል። ተስፋችንን ለማጨለም በሚሞክሩ አካላት በየቦታው የሚቃጡ ጥፋቶች ቢኖሩም በአንድነት እስከ[illegible] የተመለከተ አፍሴላዊ መረጃ

ችግሮቻችን እንደተራራ የገዘፉ ቢመስሉም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን እስከተባበርንና ትልቁን ስዕል በማየት ነገሮችን በትዕግስት ማለፍና ለግባችን ስኬት ትኩረት በመስጠት ከተንቀሳቀስን መጪው ጊዜ ብሩህ መሆኑ እሙን ነው። ችግሮቻችንን በውይይት በመፍታትም ይበልጥ ጠንካራ ሆነን ለመውጣት ልንጠቀምባቸው ይገባናል።

በተለይም በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን አገራችንን ለመርዳትና የህባችንን ህይወት ለመቀየር ያገኘነውን አጋጣሚ ለመጠቀም መዘናጋት የለብንም። ያካበትነውን ዕውቀትና ክህሎት ለማስተላለፍ፣ በኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ ተሰማርተን ኢኮኖሚውን ለማነቃቃትና ለወቅታዊ አገራዊ ጥሪዎች ምላሽ በመስጠት ሀብት ለማሰባሰብና አገራችን ለሚገጥሟት ችግሮች የመፍትሔው አካላት ለመሆን መስራት ይጠበቅብናል። በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዘርፍም በኢትዮጵያ ላይ እየተፈጠሩ ያሉ ጫናዎችን ለመመከት የጀመርናቸውን ጥረቶች አጠናክረን መቀጠል ይገባናል። ካሉብን ጫናዎች አንጻር የኢትዮጵያ ወዳጆችን ለማብዛት የጀመርናቸው ስራዎች ውጤታማ እስኪሆኑ ድረስ ሰፊ ትግል ማካሄድ እንደሚጠበቅብን ከወዲሁ ተገንዝበን ለመስራት መነሳት እንዳለብን በዚህ አጋጣሚ ማሳሰብ እወዳለሁ።

አቶ ኤሊያስ አጥላባቸው



በፈረንሳይ ከሚገኙና የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ላይ ካሉ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች መካከል ዲፌንድ ኢትዮጵያ የፈረንሳይ ቻፕተር አንዱ ነው። አደረጃጀቱ የዲፌንድ ኢትዮጵያ አውሮፓ አካል ሆኖ የተቋቋመ ሲሆን፣ ተልክዕኮውም የኢትዮጵያ ዳያስፖራዎችን በማስተባበር በአውሮፓ የኢትዮጵያን ገጽታ ለመገንባት የሚያገለግሉ አዎንታዊ የዲፕሎማሲ ስራዎችን ማከናወን ነው። አደረጃጀቱ በአውሮፓ ህብረት የሚገኙ መንግስታት ፖሊሲ አውጭዎች፣ የአውሮፓ ህብረት፣ የአውሮፓ ህብረት ፓርላማና ልዩ ልዩ የተባበሩት መንግስታት ተቋማት በኢትዮጵያ ላይ የሚቀርቡ የተሳሳቱ ዘገባዎችን ተከትሎ የሚወስዷቸውን አቋሞች ለማለዘብና በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ በጎ ፈቃደኛ አባላቱን በመጠቀም ይሰራል። አደረጃጀቱ በመላው ፈረንሳይ በሚገኙ ከተሞች የሚኖሩ አስተባባሪዎቹን በመጠቀም የአድቮኬሲና ሎቢ፣ የማህበራዊና የመደበኛ ሚዲያ ንቅናቄዎችን የሚያከናውን ሲሆን፣ የሀብት ማሰባሰብ ተግባራትንም ያከናውናል። አደረጃጀቱ በፓሪስ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ማህበር ጋር በጥምረት በመስራት ላይ መሆኑ ለዓላማው መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቶለታል።

አደረጃጀቱ ካከናወናቸው ተግባራት መካከል ለፖሊሲ አውጭዎች፣ የተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፣ ተመራጮችና ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ደብዳቤዎችን አዘጋጅቶ በመላክ የገጽታ ግንባታ ስራዎችን ማከናወኑ፣ ተመሳሳይ ዓላማን ካነገቡ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አደረጃጀቶች ጋር በመተባበር የማህበራዊ ሚዲያ ዘመቻ ማካሄዱ፣ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚቀርቡ የተዛቡ የሚዲያ ዘገባዎችን በመከታተል ምላሽ መስጠቱ፣ ሰልፎችን ማስተባበሩ፣ 45 ሺ ዩሮ በማሰባሰብ በአማራና አፋር ክልሎች የተፈናቀሉ ወገኖችን መደገፉና ለአንድ አመት የሚቆይ መደበኛ የሀብት ማሰባሰብ ስራ መጀመሩ፣ በአማራና አፋር ክልሎች ጉዳት ለደረሰባቸው የጤና ተቋማት የሚሆኑ የህክምና መሳሪያዎች ድጋፍ ማድረጉ የሚጠቀሱ ናቸው።






## በ ስ ዊ ዘ ር ላ ን ድ የላቀ አበርክቶ እያደረጉ የሚገኙ የኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አደረጃጀቶች

የሁለቱ አገሮች ግንኙነት ከ19ኛው ክ/ዘመን ጀምሮ ረዥም ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን፣ በዋናነትም እ.ኤ.አ. በ1878 ሲውዘርላንዳዊ ኢንጂነር Mr. Alfred Ilg የተባለው ባለሞያ ለአፄ ሚኒሊክ የተለያዩ የማማከር ስራዎችን በመስራት በተለይም የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር መሰረተ ልማት ግንባታ፣ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የፖስታ አገልግሎት እንዲመሰረት በማድረግ ያከናወናቸው ተግባራቶች የግንኙነቱ መነሻ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ሆኖም የሁለቱ አገሮች ይፋዊ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1923 ነው። በወቅቱም የወዳጅነትና የንግድ ግንኙነቶችን ሊያጠናክሩ የሚችሉ ስምምነቶችን ተፈርመዋል፡፡ እነዚህ ግንኙነቶች እያደጉ መጥተው የኢትዮጵያ የቆንስላ ጽ/ቤት በዙሪክ ሲውዘርላንድ እ.ኤ.አ. በ1924 መከፈት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ሲውዘርላንድ ቆንስላ ጽ/ቤት በአዲስ አበባ በ1956 የከፈተች ሲሆን፣ ይህም በ1962 ወደ ኤምባሲ ደረጃ አሳድጋዋለች።

ሲውዘርላንድ ካላት ህዝብ ውስጥ 25% የሚሆነው የሌላ አገር ዜጋ (Immigrant) ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 80% የሚሆነው ከአውሮፓ አገሮች በተለይም ጀርመን፣ ከፈረንሳይ፣ ከጣሊያንና ከፖርቹጋል የገቡ ሲሆኑ፣ ከአፍሪካ የገቡት ከ5% በታች ድርሻ እንደሚፈፍኑ ይገመታል፡፡

ከስዊዘርላንድ ኢሚግሬሽን በተገኘ መረጃ (ኤፕረል 2021) መሰረት በስዊዘርላንድ 4,408 ገደሚ የሚጠጉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩ ሲሆን፤ እነዚህ ትውልደ ኢትዮጵያን ዳያስፖራዎች ከአስር በላይ በሚሆኑ አደረጃጃቶች በመሰባሰብ በልማት እና አድቮኬሲ ስራዎች የትውልድ አገራቸውን በመደገፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ በንቃት ከሚሳተፉ አደረጃጀቶች መካካል የ እ ኔ ም ለ ወ ገ ኔ በ ስ ዊ ዘ ር ላ ን ድ እና ገበታ ለወገቤ በ ስ ዊ ዘ ር ላ ን ድ አደረጃጀቶች ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም የጣይቱ ልጆች፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች ህብረት በስዊዘርላንድ፣ አቢሲኒያ ስፖርት ክለብ በኦስትሪያ፣ ዘመቻ ለህልውና በስዊዘርላንድ፣ የኢትዮጵያ ትረስት ፈንድ በስዊዘርላንድ፣ ንጋት እና ዲፌንድ ኢትዮጵያም ተጠቃሽ አደረጃጀቶች ናቸው።

## 25. እኔም ለወገኔ በስዊዘርላንድ

እኔም ለወገኔ በስዊዘርላንድ የበጎ አድራጎት ማህበር በስዊዘርላንድ የተለያዩ ከተሞች በሚኖሩ 22 አገር ወዳድ  የበጎ ፍቃድ ግለሰቦች እ.ኤ.አ በጃንዋሪ 2020 የተመሰረተ ማህበር ነው። ዓላማውም በስዊዘርላንድ የሚኖሩ ኢትዮጵያውንና ትውልደ ኢትዮጵያውን እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጆችን በማስተባበር  በአገር ቤት በተለያየ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች በፋይናስና በማቴሪያል መደገፍ እንዲሁም በአገራችን ገጠራማ አካባቢዎች የማህበራዊ መገልገያ ተቋማትን መገንባት ነው።
የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

⁜ ማህበሩ በምስረታው ማግሰት የታዋቂው እና ተወዳጁ የኦሮሚኛ ሙዚቃ አቀንቃኝ ሀጫሉ ሁንዴሳ ድንገተኛ ሞት ተከትሎ በተፈጠረው ረብሻ ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ድጋፍ በማድረግ የበጎ አድራጎት ስራውን ጀምሯል:: በዚህም ማህበሩ በስዊዘርላንድ ለሚኖሩ አገር ወዳዶች ባቀረበው ጥሪ መሰረት በሻሸመኔ እና በአርሲ ነገሌ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች 700,000 ብር በማሰባሰብ  እና የማይበላሹ ምግቦች እና የንጽኅና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን በማዘጋጀት ከቀይ መስቀል ጋር በመተባባር ድጋፉን አድርጓል::

⁜ በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ በነበረው ጦርነት ከትግራይ ለተፈናቀሉ እና በቤንሻንጉል ክልል በነበረው አለመረጋጋት ከመተከል ለተፈናቀሉ ወገኖች ማህበሩ ከመላው የስዊዘርላንድ 579,532.20 ብር በማሰባሰብ ድጋፍ አድርጓል::

⁜ በተመሳሳይ በሰሜን ሸዋ ዞን ስር በምትገኘው የአጣዬ ከተማ ታጣቂዎች ባደረሱት ጥቃት ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን ተከትሎ ማህበሩ ለአጣዬ እንድረስላት በሚል ማህበረሰቡን በማስተባበር 715,000 ብር በማሰባሰብ ለተፈናቃዮች መከልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን የቤት ክዳን ቆርቆሮ፣ ምስማር እና ጥሬ ገንዘብ በሸዋ የሰላምና የልማት ማህበር አማካይነት ድጋፉን አበርክቷል::

⁜ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተለይም በአፋርና በአማራ ክልሎች በወረራ ምክንያት ከፍተኛ የመሰረተ ልማት ተቋማት ውድመትና የዜጎች መፈናቀል መከሰቱ ይታወቃል:: ይህንንም በማስመልከት ማህበሩ ባደረገው የእርዳታ ጥሪ 169,000 ብር በስዊዘርላንድ ከሚኖሩ አባላቱና ተባባሪዎቹ ማሰባሰብ ችሏል:: ከዚህ ከተሰበሰበው ገንዘብ ወጪ ተደርጎ ለህጻናት፣ ለእመጫቶችና ለአረጋውን የሚሆን 1,373 ካርቶን አልሚ ምግቦች፣ 170 ኩንታል የስንዴ ዱቄት፣ 3,123 ሊትር ዘይት በማህበሩ የአገር ቤት ተወካዮች ተገዝቶ በአደጋ ስጋት ኮሚሽን በኩል በአፋርና በወሎ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች እንዲደርስ አድርጓል::








## 26. ዘመቻ ለህልውና በ ስ ዊ ዘ ር ላ ን ድ

ዘመቻ ለህልውና በስዊዘርላንድ በስዊዘርላንድ የተለያዩ ከተሞች በሚኖሩ አገር ወዳድ የበጎ ፍቃድ ግለሰቦች የተመሰረተ ማህበር ነው:: ማህበሩ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተፈጠረው ግጭት የተጎዱ አካባባዎችን መልሶ ለመገንባት በስዊዘርላንድ የሚኖሩ ዳያስፖራዎችን በማስተባበር እና የገቢ ማሰባሰቢያ ሁነቶችን በማዘጋጀት ድጋፍ አድርጓል::

በመላው ስዊዘርላንድ የሚኖሩ ኢትጵያውያንን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች በማስተባበር በአገራችን በተለይም በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በአፋር እና በአማራ ክልሎች የወደሙ ተቋማትን መልሶ ለመገንባት ዘመቻ ለህልውና በሚል መርህ የዳስፖራ አባላቱን በማስተባበር በሁለት ዙር 112,758 የስዊዝ ፍራንክ ማሰባሰብ ችሏል::

የአመራር አባላቱ ይህንን ከማህበረሰቡ ያሰባሰቡንት ኃብት ይዘው በአፋርና በአማራ ክልሎች በአካል በመገኘት የተፈናቀሉ እና ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎችን በመጎብኘትና በማጽናናት ድጋፉን ለክልሎቹ አስረክበዋል::

### በኖርዲክ አገሮች የላቀ አፈጻጸም ያላቸው የዳያስፖራ አደረጃጀቶች

በስዊድን የሚገኘው የኢፌዴሪ ሚሲዮን የኖርዲክ አገሮች የሆኑት ኖርዌይ፣ ዴንማርክና ፊንላንድን ይሸፍናል። በእነዚህ አገሮችም ከ45 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንደሚኖሩ ይገመታል። በአገራቱ በርካታ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች የሚገኙ ሲሆን፣ የኢትዮጵያውያን ማህበር በኖርዌይ፣ ዲፌንድ ኢትዮጵያ ታስክፎርስ ኖርዌይ፣ በኖርዌይ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ማሕበረሠብ በስዊድን፣ የኢትዮጵያውያን ማህበር በዴንማርክ፣ በኖርዲክ አገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ማህበር፣ የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ኢንስቲትዩት በስዊድን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ በኖርዲክ አገሮች፣ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ማህበር በኖርዲክ አገሮች፣ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ማህበር በኖርዲክ አገሮች እንዲሁም የትውልድ እናት ለሰላምና ዕርቅ ማህበር ተጠቃሾች ናቸው። በኖርዲክ አገሮች የላቀ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ከሚገኙ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች መካከል የኢትዮጵያዊያን ማህበር በፊንላንድ እና እንቁም ለኢትዮጵያ በኖርዌይ ይገኙባቸዋል።

ስዊድን እ.ኤ.አ. ከ1860 ዓ/ም. ጀምሮ የሃይማት ሰዎችን ወደ ኢትዮጵያ በመላክ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ተቋማትን በመክፈት ከአገራችን ጋር የረጅም ጊዜ ግንኙነት ያላት አገር ብትሆንም በሁለቱ አገሮች መካከል ይፋዊ ዲፕሎማስያዊ ግንኙነት የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1929 ስዊድን በአዲስ አበባ የክብር ቆንስላ በሾመችበት ጊዜ ነው:: ግንኙነቱ ይበልጥ የተጠናከረውም እ.ኤ.አ. በ1946 ዓ.ም የስዊድን ሌጋሲዮን በአዲስ አበባ ሲመሰረትና ኢትዮጵያም እ.ኤ.አ. በ1963 ስቶክሆልም ውስጥ ኤምባሲ በከፈተችበት ጊዜ ነው::






## 27. የኢትዮጵያዊያን ማህበር በፊንላንድ

የኢትዮጵያዊያን ማህበር በፊንላንድ እኤአ መስከረም 1991 ዓ/ም በፊንላንድ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በአገራቸው የወደፊት ሁኔታ ላይ የበኩላቸውን ተሳትፎ ለማድረግ፣ ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን ለማሰባሰብ፣ ለመረዳዳት፣ የአገራቸውን ታሪክና ባህል ለማስተዋወቅ በማሰብ ተመሰረተ። ከአላማዎቹም መካከል ኢትዮጵያውያን ዜጎችን በማሰባሰብ እና እርስ በእርስ መረዳዳት፣ ከፊንላንዳዊያን ጋር መልካም ግንኙንትን መፍጠር፣ የዳያስፖራውን ህብረት ማጠናከር፣ የአገርን ባህልን ማስተዋወቅ፣ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ የሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነት ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንዲያገኙ መስራት ይገኙበታል። ማኅበሩ የሚተዳደረው በየአመቱ በሚመረጥ የሥራ አስፈፃሚ አካል ሲሆን፣ ስራ አስፈጻሚው አካልም የማኅበሩን የዕለት ተዕለት ተግባራትና አገልግሎቶች ይከታተላል። ማህበሩ በአሁኑ ወቅት 67 ቋሚ አባላትና በማህበሩ አላማ የሚስማሙ የፊንላንድ ዜጎች ያላቸው የክብር አባላት አሉት። ማህበሩን በሊቀመንበርነት በመምራት ላይ የሚገኙንትም አቶ በላይነህ በቀለ ናቸው።

የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

- የተለያዩ አነስተኛ ማህበራዊ እርዳታዎች ለማህበሩ አባላትና አባላት ላልሆኑ ኢትዮጵያዊያን አስፈላጊ የገንዘብ እርዳታ ያደርጋል።

- ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የገንዘብና የቁሳዊ ድጋፍ በማህበሩ እና ከፊንላንድ የውጭ ተራድኦ ድርጅት ጋር ትብብር በማደረግ ልዩ ልዩ ሰብአዊ ድገፎችን አድርጓል።

- በኤድስ በሽታ ቤተሰቦቻቸውን ያጡ ልጆችን ለመደገፍ፣ በበሽታው አስከፊነትን ላይ ህዝቡ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማስተዋወቅ፣ በተጨማሪም በተፈጥሮ አደጋዎች ችግር ውስጥ ለሚገኙ ወገኖቻችን ከፊኒሽ ቀይ መስቀል ጋር በመተባበር እርድታ አድርጓል።

- በየአመቱ የኢትዮጵያ በዓላትን በማክበር ኢትዮጵያውያን ማህበረሰብንና ፊንላንዳዊያንን በማገልግል ላይ ይገኛል።

- በኢትዮጵያ ሰብአዊና ተፈጥሮአዊ ችግሮች በተከሰቱበት ወቅቶች ሁሉ ችግሮችን ለመቅረፍ በፊንላንድ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር ከተለያዩ የፊንላንድ ለጋሽ ድርጅቶች እርዳታዎችን በማሰባሰብ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ ልኳል።

- በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊን (ሳውዲ አረቢያ፣ የመን፣ ለሚገኙ) የገንዘብ እርዳታ በመላክ ድጋፍ አድርጎአል።

- በሰሜን ኢትዮጵያ በተካሄደው ጦርነት የተጎዱትን የአፋርና የአማራ ህዝቦች በገንዘብ ለመርዳት በተደረገው ትብብር ላይ ግንባር ቀደም ሚና ተጫውቷል።

- በአሁኑ ወቅት በአዲስ ትውልድ ወጣቶች በመመራት አዲስ እርምጃ ለማድረግ ተስፋና እቅዶች ተይዟል።





## 28. እንቁም ለኢትዮጵያ በኖርዌይ

እንቁም ለኢትዮጵያ በኖርዌይ ኢትዮጵያን መልሶ ለማቋቋም እና ለመርዳት በሚደረገው ጥረት የበኩሉን አስተዋጾ ለማድረግ ታስቦ በተለያዩ ኖርዌይ አካባቢዎች በሚኖሩ ተቆርቋሪ ትውልደ ኢትዮጵያዉያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች እ.አ.አ. በ2021 የተቋቋመና በኖርዌይ መንግስት የተመገበ ድርጅት ነው። ድርጅቱ አትራፊ ያልሆነ የበጎ ፍቃድ ድርጅት ሲሆን፣ ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ፣ ከዘር እና ከመሳሰሉ ነገሮች ነጻ በሆነ ሁኔታ ተግባሩን የሚያከናውን ሲሆን፣ የድርጅቱን ስራ በበላይነት የሚመራውና የሚያካሂደው የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ነው። ከድርጅቱ ዓላማዎች መካከል ኢትዮጵያ ውስጥ በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ ችግር ምክንያት ለተቸገሩ ዜጎች ሰብዐዊ ዕርዳታ ማድረግና በተለያዩ ችግሮች ምክንያት የሚደርሱ የምጣኔ ሃብት እና የውጭ ምንዛሪ እጥረቶችን ለማቃለል የበኩሉን የገንዘብ አስተዋጾ ማድረግ ይገኙበቻዋል። ይህንንም ለማሳካት በኖርዌይ  የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆችን በማስተባበር እና በማነቃቃት ለልዩ ልዩ የድጋፍ አገልግሎቶች የሚውል ገንዘብ በማሰባሰብ ወደ አገር ቤት ይልካል።

የድርጅቱ አመራር በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የሚተዳደር ሲሆን፣ ተጠሪነታቸው ለጠቅላላ ጉባኤ የሆኑና በጉባኤው የተመረጡ ሰባት የሥራ  አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትንና ሁለት የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላትን ያካትታል። ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተወጣጡ አምስት የአማካሪ ቦርድ አባላትንም ያቀፈ ሲሆን፣ ለሁለት አመት በሚቆየው የምርጫ ዘመን በሰብሳቢነት በመምራት ላይ ያሉት ዶ/ር ነጻነት ግዛው ናቸው።

የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

*ባለፈው አመትም በአፋር እና አማራ ክልል ለሚገኙ በጦርነቱ ምክንያት ለተጎዱ ወገኖች ወደ ሶስት ሚሊዮን የሚጠጋ ብር አሰባስቦ ለፌደራል የአደጋ ስጋትና አመራር ኮሚሽን አስረክቧል።

* በጂንካ አካባቢ በጎሳ ግጭት ምክንያት ከቀያቸው ተፈናቅለው ለነበሩ ወገኖች ወደ መቶ ሺ ብር የሚጠጋ ገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።

* የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ በህዝብ ተሳትፎ ተፈጻሚ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

## 29. የዲፌንድ ኢትዮጵያ የአውሮፓ ግብረ ሀይል ተልዕኮና ዓላማዎች



ግብረ ሀይሉ በአውሮፓ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችና ምሁራን የተቋቋመ ሲሆን፣ ዓላማውም በኢትዮጵያ ላይ የሚቃጡ ጫናዎችን በአውሮፓ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበርና ልዩ ልዩ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስራዎችን በማከናወን መመከት ነው። በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረውን ግጭት ተከትሎ የተቋቋመው ግብረ ሀይሉ በመላው አውሮፓ በሚገኙ 14 አገራት ውስጥ ተወካይ ድርጅቶች አሉት። አገራቱም ቤልጂየም፣ ቼክ ሪፐብሊክ፣ ዴንማርክ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ አየርላንድ፣ ጣሊያን፣ ኖርዌይ፣ ስፔን፣ ስዊድን፣ ስዊዘርላንድ፣ ኔዘርላንድስና ዩናይትድ ኪንግደም ናቸው።

ግብረ ሃይሉ በአውሮፓ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የማህበረሰብ አባላትን ገንቢና ወሳኝ ኢትዮጵያ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ መሳሪያ የማድረግ የረዥም ጊዜ ተልዕኮ ይዞ በመስራት ላይ ይገኛል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማሳካት ከሚያከናውናቸው ጉዳዮች መካከልም በኢትዮጵያ ላይ የሚቃጡ የተሳሳቱ ትርክቶችን መመከት፣ በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የአውሮፓ አገራት፣ የአውሮፓ ህብረት፣ የአውሮፓ ፓርላማና ልዩ ልዩ የተባበሩት መንግስታት አካላት ፖሊሲዎችንና ተግባራትን መሞገት እንዲሁም ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ የኢትዮጵያ ወዳጆች፣ የውጭ ዜጎችና ፖሊሲ አውጪዎች ለኢትዮጵያ ጥቅም እንዲቆሙ ማነሳሳት ይገኙበታል።

ግብረ ሀይሉ የሚያከናውናቸው ተግባራት በአራት ምሶሶዎች ላይ የተመሰረቱ ሲሆኑ፣ የሎቢና ዲፕሎማሲ፣ የማህበራዊ ሚዲያና ቅስቀሳ ናቸው። ድርጅቱ ከምስረታው ጀምሮ ባለፉት ሁለት አመታት በአውሮፓ የተካሄዱ የዲጂታል ዘመቻዎችን፣ በሚዲያዎች ለሚወጡ የተሳሳቱ መረጃዎች ምልሽ የመስጠት ተግባራትን እንዲሁም በኢትዮጵያ ላይ ሲነዙ የነበሩ የተሳሳቱ ትርክቶችን በመመከት ሲሰራ ቆይቷል።

የዲፌንድ ኢትዮጵያ የአውሮፓ ግብረ ሀይል ሊቀመንበር አቶ ቅጣው ያየህይራድ መልዕክት፤

ያለፈው አመት በብዙ መልኩ ለዳያስፖራውም ሆነ ለምንወዳት ሀገራችን ሰላም ወሳኝ አመት ነበር ማለት ይቻላል። በቀደመው አመት የተካሄዱትን የኖሞር ንቅናቄዎች ተከትሎ በተጠራው ታላቁ ጉዞ ወደ ሀገር ቤት ዳያስፖራው ወደ አገሩ በመትመም የቁርጥ ቀን ልጅነቱን አሳይቷል። በሂደቱ ዳያስፖራው ለአገሩ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ከማበርከቱም በላይ የምዕራባውያን ሚዲያዎች ትርክት ሀሰተኝነትን አረጋግጧል።

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ እየተፈጠሩ ያሉ አበረታች ሁኔታዎች አዲሱን አመት በተስፋ እንድንቀበለውና ለተሻለ የገጽታ ግንባታ ስራ ትኩረት ሰጥተን እንድንንቀሳቀስ እድል ፈጥሮልናል ብለን እናምናለን። በቀጣይ ጊዜያትም ‘ኢትዮጵያን ማስተዋወቅና መከላከል’ በሚለው መርህችን በመመራትም ሰፋፊ የፐብለክ ዲፕሎማሲ ስራዎችን ለማከናወን አቅደናል። ቀጣዩ ጊዜ የያዛቸው ተስፋዎች ፍሬ እንዲያፈሩና የሰላም ሂደቱ እንዲጠናከር፣ ሀገራዊ ምክክሩ እንዲሳለብት እንዲሁም ኢትዮጵያና ህዝቦቿ የለውጥ ትሩፋቶቹን እንዲቋደሱና ልማታቸውን እንዲያረጋግጡ ድጋፋችንን አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል።








## ግብረ ሀይሉ ተሳትፎዎች፤

- የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብሩ ከ50 በላይ የዲጂታል ዘመቻዎችን በማስተባበር ከ4.5 ሚሊዮን በላይ ተደራሽነትን እንዲያገኙ አድርጋል፣

- ከ400 በላይ የታቀዱ የትዊተር ሀንድሎችን በማዘጋጀት በኢትዮጵያ ላይ የተፈጠሩ ያልተገቡ ዘመቻዎችን መክቷል፣

- በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ለሚችሉ የአውሮፓ አገራት፣ በአውሮፓ ህብረት፣ በአውሮፓ ፓርላማና በልዩ ልዩ የተባበሩት መንግስታት አካላት ደብዳቤ በመጻፍ አቅርቧል፣

- በልዩ ልዩ የአውሮፓ ከተሞች የተካሄዱ ሰልፎችን አስተባብሯል፣

- ለ20 ወራት ከ200 ሰዓት በላይ የወሰዱ የዌቢናር መድረኮችን በማመቻቸት የኢትዮጵያውያንንና የሌሎች አፍሪካውያንን ግንዛቤ ለማሳደግ ሰርቷል፣

- ዲጂታል ሚዲያን በመጠቀም ከ30ሺ በላይ ኢሜይሎችን ከ1ሺ 200 ለሚበልጡ የአውሮፓ ፓርላማ አባላት፣ ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ቲንክ ታንኮች፣ ለተባበሩት መንግስታት አካላት ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ላደረጉ ባለሀብቶችና በ12 አገራት ለሚገኙ ተጽዕኖ ፈጣሪ አካላት መልዕክቶችን ማድረስ ችሏል፣

- በተወካዮቹ አማካኝነት በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ በመቅረብ ዓላማውን የሚያሳኩ ተግባራትን አከናውኗል፣

- በተለያዩ ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ከ25 በላይ ደብዳቤዎችን በማዘጋጀትና በልዩ ልዩ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች እንዲፈረም በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ አድርጓል፣
- በአገራችን በልዩ ልዩ አካባቢዎች በግጭት ምክንያት ለተጎዱ ወገኖች የድጋፍ ስራ ተከናውኗን፤

# በሰሜን አሜሪካ የላቀ አበርክቶ እያደረጉ የሚገኙ የኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አደረጃጀቶች

የኢትዮጵያ እና አሜሪካ ግንኙነት የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1903 ሲሆን፣ በንጉሰ ነገስት ዳግማዊ ሚኒሊክ እና በጊዜው የአሜሪካን መንግሰት ተወካይ በነበሩት ሮበርት ስኪነር መካከል በተፈረመው የንግድ ስምምነት ነው፡፡ አሜሪካ እ.ኤ.አ በ1909 በአዲስ አባባ ለመጀመሪያ ጊዜ የቆንስላ ጽ/ቤቷን ከፍታ የነበረ ሲሆን፤ በአንደኛው አለም ጦርነት ምክንያት እ.ኤ.አ በ1914 ጽ/ቤቷን ዘግታለች። ከኢትዮጵያ በቀረበው ጥያቄ መሠረት  እ.ኤ.አ በ1928 የቆንስላ ጽ/ቤቱ እንደገና ተከፍቶ እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመሪያ ማለትም እ.ኤ.አ እስከ 1937 ድረስ ሲሰራ ቆየ፡፡ ከሁለተኛ የአለም ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ቆንስላ ጽ/ቤት በዋሽንግተን ዲሲ እ.ኤ.አ በ1943 መከፈቷን ተከትሎ  እ.ኤ.አ በ1944 አሜሪካ ለሶስተኛ ጊዜ እንደገና ቆንስላ ጽ/ቤቷን በአዲስ አበባ ከፈተች። እ.ኤ.አ 1949 ሁለቱ አገሮች የዲፕሎማትክ ውክልና ደረጃቸውን ወደ ኢምባሲ ደረጃ ከፍ በማድረግ አምባሳደሮችን ተለዋወጡ። እ.ኤ.አ በ1974 ጀምሮ ኢትዮጵያ ከሶቭዬት ህብረትና ከሌሎች ሶሻሊስት አገሮች ጋር የመሰረተችው ግንኙነት ለሁለቱ አገሮች ግንኙነት መቀዝቀዝና ብሎም መሻከር ምክንያት ሆኖ ቆይቷል። ይህም እ.ኤ.አ 1980 ጀምሮ የሁለቱ አገሮች የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ወደ ጉዳይ ፈፃሚ ደረጃ አውርዶት የነበረ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ ከ1992 ጀምሮ ግን ግንኙነታቸው በአምባሳደር ደረጃ ከፍ እንዲል ተደርጓል።

እ.ኤ.አ. ከ1909 ጀምሮ አሜሪካ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያ መዳረሻ ከሆኑ አገራት መካካል የምትጠቀስ ሲሆን፣ ይህን የረጅም ዓመታት ግንኙነትን ተከትሎ እስከ ሶስተኛ ትውልድ የተሻገረ እና ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ይኖራሉ፡፡ በአሜሪካ የሚገኙ የኢትዮጵያ ዳያስፖራዎች በአንጻራዊነት አውቀት እና ልምድ ያላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአገር ቤት በሚካሄዱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎ የላቀ ነው፡፡

በአገረ አሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በ22 ታላላቅ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች ተደራጅተው በልማት እና አድቮኬሲ ስራዎች የትውልድ አገራቸውን በመደገፍ ላይ ይገኛሉ። ከነዚህ አደረጃጀቶች መካካል የአሜሪካን ኢትዮጵያዉያን የሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ (AEPAC-ኤፓክ)፣ የኢትዮጵያን አሜሪካን ሲቪክ ካውንስል (የኢትዮጵያ አሜሪካውያን የዜጎች ምክር ቤት)፣ ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ድምጽ  (GLEAN) እና ኢትዮጵያ ትቀጥላለች (Ethiopia Shall Continue, ESC ንቁ ተሳትፎ በማድረግ  ላይ ካሉ  ማህበራት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡  በተጨማሪም ህዝብ ለህዝብ፣ የኢትዮጵያ ውሃ አማካሪ ም/ቤት፣ ሚድዌስት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ፣ ዲኤምቪ ፒዲኤ ካውንስል፣ አብረን፣ የኢትዮጵያ አሜሪካውያን ልማት ም/ቤት፣ ጌትፋክት ኢትዮጵያ፣ ሰላምና አንድነት በኢትዮጵያ ማህበር፣ ዊ አስፓየር፣ ግሎባል አሊያንስ፣ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን ስፖርት ፌዴሬሽን፣ ቲች ኤንድ ሰርቭ አፍሪካ፣ አድማስ፣ ሰላምና አንድነት ለኢትዮጵያ ማህበር - ዋሽንግተን ዲሲ ግብረ ኃይል፣ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ተግባር ምክር ቤት፣ በድር ኢትዮጵያ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ጥምረት የተሻለ ተሳትፎ በማድረግ ላይ ከሚገኙ አደረጃጀቶች መካከል ይገኛሉ።

የአሜሪካን ኢትዮጵያዉያን የሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ (AEPAC-ኤፓክ) መንግሥታዊ ያልሆነ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ድረትጅት ሲሆን፣ በፖለቲካ ገለልተኝነት መርሆ ላይ ተመስርቶ በበጎ ፈቃድ ህዝብን እያገለገለ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡ የድርጅቱ ዋና ዓላማ በአሜሪካና ኢትዮጵያ መካከል ከመቶ አመት በላይ የዘለቀው ግንኙነት እንዲጠናከር የድርሻዉን ማበርከት ሲሆን፣ የሚከተሉት ተልእኮዎች አሉት፤

❈ የአሜሪካና ኢትዮጵያን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ማጠናከር፣

❈ በአፍሪካ በተለይም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች መከበር የሚዳብሩበትን፣ የነጻ ገበያ ኤኮኖሚ የሚጠናከርበትን፣ እንዲሁም በአፍሪካ ቀንድና ባጠቃላይ በአህጉሩ፤ ደህንነት፤ ሰላምና መረጋጋት የሚሰፍኑበትን ዘዴዎች መሻትና ኢትዮጵያና አሜሪካ እነዚህን ግቦች ለማሳካት በጋራ የሚሠሩበትን መንገድ የማመቻቸት አስተዋጽኦ ማበርከት፤

❈ በተለይም በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን፣ ዴሞክራሲ እንዲዳብር፣ አገራችን ኢትዮጵያም እንደተለመደው ዋልታ ሆና እንድትቀጥል መስራት፣

የአሜሪካን ኢትዮጵያዉያን የሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ (AEPAC-ኤፓክ) ከአሜሪካን መንግሥት ባላስልጣናት፤ የኮንግሬስ አባላትና የስቪል ሶሳይቲ መሪዎች ጋር ተከታታይ ዉይይትና ምክክር በማድረግ ኢትዮጵያ ለአሜሪካ አስተማማኝ ጠንካራ አጋርና ጥሩ ወዳጅ መሆኗን ለማሳወቅና ለማሳመን ያለመታከት ይሰራል።

## የኮሚቴው ተሳትፎዎች፤

የአሜሪካን ኢትዮጵያዉያን የሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ (AEPAC-ኤፓክ) ከተቋቋመ ከሁለት ዓመታት ያነሰ ጊዜ ቢያስቆጥርም በርካታ ስኬቶችን ለማስመዝገብ በቅቷል። ከእነዚህም ዉስጥ በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች ከሀያ በላይ ቅርንጫፎችንና ኮሚቴዎችን ማቋቋም የቻለ ሲሆን፣ እስካሁን 30,000 የሚደርሱ አሜሪካን ኢትዮጵያዉያንን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በማሳተፍ ላይ ይገኛል፡፡ ኮሚቴው እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 2021 ዓ/ም ከተቋቋምንበት ጊዜ አንስቶ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት ቀጥሎ ቀርበዋል።

- በአሜሪካ ግዛቶች የምርጫ ተወዳዳሪዎችን፤ በተለይም የኤፓክን ዓላማን የሚያራምዱና ለኢትዮጵያና አሜሪካ መልካም ግንኙነት የቆሙ ተወዳዳሪዎችን በመደገፍ፤ በምርጫ አሸናፊ እንዲሆኑ አባላቱ ድምጻቸዉን እንዲሰጡና ውጤቱ እንዲቀየር አድርጓል፤

- ከአሜሪካ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና የኮንግሬስ አባላት ጋር በአሜሪካና ኢትዮጵያ ግንኙነት ላይ ውይይቶችን አካሂዷል፤

- በኢትዮጵያ ላይ የተከፈተዉን ሰፊ የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ለመቋቋምና ብሎም ለማክሸፍ በእዉነት ላይ የተመረኮዘ መረጃ በማሰባሰብና ለዓለም አቀፍ መንግሥታት፣ ድርጅቶችና ሚዲያዎች ተደራሽ በማድረግ ጉዳትን መቀነስና መከላከል ችሏል፤

- የአሜሪካንና ኢትዮጵያን ግንኙነት ሊጎዱ የሚችሉ HR.445፣ HR.6600 እና S3199 የመሰሉ የህግ ረቂቆች እንዳይጸድቁ የሴኔትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን ቀርቦ በማነጋገር፣ አባላት ለወኪሎቻቸዉ ስሞታ እንዲያቀርቡ እና ሰልፍ እንዲወጡ አድርጓል፤

- ኢትዮጵያን የአፍሪካን አገራት የንግድ እቃዎቻቸዉን ወደ አሜሪካ ከቀረጥ ነጻ በሆነ ዕድል እንዲያስገቡ ወደ ሚፈቅደዉ “ለአፍሪካ እድገትና ዕድል ለመስጠት ህግ” (AGOA) ተሳትፎዋ ተመልሳ እንድትገባ እንዲፈቀድላት የማግባባት ስራ እያከናወነ ይገኛል፤

- በተለያዩ ታዋቂ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች እንደ ዋሽንግተን ፖስትና ቢቢሲ ባሉት ኢንተርቪው በመስጠትና ጽሁፎችን በማሳተም የሰሜን ኢትዮጵያ ግጭት መነሻና ሂደት በትክክለኛ ገጽታው አሳውቋል፤



## 31. የኢትዮጵያን አሜሪካን ሲቪክ ካውንስል (የኢትዮጵያ አሜሪካውያን የዜጎች ምክር ቤት)

የኢትዮጵያን አሜሪካን ሲቪክ ካውንስል (የኢትዮጵያ አሜሪካውያን የዜጎች ምክር ቤት) ከተቋቋመበት እ.ኤ.አ. 2016 ጀምሮ በኢትዮጵያ መልካም አስተዳደር፣ ዲሞክራሲ እና የሰብዓዊ መብት እንዲከበር የዲፕሎማሲ ስራን ማካናወን ዓላማው አድረጎ የሚንቀሳቀስ ህጋዊ ድርጅት ነው። ምክር ቤቱ በአሜሪካን ግዛቶች ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሁሉ የዘር፣ የእምነት ወይም የፆታ ልዩነት ሳይኖረው በኢትዮጵያ አንድነት መንፈስ የዲፕሎማሲ ስራውን በየከተማው የሚሰሩ ጠንካራ ደጋፊ አባላት አሉት። እነዚህ አባላት በአሜሪካ የመምረጥ መብታቸውን በመጠቀም ኢትዮጵያን በተመለከተ ለሚወጡ ረቂቆች ህጎችና ውሳኔዎች ቅድሚያ በመስጠት የአሜሪካ ህግ አውጪ አካላት ላይ ጫና ለመፍጠር ከአባላቱና ከበርካታ የሲቪክ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሰራል።

## የምክር ቤቱ ተሳትፎዎች፤

የሲቪክ ካውንስሉ በአሜሪካን አገር የህግ አውጪ ወይም አስፈፃሚው አካል ውስጥ ያለው ተደማጭነት እየጨመረ የመጣ ሲሆን፣ እካሁን ከ350 በላይ ከሚሆኑ ኮንግረስ እና ሴኔት አባላት ጋር በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ እና በአሜሪካ ፖለቲካ ጉዳይ ላይ ውይይት አድርጎል። ካውስንሉ የቀድሞ የአሜሪካን ፕሬዝዳንት ክሊንተን አማካሪዎችን እና የፕሬዝዳንት ጆ ባይደን የቀድሞ አማካሪዎች ለካውንስሉ የህዝብ ግንኙነት እና የህግ አማካሪ ሆነው እንዲሰሩ ያደረገ ሲሆን፣ የሚከተሉትን ዐበይት ተግባራትም አከናውኗል፤

* በተደጋጋሚ በኮንግረስ በመገኘት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ በርካታ ምስክርነቶችን ሰጥቷል፡፡

* ዩኒቲ ፎር ኢትዮጵያ በሚል የዲጅታል ቡድን በማቋቋም ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል።

* ድርጅቱ በአሜሪካን አገር ለመጀመሪያ ጊዜ ዲያስፖራውን በማሳተፍ የሎቢ ድርጅቶችን በመቅጠር የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብሩ ህጎች እንዲረቀቁና እንዲወጡ፤ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚጻረሩት ደግሞ እንዳይጸድቁ አድርጓል።
* በአሜሪካን ታዋቂ ሚዲያዎች እንደ yahoo news, Fox News, Reuters እና AP News እና ሌሎችም ትልልቅ ሚዲያዎች ላይ በርካታ ወቅታዊ የአገራችንን መረጃዎች ተደራሽ አድርጓል።

* ከሁለት መቶ አርባ ሺ በላይ ፊርማዎችን በማሰባሰብ የአሜሪካ መንግስት በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ ገለልተኛ አቋም እንዲያራምድ ጫና መፍጠር ችሏል።

* እንደ ሪቨረንድ ጀሲ ጃክሰን የመሰሉ የጥቁር አሜሪካውያን የመብት ተሟጋቾች ኢትዮጵያ አባይን የመጠቀም መብቷ እንዲከበርላት የሚደግፍ ደብዳቤ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ፀጥታው ምክርቤት እንዲያስገቡ እንዲሁም በአሜሪካ ከፍተኛው የጥቁሮች ድርጅት የሆነው NAACP በአባይ ዙሪያ የግብፅን ድርጊት በመቃወም በኮንግረስ ደረጃ ረቂቅ እንዲወጣ ድራፍት እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

* በክቡር በጠቅላይ ሚንስትር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ የቀረበውን የአረንጓዴ አሻራ ጥሪን በመቀበልም ግሪን ላንድ ፋውንዴሽን ከተባለው አጋር ድርጅት ጋር በመሆን በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ችግኞች ተተክለዋል።

* የኢትዮጵያ አሜሪካውያን ሲቪክ ካውንስል በዩኒት ፎር ኢትዮጵያ መዋቅሩ በአገር ውስጥ ከሚሰሩ የኢትዮጵያ ሲቪክ ድርጅቶች ጋር በመሆንም ለመከላከያ ሰራዊት ጉዳት ለደረሰባቸው ቤተሰቦች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ በተለይም የአገርን ሉኣላዊነት ለማስከበር ለተዋደቁ እና የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን የመከላከያ አባላት እና ቤተሰቦች በሸራተን አዲስ የገና በኣል በማስመልከት ከቤተሰቦቻቸው ጋር የእራት ግብዣ አድርጓል።



## 32. ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ድምጽ (GLEAN)

### የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ድምጽ (GLEAN) ዋና ዓላማ እና ተልእኮ

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ድምጽ (GLEAN) ዋና ዓላማ የኢትዮጵያን ቀጣይ ልማት፣ ሰላም፣ መረጋጋት እና ዴሞክራሲ ለመደገፍ ከተለያዩ የአድቮኬሲ ድርጅቶች በተውጣጡ ኢትዮጵያውያን እና በበጎ ፈቃደኞች ቡድን የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን፣ ከፖለቲካ እና ሀይማኖታዊ ጉዳዮች ነጻ ሆኖ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና ክብር ማስጠበቅን ዓላማው አድርጎ የሚሰራ ድርጅት ነው። ከዚህም ጋር በተያያዘ ድርጅቱ የህግ የበላይነት የተከበረባት፣ ሰላም እና ዲሞክራሲ የሰፈነባት፣ የበለፀገች እና ተራማጅ ኢትዮጵያን የማየት ራዕይን ሰንቆ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እና የሕዝቧን ደኅንነት የሚያስጠብቁ ጠንካራ የጥብቅና እና የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስራ ላይ አትኩሮ ይሰራል፡፡

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ድምጽ (GLEAN) በሶስት ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ተሚጋች ድርጅቶችን እና ህዝባዊ ንቅናቄዎችን ይደግፋል፡፡ በዚህ መሰረት፤

1. ማስረጃ እና አስተማማኝ መረጃ ላይ የተመሰረቱ መልእክቶችን በመጠቀም የአድቮኬሲውን መልክዓ ምድር በአዎንታዊ መልኩ ለመቅረጽ በተሚጋች ድርጅቶች እና ግለሰቦች መካከል አገናኝ ድልድይ በመሆን፤

- አካላዊ እና ቨርችዋል የቀጥታ ክስተቶችን የማቀናበር እና የማመቻቸት፤
- በኢትዮጵያ ላይ የሚደረጉ ማናቸው ያልተገቡ ጫናዎችን ለመቃወም ለሚካሄዱ ሰልፎች አጋዥ የሆኑ  መፈክሮችን፣ ፖስተሮችን፣ በራሪ ወረቀቶችን ማዘጋጀት፤ ለኦፊሴላዊ ደብዳቤዎች እና ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ መመሪያዎችን እና አብነቶችን ማዘጋጀት፤
- በጥራት የተዘጋጁ መልዕክቶችንና  የግራፊክስ፣ የአኒሜሽን፣ የቪዲዮ ዲጂታል አቅሞችን ማልማት እና መጠቀም፤
- የአድቮኬሲ መርጃዎችን እና መሳሪያዎችን ለማቅረብ ድረ-ገጾችን እና የማህበራዊ ሚዲያ ገጾችን ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ማዋል፡፤

2. የአቅም ግንባታ፡- ውጤታማ የጥብቅና ጥረቶችን እንዴት ማከናወን እንደሚቻል ለአጋር ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት፤

- በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ህብረተሰቡን  ማስተማርና ግንዛቤ ማስጨበጥ፤
- ህዝቡን ለደጋፊነት የሚያገለግሉ የቴክኖሎጂ መድረኮችን (ለምሳሌ፣ VoterVOICE፣ ለደብዳቤ መፃፍ እና የስልክ ዘመቻዎች፣ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮችን (ለምሳሌ ትዊተር፣ ፌስቡክ፣ ዩቲዩብ፣ ኢንስታግራም) ማስረዳትና እና/ወይም ማሰልጠን፤
- በገጽ ለገጽና የበይነ መረብ ውይይቶች (ለምሳሌ ትዊተር፣ ፌስቡክ) እና ከዋና ዋና የዜና ማሰራጫዎች (ለምሳሌ ቲቪ፣ ሬዲዮ) ጋር ለሚደረጉ ቃለመጠይቆች ውጤታማ መልዕክቶችን ለማድረስ እና አስቸጋሪ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተሚጋቾችን ማዘጋጀት፤
- በገጽ ለገጽ፣ በቨርችዋል የቀጥታ ክስተቶች፣ የተቃውሞ ሰልፎች ላይ አሳታፊ እና ኃይል ሰጪ መልዕክቶችን ለማድረስ የንግግር ነጥቦችን አዘጋጅቶ ማቅረብ፤
- ከታዋቂ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ጋር ግንኙነት መፍጠር፤

3. የአስተሳሰብ አመራር፡- አወንታዊ የፖሊሲ ውጤቶችን ለማድረስ አዳዲስ ሀሳቦችን ማነሳሳት ወይም ነባር ሃሳቦችን ለማስተካከል፤

- በኢትዮጵያ ውስጥ በሕዝብ ችሎቶች ወይም በስብሰባዎች ወቅት ሊጠቀሱ ስለሚችሉ ክስተቶች በማስረጃ ላይ የተመሠረቱ ጽሑፎችን መጻፍና ማተም፤
- አዳዲስ እና/ወይም ነባር ሀሳቦችን ወይም እንቅስቃሴዎችን ማበርከት (ለምሳሌ #NoMore, #BreakThe Silence) የኢትዮጵያውያን ዳያስፖራ ማህበረሰብ እና የኢትዮጵያ ወዳጆች በታለመለት አላማ ዙሪያ እንዲሰለፉ ማሳወቅ እና ድጋፍ ማግኘት፤
- አዝማሚያዎችን እና የፖሊሲ አንድምታዎችን ለመለየት የሚዲያ ክትትልን ጨምሮ በታለመላቸው አካባቢዎች ንቁ ምርምር (ለምሳሌ ታሪካዊ እውነታዎች፣ ክስተቶች፣ የህዝብ አስተያየት) በማካሄድ ፀረ-ኢትዮጵያ ትረካዎችን ለመቋቋም እና ለመለወጥ የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ ግኝቶችን በተገቢው መድረኮች (ለምሳሌ ጋዜጦች፣ ዜና መጽሄቶች፣ የምርምር ህትመቶች፣ ዊኪፔዲያ፣ ድረ-ገጾች፣ ብሎጎች) ማሳተም፤
- ከታዋቂ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ጋር በመተባበር እንደ ተወያዮች ወይም አቅራቢዎች የቀጥታ ዝግጅቶች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፤

## የድርጅቱ ተሳትፎዎች፤

⁜ ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ድምጽ  (GLEAN) ስትራቴጂካዊ ባለድርሻ አካላትን በማስተማር እና ከህዝብ ጋር ግልጽ ውይይት በማድረግ መድረኮችን በማዘጋጀት ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ፣ ስትራቴጂካዊ ጥቅሞች እና የተሳሳቱ መረጃዎችን መዋጋት የሚያስችሉ  ዓለም አቀፍ ግንዛቤ የመፍጠር፤ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከህግ እና ፖሊሲ አውጪዎች ጋር በመወያየት በኢትዮጵያ እና በአለም አቀፉ ማህበረሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት በጋራ በመከባበር፣ በጋራ ግቦች እና በአለም አቀፍ ህግጋት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲጠናከር የሚያግዙ ምክክሮችን አድርጓል፤

⁜ በኢትዮጵያ እና በአለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ቁርጠኛ ከሆኑ ግለሰቦች እና ቡድኖች ጋር ስትራቴጅካዊ ጥምረት የመፍጠር፤ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች በአንድነት እንዲሰባሰቡ እና የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ አንድነት ያለው መልእክት እንዲያስተላልፉ የማድረግ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ይገኛል፤

⁜ የኢትዮጵያ መንግስት የህግ የበላይነትን የማስመለስ እንቅስቃሴ ከጀመረበት እ.ኤ.አ. ከህዳር 2020 አጋማሽ ጀምሮ የቮተርቮይስ ዘመቻ በማስተባበር ከ150 በላይ ከሚሆኑ ጋዜጠኞች እና ከዩናይትድ ስቴትስ ኮንግረስ አባላት ጋር በመነጋገር  የኢትዮጵያን መንግስት ህግ የማስከበር ዘመቻን በአወንታዊነት እንዲረዱ የሚያደርግ ስራ አከናውኗል፤

⁜  በተጨማሪም ጋዜጠኞች እና የአሜሪካ መንግስት ተወካዮችን ጨምሮ ከ150 በላይ ተሳታፊዎች የተገኙበት ጋዜጣዊ መግለጫ ያካሄደ ሲሆን፣ በአሜሪካ መንግስት የተያዙ የተሳሳቱ ትርክቶችን የማስተካከል እንቅስቃሴ አከናውኗል፤

⁜ በአለም ፖለቲካ ኢንስቲትዩት የተደገፈ "ኢትዮጵያ በ2021፡ ተግዳሮቶችን መፍታት እና የወደፊትን ጊዜ ማየት" በሚል ርዕስ ዶ/ር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ፣ ብሮንዋይን ብሩተን፣ ዮሴፍ ሙሉጌታ፣ በሱ ፈለቀ እና ፕሮፌሰር ጆን አቢንክ የተሳተፉበት እና ፕሮፌሰር ሃሽም መኪ ያስተባበሩት የፓናል ውይይት በማካሄድ በኢትዮጵያ ወደ ሰላም እና መረጋጋት የሚደረገውን ሽግግር እና የኢትዮጵያ መንግስት የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚያደርገውን ጥረት አወንታዊነትን የማጉላት ስራ ማከናወን ችሏል፤

⁜ በተበሳሳይ ጭብጥ በቨርጂኒያ፣ ሜሪላንድ፣ ካሊፎርኒያ፣ ቴክሳስ፣ ኢሊኖይ እና ጆርጂያ ግዛቶች ውስጥ ከአሜሪካ ኮንግረስ ሰራተኞች ጋር ከሃያ በላይ ስብሰባዎችን ማካሄድ ችሏል፤

⁜

"የኢትዮጵያ ሰላም፣ መረጋጋት እና ዴሞክራሲን ይደግፉ" በሚል ርዕስ የቮተርቮይስ ዘመቻ መርቷል። በተቀናጀ ዘመቻው ከ12,000 በላይ ኢትዮጵያውያን አሜሪካውያን በአሜሪካ ኮንግረስ ላሉ ወኪሎቻቸው የኢሜል መልእክት እንዲልኩ አድርጓል፤

⁜ ታዋቂው የፊልም ዳይሬክተር ፕሮፌሰር ኃይሌ ገሪማ በታደሙበት የአድዋ ድልን የሚዘክር መርሃ ግብር በማዘጋጀት በአሜሪካ የሚኖሩ ከ300 በላይ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከታሪካቸው ጋር የማስተሳሰር ስራ አከናውኗል፤

⁜ "በኢትዮጵያ ላይ የሚጣሉትን ያላግባብ ማዕቀብ ተቃወሙ" በሚል ርዕስ ዘመቻ በማድረግ በመላው ዩናይትድ ስቴትስ ከ12,000 በላይ ኢትዮጵያውያን አሜሪካውያን በኮንግረስ ላሉ ወኪሎቻቸው የኢሜል መልእክት እንዲልኩ አስችሏል።

⁜  የአሜሪካንን የተሳሳተ የውጭ ፖሊሲ የመቃወም ከ12,000 ሺህ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን አሜሪካውያን የተሳተፉበት "ኖ ሞር" (#No More) የመራጮች ድምጽ ዘመቻ እና በርካታ የተቃውሞ ግልጽ ደብዳቤዎችን ለኮንግረስ አባላት እንዲደርስ በማድረግ የአሜሪካ መንግስት በኢትዮጵያ ላይ በያዘው ኢፍትሃዊ አቋም ላይ ጫና ማሳደር ተችሏል፤

⁜  የGLEAN አባላት በኢትዮጵያ እና በዩናይትድ ስቴትስ መካከል በመተማመን እና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ አዎንታዊ እና ቀጣይነት ያለው ግንኙነት እንዲቀጥል ለመደገፍ ያለመ ኤኢፒኤሲ (የአሜሪካ የኢትዮጵያ ህዝብ ጉዳይ ኮሚቴ) እንዲቋቋም የበኩሉን አበርክቶ አድርጓል።

## 33. ኢትዮጵያ ትቀጥላለች (Ethiopia Shall Continue, ESC)

**ETHIOPIA SHALL CONTINUE (ESC)**

**ኢትዮጵያ ትቀጥላለች**

**ITOOPHIYAAN ITTI FUFTI**

ኢትዮጵያ ትቀጥላለች (Ethiopia Shall Continue, ESC) በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ስምምነት፣ አብሮነት እና የህብረተሰብ ብልፅግናን ለማስፈን ይረዳ ዘንድ በአሜሪካ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን አሜሪካውያን የተመሰረተ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ነው።
በኢትዮጵያ ክልሎች ውስጥ ያሉ ህዝቦች በመከባበር እና በመፈቃቀር በአብሮነት እንዲኖሩ፣ ሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ ግንኙነቶች እንዲዳብሩ ማበረታታት የኢትዮጵያ ትቀጥላለች (ESC) ዋና ተልእኮ ሲሆን፣ ማህበረሰቡ ሊታረቁ የሚችሉ ዲሞክራሲያዊ እሴቶችን ተቀብሎ እንዲያጎሎብት እና ለልማት እንዲያበረታታ የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች እና ዓላማዎች ላይ ተመስርቶ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል።

❖ በአገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ በፖሊሲ እና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ድምፁን በማጠናከር የሲቪል ማህበረሰብ ሚናን ማሳደግ፤

❖ በሕዝብ ፖሊሲዎች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር በሲቪል ማህበረሰብ ተዋናዮች እና በክልል የመንግስት ተቋማት እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ የሲቪል ውይይቶችን ማበረታታት፤

❖ የሲቪል ማህበረሰብ ተዋናዮችን ተሳትፎና ተጽዕኖ ለማሳደግ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ለአገር የሚደረግ ድጋፍና ጥብቅና እንዲኖር ማድረግ ፤

❖ በኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት ማቀናባበር፣ መስተባበር እና ማጠናከር፤

### የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

❖ መረጃን ለማሰራጨት እና የሲቪል ማህበረሰቡን ዕይታ ለማሳደግ ለታዋቂ ኢትዮጵያውያን፣ ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨጫ ኮንፈረንስ አዘጋጅቷል፤

❖ በበርካታ የሚዲያ ፎረሞች ላይ ከሌሎች የኢትዮጵያ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የነቃ ተሳትፎ አድርጓል፣

❖ በግጭት እና በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ገንዘብ በተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ መንገዶች በማሰባሰብ ተጨባጭ የምግብ እና የቁሳቁስ ድጋፍ አድርጓል፤

❖ አባላቶቹን በማስተባበር ለታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የገንዘብ ድጋፍ አሰባስቧል፤

❖ ዳያስፖራው የትውልድ አገሩን እድገት መደገፍ የሚያስችሉ የልምድ ልውውጥ እድሎችን አመቻችቷል፤

❖ ዳያስፖራውን ከትውልድ አገሩ ጋር የሚያገናኝ ፕሮጀክት ለመጀመር በሚደረገው ጥረት ከክልል እና ከኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የበላይ ኃላፊዎች ጋር አብሮ መስራት የሚቻልበትን ሁኔታ ፈጥሯል፤

## 34. ተስፋ ለኢትዮጵያ ድርጅት
## (New York/New Jersey Tristate Hope for Ethiopia,Inc.)



የድርጅቱ ኃላፊ የአቶ አክሊሉ ታፈሰ መልዕክት፤

ውድ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጅ የሆናችሁ ሁሉ። ኢትዮጵያ በታሪክ ውስጥ ያጋጠሟትን ፈተናዎች መቋቋምና መሻገር የምትችል አገር መሆኗን በተደጋጋሚ አሳይታለች። የሚያጋጥሙንን ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ፈተናዎች መቋቋም የቻልነው እና ኢትዮጵያ በሉዓላዊነቷ ለዘመናት ጠላቶቿን እያሳፈረች የኖረችው በህዝቦቿ ህብረትና አንድነት መሆኑ ይታወቃል።

ዛሬም ሆነ ወደፊት የሚከፈቱብንን የተቀነባበሩ ሴራዎች ማምከን የምንችለው ቀድሞ ወደ ነበርንበት አንድነትና ህብረታችን ተመልሰን ስንመክት ስለሆነ በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ያሉንን ልዩነቶች ወደ ጎን በማድረግና ትልቁን ስዕል በማየት ባለንበት ቦታ ሁሉ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሞች መከበር የጀመርናቸውን ስራዎች አጠናክረን እንድንቀጥል ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ኢትዮጵያ ለዘለአለም በልጆቿ ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!
ድል ለመላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን!

የኒውዮርክና ኒውጀርሲ ተስፋ ለኢትዮጵያ ድርጅት በኒውዮርክ “ተስፋ ለኢትዮጵያ” በሚል ስያሜ ማርች 2021 የተቋቋመ ሲሆን፣ ከዋና ዋና ዓላማዎቹ መካከል አገራችን ኢትዮጵያ ሉአላዊነት ላይ የሚቃጡ ማናቸውንም አይነት ጥቃቶች መመከት እንዲቻል በኒውዮርክ እና ኒውጀርሲ እንዲሁም በከነትኬት አካባቢ የሚገኘዉን የኢትዮጵያ ኮምኒቲ ማስገንዘብና ማሳወቅ፣ በተለያዩ የሚዲያ ተቋማት በአገራችን ላይ የሚሰነዘሩትን ከእውነት የራቁ ዘገባዎችን መከላከል እንዲሁም የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስራዎችን በማከናወን በኢትዮጵያ ላይ ተጽእኖ መፍጠር ከሚሞክሩ አካላትን መሞገት የሚገኝበት ሲሆን፣ ለወቅታዊ ሀገራዊ ጥሪዎችም ምላሽ መስጠት የሚያስችሉ የሀብት ማሰባሰብ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል።




ድርጅቱ በኢትዮጵያ ላይ በምእራባዊያንና በውስጥ ጠላቶች እንዲሁም በተለያዩ የህዝብ መገናኛ ሚዲያዎች የተከፈቱ ሀሰተኛ ፕሮፖጋንዳዎችን በማምከንና የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ድምጽ መሆን የሚያስችሉት ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል። ከዚህም ጋር በተያያዘ የአሜሪካን ህግ ከሚያወጡት የኮንግረስ አባላት ጋር ውይይት በማድረግና ግንዛቤያቸውን በማሳደግ የተሳሳተ ፕሮፖጋንዳ ሰለባ በመሆን በኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ህጎችን እንዳያጸድቁ፣ ለሴናተሮችም ደብዳቤ በመላክ የአሜሪካ መንግስት በአገራችን ላይ እያደረገ ያለዉ ተጽዕኖ ትክክል አለመሆኑን እንዲገነዘቡና የሁለቱ አገሮች የቆየ ግኑኝነት እንዳይሻከር ትኩረት አድርገው እንዲሰሩ ለማሳሰብ የሚያግዙ ሰላማዊ ሰልፎችን አደራጅቷል፤ በጽሑፍ የተዘጋጁ መረጃዎችን አቅርቧል፤ ረቂቅ ህጎችም እንዳይጸድቁና ህግ ሆነው እንዳይወጡ ሰርቷል።

አባላትና ደጋፊዎቹን በማስተባበር ኒውዮርክ በሚገኘዉ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጽ/ቤት ደጃፍ ላይ በመገኘት ሀያላን የተባሉት አንዳንድ ምእራባዊያን አገሮች በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንዲያቆሙና እጃቸዉንም ከኢትዮጵያ ላይ እንዲያነሱ፣ እንደ CNN እና NY Times የመሳሰሉ ታላላቅ ሚዲያ ተቋማት በር ድረስ በመሄድ በኢትዮጵያ ላይ የሚያቀርቡትን ምንጩ ያልተረጋገጠ ውሸትና የተዛባ የሚዲያ ዘመቻቸዉን እንዲያቆሙ የተቃዉሞ ድምጹን አሰምቷል።







በውጪው ዓለም የአገርን ብሔራዊ ጥቅም ከማስከበር በተጨማሪ ድርጅቱ በአገር ውስጥ ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖቻችን ላይ በማተኮር ልዩ ልዩ የድጋፍ ስራዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል። ለአብነት ያህልም በግጭት ምክንይት ለተጎዱና ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን ድጋፍ የሚሆን እርዳታ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ከ52 ሺ ደላር በላይ በማሰባሰብ ልኳል። በክቡር ጠ/ሚ ዶ/ር ዐቢይ አህመድ የቀረበዉን የታላቁ ጉዞ ወደ አገር ቤት ጥሪን በመቀበል አራት የድርጅቱን አባላት ወክሎ በመላክ ባሸባሪዉ የህውሃት ቡድን ጥቃት ደርሶባቸዉ የተጎዱትን ወገኖቻችን ለመርዳት በባህር ዳር ሆስፒታል ተጠግተዉ እርዳታ በመሻት ላይ ለነበሩ 10ሺ ዶላር፤ ለደብረ ብርሃን ሆስፒታል ቁስለኞች መርጃ 10ሺ ዶላር፣ ለደሴ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል በአምስት መቶ ሃያ ሺ ብር የተገዙ (10 ሺ ዶላር የሚያወጡ) አምስት መድሃኒት ማቀዝቀዣዎች እንዲሁም ለአፋር ክልል (ዱብቲ ሆስፒታል) 10ሺ ዶላር፣ በቅርቡ የእርዳታ ማሰባሰቢያ ዝግጅት በማድረግ ጉዳት ለደረሰበት የአፋር ክልል እርዳታ የሚዉል ተጨማሪ 10ሺ ዶላር እንዲሁም በደሴ አካባቢ በወራሪዉ ሀይል ጉዳት ለደረሰባቸዉ ለተወሰኑ ሴቶች እህቶቻችን መርጃ የሚውል 5ሺ ዶላር እርዳታ በአጠቃላይ ከ107ሺ ዶላር በላይ ድጋፍ አድርጓል።



ድርጅት ለወደፊትም የጀመራቸውን የፐብሊክ ዲፕሎማሲም ሆነ የህብት ማሰባሰብ ተግባራት አጠናክሮ የመቀጠል ዕቅድ አለው።

## 35. የኒዮርክ ኒውጀርሲና ከንቲኬት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ



### የኒዮርክ፣ ኒውጀርሲና ከንቲኬት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ መልእክት፤

እኛ በኒዮርክና አካባቢው ባሉ ስቴቶች ነዋሪ የሆንን ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ህዝብ አንጡራ ሀብት እየተገነባ ያለውንና ለሚሊዮኖች የሙብራት አገልግሎት የሚሰጠውን፣ ለአገር ክብርና ኩራት የሆነውን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በገንዘብ፣ በዲፕሎማሲና በአድቮኬሲ ስራዎች ለማገዝና ለማስተባበር በመቻላችን ታላቅ ደስታ ይሰማናል።




ይህ ግድብ ለፍጻሜ እንዳይደርስ በተለያዩ አገራት ይደረግ የነበረው ግፊት አሳስቦን ቁጥራችን 20 የምንሆን የአስተባባሪው ኮሚቴ አባላት በተባበሩት መንግስታት የኢትዮጵያ ልዩ መልእክተኛ ጽ/ቤት አስተባባሪነት በመሰባሰብ የስብሰቡን የስራ እቅድ (Terms of reference) ካዘጋጀን በኋላ መጀመሪያ ለአሜሪካ የህግ አውጭ አባላትና ጉዳዩ ይመለከታቸዋል ብለን ላሰብናቸው ተቋማት ስለግድቡና በአባይ ወንዝ ተፋሰስ ዙሪያ ያሉ መረጃወችን በNewsletter/Factsheet መልክ አዘጋጅተን እንዲደርሳቸው አድርገናል።



GERD

THE GRAND ETHIOPIAN RENAISSANCE DAM: THE FACTS

The Nile is a shared water resource among eleven countries: Burundi, D.R. Congo, Egypt, Ethiopia, Eritrea, Kenya, Rwanda, South Sudan, Sudan, Tanzania and Uganda. Abbay (the Blue Nile) that originates from Ethiopia constitutes 86% of the Nile and the White Nile that originates from Lake Victoria constitutes 14% of the Nile. Blue Nile consists of two third of Ethiopia's surface water resource.

IMPORTANCE OF THE GERD FOR ETHIOPIA, EGYPT AND THE SUDAN

- The GERD will generate 5150 megawatts (MW) or 15, 692 Gigawatt hours (GWh)/year. Currently Ethiopia's demand for energy grows by 19% every year. More than sixty-five million Ethiopians do not have access to electricity. In contrast, hundred percent of Egyptians have access to electricity.

THE GRAND ETHIOPIAN RENAISSANCE DAM

- Construction officially started in April 2011.
- The largest hydroelectric generating plant in Africa.
- The sixth largest reservoir in Africa and the tenth largest in the world.
- The 5 Billion USD GERD construction cost is entirely covered by Ethiopian resources.

- From the entire population of Ethiopia, seventy percent are under the age of thirty years. Ethiopia has about thirty-two million of its population in schools at different levels of training, from which close to a hundred thousand graduates from higher education and vocational training institutions every year.
- Job and employment creation and the socio-economic wellbeing of the predominantly young population is critical for the survival and political stability of Ethiopia.
- The GERD – will accrue substantial benefits to Egypt and Sudan. Sudan with minor adjustment of its dams operations will be able to generate close to 3000 MW electricity, it will expand its irrigation agriculture by nearly forty percent, it will save the investment in silt control and removal, it will also have lesser effects from flood to worry about every year.

በአባይ ወንዝና በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ ጥናት ያደረጉና የጻፉ ምሁራንን በመጋበዝ ከአምስት ጊዜ በላይ የበይነመረብ መድረክ አዘጋጅተን አወያይተናል። ለቦንድ ግዥ የሚረዳ ብሮሸር አዘጋጅተን በድህረ ገጻችን ላይ አስቀምጠናል። የገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም በማዘጋጀትም ከ60ሺ ዶላር በላይ አሰባስበናል። በቀጣይም ለአገራችን የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን መግለጽ እንወዳለን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ህዝቧን ይባርክ።
ወንድማገኝ አዲሱ መርሻ




## በካናዳ የላቀ አበርክቶ እያደረጉ የሚገኙ የኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አደረጃጀቶች

ካናዳ ሰፊ ግዛት፣ በሁሉም መስክ በሚባል ደረጃ ከፍተኛ የተፈጥሮ ጸጋ ያላት እና ከአለማችን በጣም ኃብታም ከሚባሉት አገራት የምትሰለፍ የተረጋጋ ፖቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አኗኗር ያላት አገር ናት፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ ካናዳ ከተባበሩት መንግሰታት ጀምሮ በአህጉራዊና በክልላዊ እንዲሁም በተለያዩ ባሉብዙ መድረክ ድርጅቶች ውስጥ በአለም ፖለቲካ ተጽእኖ ፈጣሪ ከሚባሉ አገራት ተርታ ትሰለፋለች፡፡

ኢትዮጵያና ካናዳ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት የመሠረቱት እ.ኤ.አ. በ1965 ሲሆን፣ የዲፕሎማቲክ ግንኙነቱ ከመመሥረቱ በፊት የካናዳ ዜጎች በወቅቱ ዘመናዊ ኢትዮጵያን ለመፍጠር ይደረገ የነበረን ጥረት ለማገዝ በቀድሞ የተፈሪ መኰንን እና የኮተቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በማስተማርና በማስተዳደር ሥራ ላይ ተሰማርተው ነበር። የሁለቱን አገራት ዲፕሎማቲክ ግንኙነትን ለመጀመር ካናዳ እ.ኤ.አ 1967 በአዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያም በኦታዋ ኤምባሲ ከፍተዋል፡፡

ካናዳ የሰሜን አሜሪካ ግማሽ የሚሆነውን የመሬት ስፋት የያዘች አገር ስትሆን፣9,984,670 ስኩዌር ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት አላት፡፡ እንግሊዘኛ (58.7%) እና ፈረንሳይኛ (22%) የአገሪቱ ኦፊሻል ቋንቋዎች ሲሆኑ ጣልያንኛ፣ ቻይንኛ፣ ጀርመንኛ እና ሌሎች ቋንቋች በስፋት ይነገራሉ፡፡ የሕዝብ ብዛቷም 38,381,044 ደርሷል፡፡

በካናዳ ከ40ሺ በላይ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንደሚኖሩ የሚገመት ሲሆን፣ አገራቸውን በፐብሊክ እና ዲጂታል ዲፕሎማሲ እንዲሁም በሀብት ማሰባሰብና በልዩ ልዩ የምላት ስራዎች በመደገፍ ላይ ይገኛሉ። በካናዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚሳተፉባቸው ከ50 በላይ አደረጃጀቶች የሚገኙ ቢሆንም የላቀ ተሳትፎ በማከናወን ላይ ካሉ አደረጃጀቶች መካከል የኢትዮጵያ ካናዳውያን ኔትወርክ ለማህበራዊ ድጋፍ እና ጥምረት ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በካናዳ ይገኙባቸዋል፡፡

## 36. ወገን ለወገን በጎ አድራጎት ድርጅት People to people Inc (P2P)

People to People (P2P) ወይም ወገን ለወገን በጎ አድራጎት ድርጅት ለትርፍ ያልተቋቋመ እና ትኩረቱን በጤና አጠባበቅ፣ በልማት እና ትምህርት ላይ አድረጎ የሚሰራ በፍቃደኛ ሃኪሞች፣ የጤና ባለሙያዎች እና በሌላ የሙያ መስክ የተሰማሩ ባለሙያ ዳያስፖራዎች የተቋቋመ ዓለማቀፍ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ የዳያስፖራውን ማህበረሰብ እና ሌሎች የኢትዮጵያ ወዳጆችን በማስተባበር በኢትዮጵያ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት እንዲችሉ ድልድይ የመሆን ሚናንን የመወጣት ተልእኮ አንግቦ እየሰራ ይገኛል፡፡

ድርጅቱ እ.ኢ.አ 1999 በፕሮፌሰር እናውጋው ማህሪ ሃሳብ አፍላቂነት የተቋቋመ ሲሆን በሰሜን አሜሪካ በ 501(c)(3) ፍቃድ ቁጥር የተመዘገበ ሲሆን በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ ቤት ያለው ሲሆን፣ በተመሳሳይ በሰሜን አሜሪካ፣ ካናዳ፣ ስዊድን፣ ፊላንድ፣ ጀርመን እና በመላው አለም ከተባበሩት መንግስታት የኢኮኖሚ እና ሶሻል ካውንስል ጋር በአጋርነት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡









ድርጅቱ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ዳያስፖራዎችን ተጠቅሞ በታዳጊ  እና ባደጉ አገራት ተቋማት መካካል የሶስትዮሽ የኢጋርነት ግንኙነትን በማጠናከር የግብዓት፣ እውቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግረ እንዲኖር ማስቻል እሳቤ ላይ ተመስርቶ እየሰራ ያለ ድርጅት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከምእራባዊያ አገራት ሰሜን አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመን፣ ፊላንድ፣ ስዊድን፣ አውስትራሊያ እና ከአፍሪካ ቀንድ አገራት ሰሜንና ደቡብ ሱዳን፣ ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ እና ኬኒያን የሚያገናኝ ዓለማቀፍ ትስስር መስርቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ በዚህ መሰረት ባደጉ እና በማደግ ላይ ባሉ አገራት መካካል ያለውን የልማት ልዩነት በትስስር በማጥበብ በማደግ ላይ ያሉ አገራት የተሻለ ተጠቃሚ የማድረግ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡








ድርጅቱ በዋነኝነት ትኩረቱን በአፍሪካ ቀንድ ላይ አድርጎ  በማህበረ-ኢኮኖሚ፣ በባህል እንዲሁም በሰላም ግንባታ እና ጸጥታ ነክ ጉዳዮች፣ በባለሙያ ማህበራት በካካል ትስስር በመፍጠር የማህበረሰብ ልማት ስራዎች፣  ሁሉን አቀፍ የልማት ፕሮጀክቶችን እና በአገር ቤት ለሚፈጠሩ የተፈጥሮ እና ሰውሰራሽ አደጋዎች ምላሽ የሚሆኑ ዓለም አቀፍ ሃብት በማሳባሰብ የድጋፍ ስራዎችን በሰፋት ያከናውናል፡፡
የድርጅቱ ተሳትፎዎች፤

❈ እ.አ.አ በ2000 በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ቤተሰቦቻቸውን በኤድስ ላጡ ህጻናት ትምህረት ቤት የማስገንባት እና በዚሁ ዓመት የመጀመሪያ የሆነውን ዓመታዊ ስብሰባ የገና እና የኢድ አልፈጠር በአላትን ምክኒያት በማድረግ ትኩረቱን ቤተሰቦቻቸውን በኤድስ ባጡ ህጻናት ላይ ያደረገ ውይይት አካሂዷል፡፡

❈ እ.አ.አ በ2001 ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በመሆን የሶሻል ወርክ ትምህረት በሁለተኛ ድግሪ ደረጃ ለመስጠት የሚያስችል የካሪኩለም ዝግጅት ስራ አከናውኗል፤ እንዲሁም በሚዲያ ‘ዓለማቀፍ ማህበረሰብ እንፍጠር’ በሚል መሪ ቃል የሚዲያ እና የፊልም ዝግጅት ስልጠና ለታዳጊ ህጻናት መስጠት ችሏል፡፡

❈ እ.አ.አ 2002 የጸረ ኤድስ ክለብ ፕሮጀክት ምስረታ እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የኤድስ ስርጭትን በመቀነስ ረገድ የእነዚህ ክለቦች ውጤታማነት ላይ ያተኮረ ጥናት አካሂዷል፡፡ በዚሁ ዓመት የዳያስፖራ የጤና ባለሙያዎች እና ሶሻል ወርከሮችን ያሳተፈ  ጤናችን ግድ ይለናል (Health Matters) ዓለም አቀፍ  ውይይት አካሂዷል፤ በተመሳሳይ የኤች አይቪ ኤድስ ካውንስሊንግ መሰረታዊያን እና የባህሪ ለውጥ በማምጣት የኤድስን ስርጭት መቀነስ የሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ወርክሾፕ አካሂዷል።

❈ እ.አ.አ 2003 የኤች አይ ቪ ኤድስ ታማሚዎች ድጋፍ እና እንክብካቤ ላይ ያተኮረ ስልጠና፣ በአፍሪካ አንድ የኤድስ ስርጭት ላይ ያተኮረ ጆርናል ህትመት፤ የመጀመሪያው የወገን ለወገን የህክምና ስራዎች እውቅና መድረክ አከናውኗል።

❈ እ.አ.አ 2005 People's Clinic opens in Morehead, KY, USA ከፍተዋል እንዲሁም በጤና ጥበቃ ሚንቴር እና ፒፍዘር ፋውንዴሽን መካከል አጋርነት እንዲፈጠር እና  የጤና አገልግሎት አቅርቤት እንዲሸሻል በማድረግ የአንቲ ፈንጋል መድሃኒቶች ስርጭት የማሳደግ ስራ አከናውኗል፡፡

❈ እ.አ.አ. በ2006 Neurology Training Program: A P2P-supported neurology fellowship at Addis Ababa University እና CNS Involvement in the HIV Population in Ethiopia: A Post-mortem Forensic Study ስልጠኛዎች ሰጥቷል፡፡

❈  እ.አ.አ በ2007 ዳያስፖራዎች በስፋት የተሳተፉበት የወጣቶች ጤና ፕሮግራም አስጀምሯል፡፡

❈ እ.አ.አ በ2008 ወርሃዊ የማህበረሰብ ጤና መረጃ ስርጭት ቡድን ማቋቋም እና የዳያስፖራ ዶክተሮች ዳታ ቤዝ፤ እንዲሁም በመላው ዓለም የሚገኙ የጤና ባለሙያ ዳያስፖራዎች ትስስር መመስረት ችሏል፡፡

❈  እ.አ.አ 2009 የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ፕሮጀክትን ማጠናከር እና የመጀመሪያው ዓመታዊ የጤና እንክብካቤ እና የህክምና ትምህረትበ ጉባኤ አካሂዷል፡፡

❈ እ.አ.አ. በ2010 ዓለም አቀፍ የኒውሮኢንፌክሺየስ በሽታ ኮንፈረንስ በአዲስ አበባ አካሂዷል፡፡

❈ እ.አ.አ. በ2011 የኢትዮጵያ ዳያስፖራ የጤና እና የትምህርት ባለሙያዎች ንቅናቄ ፕሮጀክት አዘጋጅቷል።

❈ እአ.አ. በ2012 የኢትዮጵያ ህክምና ታሪክ ማንዋልን አዘጋጅቷል።

❈ እ.አ.አ በ2013 ላከናወናቸው ስራወች በአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት እውቅና አግኝቷል።

❈ እ.አ.አ. በ2016 በኢትዮጵያ የካንሰር ክትትልን ለማሻሻል የተዘጋጀውን ፕሮጀክት የመጀመሪያ ክፍልን አስጀምሯል።

## 37. ድር ኢትዮጵያ አለም አቀፍ የሙሲሊሞች ድርጅት



በድር ኢትዮጵያ አለም አቀፍ የሙሲሊሞች ድርጅት በአሜሪካ፣ በካናዳና በአውሮፓ 27 ኮምዩኒቲዎችን አሰባስቦ በአራት መርሆ ላይ በመመስረት በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ድርጅቱ ባሳለፋቸው ሃያ ሁለት አመታት ለኢትዮጵያ እድገትና ልማት ይረዳሉ ባላቸው ጉዳዮችም ላይ ከመንግሰት ጋር ውጤታማ ውይይት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡
የበድር ኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት አቶ አህመድ ወርቁ መልእክት፤

*መቀመጫውን በሰሜን አሜሪካን ያደረገውና ከተመሰረተ 23 አመቱን የያዘው በድር ኢትዮጵያ የኢትዮጳያ ሙስሊሞች ተቋም በአገራችን የልማትና የዕድገት እንቅሰቃሴዎች ላይ ቀጥተኛ ተሣታፊ ከሆነ አመታትን አሰቆጥሯል።*

*በለውጡ መባቻ ክቡር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አቢይ አህመድ አሜሪካ መጥተው በነበረ ጊዜ በ18ኛው የበድር አለም አቀፍ ጉባኤያችን ላይ ተገኝተው ዳያስፓራው በሀገሩ ጉዳይ ቀጥተኛ ተሣታፊ እንዲሆን ከፍተኛ ማነቃቂያ ሊሆን የሚችል ጥሪ ባስተላለፉበት ወቅት በድር ኢትዮጵያም ላለፉት 21 አመታት በሰሜን አሜሪካን ሲያደርግ የነበረውን አመታዊ ኮንፈረንሱን ለመጀመሪያ ግዜ በሀገሩ በኢትዮጵያ ምድር 22ኛ አመት ኮንፈረንሱን ለማድረግ አቅዶ እጅግ የተሳካ ፕሮግራም አከናውኗል። ለፈጣሪያችን ምስጋና ይግባውና!*

*በድር ኢትዮጵያ ወደ ቤቱ ሲመጣ ጉባኤውን ብቻ አካሂዶ ሊመለስ አይደለም። ለሀገራችን ይጠቅማሉ ያልናቸውንና ያዘጋጀናቸውን ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ተግባራዊ ለማድረግ በመዘጋጀትም ጭምር እንጂ። ለዚህም እንዲረዳው በኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት አመቻችነት በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች ከሚገኙ የተለያዩ የመንግሥት ሃላፊዎች ጋር ውይይቶችን አድርጓል። በውይይታችን መሰረትም መንግሰት ለአሰራር ምቹ ሁኔታ ይፈጥርልናል ብለን እናምናለን።*

*በድር ኢትዮጵያ ከሀያ በላይ የሆኑ ተቋሞች በሰሩ ያሉ በመሆኑ ቀድሞ ሲሰራቸው የነበሩትንም በማጠናከርም ሆነ አዳዲስ የልማት ውጥኖቹን በተለያዩ ክልሎችም ለማከናወን ጥናቶችን የሚያደርግ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ፅ/ቤት በመክፈት እንቅሰቃሴውን በቅርቡ ለመጀመር በሚያስችለው መንገድ ላይ ይገኛል ።*

*በድር ኢትዮጲያ በ22ኛው ጉባኤ በህዳሴው ግድብ ሶስተኛ ሙሌት፣ በሀገራችን ዘላቂ ሰላም ሂደት እና እየተከናወነ ስላለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በቂ መረጃ አግኝቷል፤ የበኩሉን ለማበርከትም ተስፋ አድርጎ ውጥን ይዟል።*

*በዳያስፖራ ከሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ተቋማት የህዳሴ ግድብን በላቀ ደረጃ ከሚደግፉት በድር ኢትዮጵያ ግንባር ቀደሙ እንደሆነ ይታወቃል። ለዚህም ከተለያዩ የመንግስት ኣካላት ከፍተኛ እወቅና ተችሮታል። ከዚህም በተጨማሪ አንድ ዳያሰፖራ ለአንድ ቤተሰብ መርሃግብር እና በጦርነት እና በሰላም ማጣቱ ጉዳት ለደረሰባቸው አካባቢዎች በአካል በመገኘት ድጋፍ ማድረግን ጨምሮ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ሀገራቸውን የሚያውቁበት ሁኔታ አመቻችቶ አመርቂ ስራ ሰርቷል።*

*ከጉባኤያችን በተጓዳኝ የሴቶችና የወጣቶች ፕሮግራም አዘጋጅቶ የተለያዩ የጎንዮሽ ሰብሰባዎች፣ ሰምምነቶች እና ጉብኝቶች አከናወኗል። ጥሩ የሆነ ግንዛቤ ማስጨበጥና መጨበጥ የተቻለበት ድንቅ ግዚያትን በሀገር ቤት አሳልፈናል።*

*ይህ ጉባኤ እንዲሳካ ድጋፍ ያደረጉትን ሁሉ እያመሰገንን በተለይም በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠ/ሚ/ር ፅ/ቤት፣ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር፣ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት እና የ አ/አ መስተዳድር እንዲሁም የሚዲያ አካላትና ሌሎች ያልገለፅናቸውን ሁሉ በበድር አለም ዐቀፍ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ድርጅት ሰም ከፍ ያለ ምሰጋናችንን እናቀርባለን።*








## የድርጅቱ ተሳትፎዎች፤

◈ ህብረተሰባችን የኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ ሰለባ በሆነበት ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ አሰባስቦ በአዲስ አበባና አከባቢዋ በ5 ወረዳዎች ለሚገኙ እምነትን ያላማከለ በሺዎች ለሚቆጠሩ ወገኖች ለአንድ ወር የሚበቃ ቀለብ አከፋፍሏል፡፡

◈ ክቡር አቶ ፍጹም አረጋ በአሜሪካ የኢፌደሪ ባለ ሙሉ ስልጣን አምባሳደር የበድር ቦርድ ሊ/መንበር አቶ አህመድ ወርቁ ላሳዩት የአመራር ብቃት ዋሺንግተን ዲሲ ከሚገኘው የኢትዮጵያ የእውቅና የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል፡፡

◈ በድር ኢትዮጵያ ከአባይ ንጉሶች እና ከኤምባሲዎች ጋር በመተባበር ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የ' Go fund me' አካውንት በስሙ በመክፈት የተሰበሰበውን $ 1,050,000. (አንድ ሚሊዮን ሃምሳ ሺህ የአሜሪካን ዶላር)
ለዚሁ ተብሎ በኢትዮጵያ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ በመላክ ማረጋገጫ አቅርቧ፡፡

◈ የህዳሴን ግድብ በሚመለከት ጸጥታው ምክር ቤት ኢ. ፍትሃዊ ሆነ መንገድ ለግብጽ ባደላ መልኩ ተደጋጋሚ ስብሰባዎችን ሲጠራ፣ ድርጅታችን ይህን ድርጊት በመቃወም ለፀጥታ ምክር ቤት፣ ለአውሮፓ ህብረት፣ ለአፍሪካ ህብረት 57 ሃገራትን በአባልነት ላቀፈው አለም አቀፍ የሙስሊም ሃገራት ድርጅ ደብዳቤ ፅፏል፡፡

◈ ለህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ዙር ውሃ ሙሌት ኢትጵውያንና ትውለደ ኢትዮጵያንን በማስተባበር ከአንድ ሚሊዮን ዶላር በላይ አሰባስቦ ለታለመለት አላማ ገቢ አድርጓል፡፡

◈

ለኢስላማዊ ባንክ መቋቋሙና ለመጅሊስ ተቋም ምስረታ በለውጡ መንግስት በአዋጅ እውቅና እንዲያገኝ ድጋፍ አድርጓል፡፡

◈ የኢትዮጵያ መጅሊስ አጣዳፊ ችግሮችና አማራጩ መፍትሄ የሚል ባለ 208 ገጽ መፅሀፋት አስጠንቶ በjuly 2012 አሳትሟል፡፡

◈ ማዕከሉ ባደረገው በሰሜን አሜሪካ ማለትም የአሜሪካ ተለያዩ ግዛቶችና ካናዳን ጨምሮ በየአመቱ በሚደረገው ጉባኤ ላይ የገንዘብ ማሰባሰብ መርሃ ግብር በማኪያሄድ አዘጋጅቶ ኪምኒቲዎች የራሳቸው ማዕከል ባለቤት እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

◈ የሃገር ቅርጽና ንብረትም በሚመለከት በጂቡቲ በኩል ወደ ውጭ ተሸጠው ሊወጡ የነበሩ በርካታ ኢስላማዊ ቅርሶች በደረሰው መረጃ ተከታትሎ ከነጋዴዎች በራሱ በጀት በመግዛት ዛሬም ድረስ በበድር ስም ተመዝግቦ በአዲስ አበባ ሙዚየም ውስጥ በክቡር እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

◈ በደቡብ ኢትዮጵያ ለነበረው ድርቅ የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል፡፡ በተለያዩ ክልሎች የዘካ ገንዘብ በመላክ አከፋፍሏል፡፡ በተጨማሪም የህክምና መሳሪያዎችና የተለያዩ ቁሳቁሶች ወደ ሃገር ቤት ልኳል፡፡

◈ በተቃጠሉበት መስጊዶች ምትክ አማካኝ በሆነ በጉራጌ ዞን በአክሊል ወረዳ በምሁር ሁሉን የሚያሰባስብ መስጊድ ገንበቶ አስረክቧል፡፡ በደቡብ ክልል በሳዳ ከተማ ባለ ስምንት ክፍል ት/ቤት ገንብቶ ለነዋሪው አበርክቷል፡፡






## 38. የኢትዮጵያ ካናዳውያን ኔትወርክ ለማህበራዊ ድጋፍ
## የኢትዮጵያ ካናዳውያን ኔትወርክ ለማህበራዊ ድጋፍ (ኢክናስ) ፕሬዚዳንት መልዕክት፤



የኢትዮጵያ ካናዳውያን ኔትወርክ ለማህበራዊ ድጋፍ (ኢክናስ)ን ወክዬ መልዕክት የማስተላለፍ ዕድል ስላገኘሁ የተሰማኝን ደስታ መግለጽ እወዳለሁ። ኢክናስ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን፣ ዓላማውም ኢትዮጵያን በአድቮኬሲና በአስቸኳይ ጊዜ የሀብት አሰባሰብ ተግባራት ማገዝ ነው። የድርጅቱ ራዕይም በኢትዮጵያና ካናዳ መካከል የትብብር መንፈስን በማጎልበት ለኢትዮጵያውያን ሰላምና ደህንነት፣ ማህበራዊ ፍትህና ዘላቂ ልማት መስራት ነው። ድርጅታችን በሰሜን ዕዝ ላይ የተፈጠረውን ጥቃትና  በአካባቢው በሚኖሩ ህዝቦች ላይ የተከሰተውን ጉዳት ለመከላከል በቆረጡ አባላት ከተቋቋመበት ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ባከናወናቸው ተግባራትና በተገኙ ውጤቶች  ደስታ ይሰማኛል።

ድርጅታችን “ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” የሚለውን መርህ  መሰረት በማድረግ ግጭቱን ተከትሎ በኢትዮጵያ ህልውና ላይ ሲሰነዘሩ የነበሩ ዲፕሎማሲናዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎችን ለመመከት በመላው ዓለም የሚገኙ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድኖችን በመቀላቀል ድምጹን አሰምቷል። ከፐብሊክ ዲፕሎማሲ ትግሉ በተጓዳኝም የኢትዮጵያን ልማት የሚያግዙ በርካታ የሀብት ማሰባሰብ ተግባራት ላይ በንቃት በመሳተፍ ላይ ይገኛል። ከነዚህም መካከል ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሀብት ማሰባሰቢያ፣  በግጭት ለተጎዱ አካላት የህክምና መሳሪያዎችና ገንዘብ ድጋፍ፣ ለተፈናቀሉ ሰዎች ቤት መስሪያ የሚሆን ገቢ ማሰባሰቢያ መርሀ ግብር ይገኙባቸዋል። በዚህም በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ብቻ በካናዳ ያሉ አስራ አንድ ቻፕተሮቻችን በመጠቀምና በመላው ካናዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር ከአምስት ሚሊዮን የካናዳ ዶላር በላይ ማሰባሰብ ችለናል። ከተሰባሰበው ሀብትም ሶስት ሚሊዮን የካናዳ ዶላር የሚያወጡ የህክምና ቁሳቁሶች እና ሁለት ሚሊዮን የካናዳ ዶላር የሚያወጡ ልዩ ልዩ ድጋፎችን በግጭት ምክንያት በአማራና አፋር ክልሎች ለተፈላቀሉ ዜጎች ማድረስ ተችሏል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የተካሄዱ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ትግሎችን በመቀላቀልም የኢትዮጵያን ድምጽ ከማሰማት ባሻገር የካናዳ ፓሊሲ አውጭዎችና ምሁራን በኢትዮጵያ ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ልዩ ልዩ መድረኮችን አመቻችተናል። ያለፉት ሁለት አመታት ድርጅታችን ኢክናስ ካሰባሰበው ሀብትና ካከናወናቸው የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስራዎች ባልተናነሰ በካናዳ፣ አሜሪካና አውሮፓ ከሚገኙ ወዳጆች ጋር እንዲተዋወቅና ጠንካራ ትስስር እንዲፈጥር አስችለውታል። በተፈጠረው ትስስርም በሀገራችን ላይ ተቃጥተው የነበሩ ጫናዎችን በጋራ ማርገብና ድምጽ መሆን በመቻላችን ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል።

ባለፉት ሁለት አመታት አብረውን ለሰሩና ለስኬታችን ምክንያት ለሆኑ በካናዳም ሆነ በሀገር ቤት ላሉ አካላት በተለይም ለካናዳውያኑ ፕሮፌሰር አን ፊዝጂራልድ እና ለጄፍ ፒርስ ምስጋናችንን ማቅረብ እፈልጋለሁ። ለመላው የድርጅታችን አባላትና አስራ አንዱ ቻፕተሮችም ጥረታችን ላስገኘው ውጤት ወሳኝ አካላት ናችሁና እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እወዳለሁ።

በመጨረሻም ኢትዮጵያውያን በያለንበት በፈተናዎች ሳንበገር አንድነታችንን እንድናጠናክርና በጋራ እንድንቆም እየጠየቅሁ፣ መጪው ጊዜ ብሩህ እንዲሆንልን መልካም ምኞቴን መግለጽ እፈልጋለሁ። ኢትዮጵያ በልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኖራለች!

አመሰግናለሁ

ዶ/ር ትሁት አስፋው



የኢትዮ-ካናዳውያን የአድቮኬሲ እና የድጋፍ ድርጅት (ECNAS) የተመሰረተው እ.ኤ.አ. በህዳር 2020 ህወሀት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ብሔራዊ መከላከያ ኃይል ላይ ያደረሰውን ጥቃት ተከትሎ በአገራችን አንድነት ላይ የተከሰተውን አደጋ ለመመከት ነው።





ማህበሩ በዋና ዋና የካናዳ ከተሞች 12 ቻፕተሮች ያሉት ሲሆን፣ በኢትዮ-ካናዳውያን እና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል ያለውን ግንኙነት ማጠናከር፣ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት መንግስት የሚያደርገውን ጥረት መደገፍ፣ በኢትዮጵያ ላይ የሚነዙ የሀሰት እና የተሳሳቱ መረጃዎችን መከላከል፣ በአገር ውስጥ ሰብአዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸ የህብረተሰብ ክፍሎች ሀብት ማሰባሰብና መርዳት እንዲሁም የተጎጅዎች ድምፅ መሆን ከዓላማዎቹ መካከል ይገኙበታል።
የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

❈ ማህበሩ ለካናዳው ጠቅላይ ሚኒስትር ጀስቲን ትሩዶ እንዲሁም ለካናዳ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ቢሮ ስለ ኢትዮጵያ ትክክለኛ እና ወቅታዊ ሁኔታ የሚያስረዱ ደብዳቤዎችን ልኳል፤

❈ ከተለያዩ ፓርቲዎች የፓርላማ አባላት ጋር ተወያይቷል፤ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ እና ቃለ-መጠይቆች ሰጥቷል፤

❈ ግንዛቤ የሚፈጥሩ ቪዲዮዎችን በማዘጋጀትና መሠረታቸውን ሰሜን አሜሪካ ካደረጉ ሌሎች የኢትዮጵያ ማህበራት እና ድርጅቶች (GLEAN እና AEPAC) ጋር ግንኙነት በመፍጠር በንቃት በመስራት ላይ ይገኛል፤

❈ በመንግስት የቀረቡ ወቅታዊ አገራዊ ጥሪዎችን እና ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ ከፍተኛ ሀብት የማሰባሰብ ተግባራት ተከናውነዋል። በዚህም መንግስት ለሚያከናውነው የሰብአዊ ድጋፍ ስራ 287,000 የካናዳ ዶላር፣ ግምታቸው 3,475,000 የካናዳ ዶላር የሆኑ የሕክምና መሣሪያዎች እና መገልገያዎች እንዲሁም ከ'Alliance for GERD' ጋር በመተባበር 400,000 የካናዳ ዶላር ድጋፍ አሰባስቧል፤

❈ እ.ኤ.አ. 14 Jan 2022፣ በሰሜን ሸዋ፣ አጣዬ በግጭት ምክንያት ለተፈናቀሉ ወገኖች ቤት ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ ጥሏል፤

❈ ከኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ጋር በመተባበር በአፋር ክልል ለተፈናቀሉ ወገኖች 130,850 የካናዳ ዶላር ድጋፍ አድርጓል፤

❈ ከሸዋ የሠላምና ልማት ማሕበር ጋር በመተባበር ለደብረብርሀን ሆስፒታል፣ በጦር ግንባር ተሰልፈው በሠላም ማስከበር ዘቻው ጉዳት ለደረሰባቸው ወታደሮች እና ሲቪሊያን ወደ 156,000.00 የካናዳ ዶላር፣ ለባህር ዳር፣ ጎንደር እና ደብረ ታቦር 190,850 የካናዳ ዶላር ፣ ለወሎ 110,250 የካናዳ ዶላር ፣

❈ በአጠቃላይ ማህበሩ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ 4.5 ሚሊዮን የካናዳ ዶላር አሰባስቧል፡፡





## 39. ጥምረት ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በካናዳ Alliance for GERD in Canada (AFGIC)

ጥምረት ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በካናዳ በካናዳ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በ2020 የተቋቋመው የኢትዮ-ካናዳዊያን ማሕበር ሲሆን፣ በካናዳ የሚገኙ ዳያስፖራዎችን በማስተባበር ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን በአድቮኬሲ እና በክራውድ ፈንዲንግ (Crowd Funding) መደገፍ ነው፡፡ ጥምረቱ ከመመስረቱ በፊት ኢትዮ-ካናዳውያንን እና ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን የተመለከቱ ስራዎችን የሚያስተባበር ቋሚ አካል አልነበረም።

የማሕበሩ ዋና ዋናዎቹ ተልዕኮ እና አላማዎች ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ትክክለኛ መረጃ ለዳያስፖራው፣ ለካናዳ መንግስት እና ለካናዳ ህዝብ ማቅረብ ነው።

ጥምረቱ አራት የስራ አስፈፃሚ ቦርድ አባላት፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ በካናዳ ዋና ዋና ከተሞች የተቋቋሙ 11 የአካባቢ ቻፕተሮች እና ተግባራቱን የሚመራ እና የሚያስተባብር ሙያዊ ግብረ ሃይል አለው።

| | | | |
|---|---|---|---|
|  |  |  |  |
| Dr. Fisaha Unduche, P. Eng. | Dr. Getu Biftu, P. Eng. | Mr. Semaneh Jemere | Mr. Behailu Atnafu |

### የማህበሩ ተሳትፎዎች፤

- ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ዓላማዎቹን ለማሳካት በርካታ ስኬታማ ተግባራትን አከናውኗል፤

- በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን ለማረም በካናዳ ከሚገኙ የሚዲያ አውታሮች የተገኙ የተሳሳቱ መረጃዎችን በመረጃዎች፣ በትክክለኛ እና ሳይንሳዊ መንገድ በማቅረብ ሞግቷል፤

- በካናዳ ለሚገኙ ኢትዮ-ካናዳውያን እና በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የኢትዮጵያን የኢነርጂ ልማትና የአካባቢ ጥበቃ ዋና አካል የሆነውን ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን ለመደገፍ የሚያስችል መደበኛ መድረክ ፈጥሯል፤

- ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቴክኒካዊ እንዲሁም ከ400,000 በላይ የካናዳ ዶላርን በቀጥታ የገንዘብ መዋጮ እና 100,000 ዶላር የካናዳ ዶላር የቦንድ ግዥን እንዲገዛ አድርጓል፤

- በመዋቅሩ ውስጥ ቴክኒካዊ እና ሙያዊ ግብረ ሃይል በማቋቋም በግብፅ እና በሱዳን ባለሙያዎች እና የሚዲያ አውታሮች ሲፈጸሙ የነበረሩ የተሳሳቱ ትርክቶችን ተከላክሏል፣

- ጋዜጣዊ መግለጫዎችን፣ የተቃውሞ ደብዳቤዎችን እና የመገናኛ ብዙሃን ቃለመጠይቆችን በማዘጋጀት የካናዳ ህዝብን ለማስተማር በተለይም ኢትዮጵያ በወንዞቿ እና በአፈርዋ ላይ የውሃ ግድብ የመገንባት ተፈጥሯዊ መብት እንዳላት አጽንኦት ሰጥቶ ታግሏል፤

- ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአምስት አመታት ግቦች ላይ የኃይል አቅርቦትን ለማሳካት አሁንም የኤሌክትሪክ ሃይል የሌላቸውን 60 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን ለማርካት የምታደርገውን ጥረት እንድታሳካ ተሟግቷል፤

- ባቋቋመው የባለሙያዎች ቡድን አማካኝነት ለወደፊት ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ምርጥ ስራዎች የሚያገለግሉ የውሂብ ጎታ እና የፍሰት ትንበያ መሳሪያዎችን (database and flow forecasting tools) በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፤

## 40. ኢትዮጵያን እንታደግ የበጎ አድራጎት ድርጅት

## ኢትዮጵያን እንታደግ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሰብሳቢ መልዕክት፤



በመላው አውስትራሊያ የምንኖር ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአውስትራሊያ ኢትዮጵያን እንታደግ የምግባረ ሰናይ ድርጅት ያቋቋምነው ኃያላን መንግሥታትና ተቋሞቻቸው በአገራችን ኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ እንጥላለን እያሉ በሚያስፈራሩበት ወቅት አገራችንን በውጪ ምንዛሪ ግኝት በመደገፍ የትምህርት፣ የጤና፣ የንፁህ ውሃና መሰል የህዝባችን ፍላጎቶችን ማገዝ ታሳቢ በማድረግ ነው። ድርጅቱን እኛ ብንጀምረውም ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን ተረክበው በተከታታይ የትውልድ ቅብብሎሽ ኢትዮጵያን የመገንባት ሥራን ለማስቀጠል ዕቅድ አለን።

አገር አልባ ሆነው በዓለም ዙሪያ የተበተኑ ትውልደ እስራኤላውያን ተደራጅተው ሃብቶቻቸውን በማሰባሰብ በ1948 ዓ/ም እስራኤልን መልሰው መፍጠር ከመቻል አልፈው ገናና አገር መገንባት ከቻሉ፤ እኛ በዓለም ዙሪያ የምንገኝ የኢትዮጵያ ተወላጆች አገራችንን እንዴት ከድህነት ማውጣት ያቅተናል ብለን ራሳችንን መጠየቅና ምላሽ መስጠት ተገቢም አስፈላጊም ነው ብለን እናምናለን። በእኛ በኩል በዓለም ዙሪያ የምንገኝ የኢትዮጵያ ተወላጆች ለዚህ ሃሳብ አፅዕኖት ሰጥተን ልንወያይበትና እንቅስቃሴ ልንጀምር ይገባል ብለን እናምናለን።

ኢትዮጵያን እንታደግ የምግባረ ሰናይ ድርጅት በዝግታ የሚያድግ፣ በጊዜያዊ የፖለቲካ ወጀቦች የማይናወጥ፤ ይልቁንም ማዕበሉንና ወጀቡን አሻግሮ በሁሉም ዘርፍ የበለፀገች ኢትዮጵያን ለማየት ያለመና ይህንንም እውን ለማድረግ የአንድ ሺውን ኪሎ ሜትር ጉዞ በአንድ እርምጃ የጀመረ አደረጃጀት ሲሆን፣ ዓላማውን ተቀብለው የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆችን በማሰባሰብ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

አበው "ድር ቢያብር፣ አንበሳ ያስር" እንዲሉ፤ ከአገራችን ርቀን በተለያዩ የዓለማችን አገሮች የምንኖር የኢትዮጵያ ተወላጆች በሙሉ ተባብረን ኢትዮጵያን እንታደግ የሚል መልዕክታችንን በዚህ አጋጣሚ ማቅረብ እወዳለሁ።

አያሌው ሁንዴሳ

እ.ኤ.አ. በ2016 በደረገ ህዝብ ቆጠራ መረጃ መሰረት በአውስትራሊያ 12ሺ የሚሆኑ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ይገኛሉ። መረጃው በአውስትራሊያ ውስጥ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከግማሽ በላይ (54 በመቶ) ማለትም ወደ 6,368 የሚሆኑት በቪክቶሪያ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ እንደሆነ ያሳያል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አገራችን እያጋጠማት ያለውን የምእራብ አገራት ተፅእኖ ለመቋቋም በአውስትራሊያ የሚገኙ አገር ወዳድ ዳያስፖራዎች በሌሎች አካባቢዎች እንደሚገኙ ዳያስፖራዎች ሁሉ የፐብሊክ ዲፕሎማሲም ሆነ በሀብት ማሰባሰብ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በዚህ ረገድ ሰፋ ያለ ስራ በማከናወን ላይ ካሉ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች መካከል ኢትዮጵያን እንታደግ የበጎ አድራጎት ድርጅት ይገኝበታል።

ኢትዮጵያን እንታደግ የበጎ አድራጎት ድርጅት
(Save Ethiopia Inc. none profit organisation)

ድርጅቱ  እ.ኤ.አ. ኦገስት 2021 ዓ.ም የተመሠረተ ሲሆን፣ ኢትዮጵያን በውጪ ምንዛሪ ማገዝና በኢትዮጵያ ውስጥ ፕሮጀክቶችን ማጥናት ወይም የተጠኑም ካሉ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ከዓላማዎቹ መካከል ይገኙበታል። ከመላው አውስትራሊያ በተወከሉ አሥራ ሦስት የቦርድ ሥራ አመራር አባላት የሚመራው ድርጅቱ  ከአባላትና ከበጎ አድራጊዎች በሚገኝ ወርሃዊ መዋጮና እርዳታ ስራውን ማከናወን የሚያስችለውን ሀብት ያሰባስባል። የሚሰበሰበውን ገንዘብም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተው የሴቭ ኢትዮጵያ የባንክ አካውንት ውስጥ በማስቀመጥ የአገራችንን የውጭ ምንዛሪ በማገዝ ላይ ይገኛል። በቀጣይነት የገንዘቡ መጠን እያደገ ሲሄድ ለተመረጡ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ለማዋል አቅዷል።

ከዚህም በተጨማሪ ድርጅቱ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተከፈተውን ጦርነት ተከትሎ የተፈናቀሉ ወገኖቻችን ለመርዳት በአውስትራሊያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በማስተባበር ከ153ሺ ዶላር በላይ አሰባስቦ ልኳል። በአሁን ወቅትም በጦርነቱ ከወደሙ ተቋሞች መካከል በጥናት የተለዩትን መልሶ ለመገንባት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል።



## THE GRAND ETHIOPIAN RENAISSANCE DAM

The GERD is located in the Benishangul Gumz region of the south western Ethiopia. It is the biggest Hydroelectric dam in Africa and the largest water body in Ethiopia built on River Abay (commonly known as Blue Nile). The place will be ideal for marine tourism; such as shing, resort development, water based sport, creating islands, etc.festivals such as Kulubi Gabriel, Aksum Mary Tsion, Irecha, Chambalala, Gishen Mariam, Ashenda, and Dire Sheik Hussein draw vast crowds



With Compliments from



IS Promotion and Specialsevents

**CEO Mr. Idris Bunsuru Abdela**

## Message of Congratulations

አይ ኤስ ፕሮሞሽን እና እስፔሻል ኤቨንትስ ውጭ በሚኖሩ ዳያስፖራዎች የተመሰረተ ድርጅት ሲሆን ትኩረት አድርጎ የሚሰራው በተለያዩ አለም ክፍል የምንገኝ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች በሚሳተፉባቸው መርሀግብሮች እና ከአለም አቀፍ ተቋማት ጋር የተለያዩ ስራዎችን የሚሰራ ተቋም ነው።

ድርጅታችን ኢትዮ-ዳያስፖራ አዋርድ የተሰኘ የእውቅና እና የመጽሀፍ ምረቃ ዝግጅት ከኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ጋር በመሆን የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሚሲዮን በሚገኙባቸው ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊ ዳያስፖራ አደረጃጀቶች ለሀገራቸው በፐብሊክ ዲፕሎማሲ በህዳሴው ግድብ ገንዘብ በማሰባሰብ ፣ በእውቀት ሽግግር ፣ በምርምር እና የተለያዩ መስኮች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ድርጅቶች የመጀመሪያ የሆነ መርሀግብር በማዘጋጀታችን የተሰማንን ላቅ ያለ ደስታ እንገልጻለን። ከሀገር ውጭ የሚገኙ ዲያስፖራዎች ምንግዜም ቢሆን ሀገራቸው ባጋጠማት የፈተናዎች ግዜም ሆነ በመልካሙ ወቅት በከፍተኛ ሞራል እና ሀገራዊ ስሜት ሰፋፊ ተግባራትን እያከናወኑ ይገኛሉ።

ስለሆነም በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች ላደረጉት እጅግ ከፍተኛ ድጋፍ እና በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ረገድ ባለመሰልቸት ባደረጉት ተጋድሎ ላስመዘገቡት አንጸባራቂ ድል ለማመስገን እና እውቅና ለመስጠት ብሎም ለቀጣይ ትውልድ ማሳያ እንዲሆን በተዘጋጀው የመጽሀፍ ምረቃ ቀን እንኳን

አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።

አይ ኤስ ፕሮሞሽን እና እስፔሻል ኤቨንትስ
ዋና ስራ አስፈጻሚ
አቶ እንድሪስ ቡንስሩ

With Compliments from

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት
ETHIOPIAN DIASPORA SERVICE


የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN DIASPORA SERVICE
እኔ ለሀገሬ ፣ ሀገሬም ለእኔ
Tel: +251 115 54 46 00 | Email: diaspora.agency@mfa.gov.et
nfo@ethiopiandiasporaagency.org | Website: www.ethiopiandiasporaagency.org
EthiopianDiasporaAgency @DiasporaAgency







Khaleej Times

<u>Message of Congratulations</u>

10th August 2022
Managing Director,
IS Promotions and special Events
Addis Ababa,
Ethiopia

Dear Sir,

COMFIRMATION TO BE A MEDIA PARTNER OF BOOK PRODUCTION BY IS PROMOTIONS AND SPECIALS EVENTS

Khaleej Times publishing firm wish to confirm it will take part in the "Ethiopia for me I for Ethiopia" book that IS Promotions and special Events is publishing

The book will published and launch in 2022 and it will highlights media opportunities in Ethiopia alongside other vital history and inform about the country

Yours Sincerely,

Harjyot Oberoi
Marketing Manager
Khaleej Times

خليج تايمز
Khaleej Times

Editorial Department
PO Box 11243, Dubai, UAE
Tel +971 4 338 3535
Fax +971 4 338 3248
Email: editor@khaleejtimes.com
www.khaleejtimes.com

كلداري للطباعة والنشر (ذ.م.م)
Galadari Printing & Publishing L.L.C.
C.R. No. 41941 ٤١٩٤١ سي.ار رقم



## *Letter of Best Wishes*

Ethiopian residents, have been at the forefront of giving back to the community, both here In UAE and in Ethiopia. Moreover, they - have been increasingly achieving great success, thereby using the fruits of their success to drive the growth and progress to all mankind.

The UAE government has always lavished praise at the Ethiopian expat community, for their role in building the modern and futuristic UAE.

I congratulate Ethiopian Diaspora for coming out with this publication, "Ethiopia for me, I for Ethiopia" which details the achievements of Ethiopia most iconic community members. This is not the first such effort from IS Promotions & Special Events who have always been enthusiastic about celebrating the accomplishments of the various community in the UAE.

I am sure that this book will serve not only as a source of pride for the Ethiopian community, but also as a source of inspiration for young and upcoming Ethiopian professionals and entrepreneurs who are driven by the dream of transforming our country into a global superpower

**Awad Mohammad Bin Shaikha Mujren**
**Director General of Emirates Travelers Festival**

GIFT
REAL ESTATE


GIFT
REAL ESTATE
Let's Start the Journey








ጊፍት ሪል እስቴት
ማህበረሰብን እንገነባለን!

ጊፍት ሪል እስቴት ለሁለት አስርት አመታት የተዋቡና ጠንካራ የመኖሪያ ቤቶችን ገንብቶ በማስረከብ በደንበኞቹ ዘንድ ተመራጭ ድርጅት ነው፡፡
የጊፍት ቢዝነስ ግሩፕ አባል የሆነው ጊፍት ሪል እስቴት እህት ኩባንያዎቹ ከሆኑት ጊፍት ትሬዲንግ፣ ጊፍት ኮንስትራክሽን፣ ጊፍት የግንባታ ዕቃዎች ማምረቻ እና ጊፍት ብረታ ብረት ፋብሪካ ጋር የግብዓትና የስራ ትስስር መፍጠሩ ጥራታቸው የላቀ ቤቶችን በተመጣጣኝ ዋጋና በወቅቱ ለደንበኞች ለማቅረብ አስችሎታል፡፡
ሲኤምሲ አደባባይ አካባቢ የሚገኘው የጊፍት መንደር ቁጥር 1 ግዙፍ እና ቅንጡ ቪላዎች ደንበኞቻችን ተረክበው መኖር ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡
ሲኤምሲ መሪ የሚገኘው የጊፍት መንደር ቁጥር 2 ግዙፍ በሆነው ከ90,000 ካሬ ሜትር በላይ በሚሰፋው ግቢ ውስጥ ገንብተን ያስረከብናቸው ቪላ እና አፓርትመንቶች ከቤቶቹ ጥራት በተጨማሪ የመኖሪያ ግቢዎቹ ውበት ጊፍት ለጥራት ምን ያክል እንደሚጨነቅ የሚመሰክሩ ናቸው፡፡
ከ57,000 ካሬ ሜትር ይዞታ በሚሰፋው የጊፍት ሶስተኛው መንደር ፕሮጀክት ከ80% በላይ የመንደሩን ግንባታ አጠናቀናል፡፡ በዚህ መንደር በርካታ ቪላ፣ ታወን ሀውስ፣ ሮው ሀውስ እና አፓርመንቶቹን አጠናቀን ለነዋሪዎች አስረክበናል፡፡
ቦሌ አትላስ የሚገኘው 3ኛው መንደር ሽያጭ በመገባደድ ላይ ሲሆን ግንባታውም በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ አሁን ደግሞ የድርጅቱ 4ኛ መንደር በሆነው የሲኤምሲ ሳይት ላይ ከባለ አንድ መኝታ እስከ ባለ 4 መኝታ አፓርትመንቶች እና ሱቆችን ላይ ልዩ ቅናሽ አድርጓል፡፡

Ethiopia Media Parter

Ethiopian Broadcasting Corporation

Other Media Parter




United Kingdom Office: 78 York Street London W1H 1DP UK. +44 (0) 2076925669
Africa Regional Office: Merit House, Maitama Abuja. +234 (0) 8137383109
admin@finmagazine.com www.finmagazine.com

fIN
Foreign Investment Network

# FIN FORBES PARTNERSHIP

fIN
Foreign Investment Network

**FIN and Forbes best of Africa have had long time business relationship, organizing successful events, publications and award receptions together.**

**Some of the past FIN/FORBES events include the following**

1. **FIN Forbes Oil and Gas Best of Africa Summit London 2018**
2. **FIN Forbes Banking Event, Washington DC 2017 USA**
3. **FIN Zimbabwe Investment Forum and Forbes Reception 2019**

**4.IN Philanthropy and Award Ceremony 2020**

**5.FIN Philanthropy and Award Ceremony 2021**

**5.FIN Trade & Investment Forum, Burj Al Arab Hotel, Dubai UAE 2021**

**6.FIN Cashless Africa Conference, Accra Ghana 2021**

**7.FIN Mahabiz Business Summit, Dubai UAE 2022**

**8.FIN Block Chain Conference, Dubai UAE 2022**

















# አዲስ አበባ

## Addis Ababa



## የአፍሪካ መዲና

## Capital of Africa






I.S Promotions &
Special Events

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት
ETHIOPIAN DIASPORA SERVICE